በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የማህበራዊ ጉዳይ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንዳፍታ



## በስደት ያሉት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለ መጠይቅ

## በዚህ እትም


- ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)
  ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ (ገብርዬ)
- ጦርነቱን በተመለከተ ሰፋ ያለ ዜና
- "አዲሳባና አዲስ አበቤው ባዲሳብኛ" (ከጦራ ጦጦራ)
- "የመከላከያ ኃይላችንን ለማሽመድመድ ..." (ከምንተስኖት)
- ማህበራዊ ጉዳይ
  "መስቀል—መስቀል መንገዶች ሁሉ ወደ ጉራጌ አገር"
  "ከሠርግ በፊት ስለሚደረግ ዕቅድ"
  (ከበደ ኃይሌ)



ህዳር
፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
፯ኛ ዓመት
ቁጥር ፪

LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
December 1998
Vol. 7 No.2

# L & M GLOBAL SERVICES, INC.

450 N. Indian Creek Dr., Clarkston, GA 30021
Phone: 404-296-3088 - Fax: 404-296-7413

## ታክስ በማዘጋጀት ልምድ ባላቸው፤

- ✈ የግልና የንግድ
- ✈ ፈጣን የታክስ አገልግሎት
- ✈ ፌዴራልና ስቴት
- ✈ አሜንድድ ሪተርን

ጥያቄ ካልዎት ለአከን ያነጋግሩ።

ለአከ ማለደ — LEAKE MALEDE

AUTHORIZED IRS e-file PROVIDER

*Member of National Society of Tax Professionals*

## RTS ACCOUNTING & INCOME TAX SERVICE

Professional Tax Preparation

- Indiviadual & Business
- Electronic Tax Filing
- Federal & State Return
- Amended Return

### Other Services:

- ⇒ **Prepare monthly Sales Tax Report**
- ⇒ **Prepare Business Loan Package**
- ⇒ **Book Keeping Service**

Choose how fast you want your Refund:

- ♦ Electronic Refund
- ♦ Direct deposit
- ♦ I.R.S. Check

# ASAP COPIES

**The Mission of ASAP COPY Center** Quality service as cost effectively as possible.

**Turn Around Time:** The Copy Center can turn around most jobs in 24 to 48 hours based on 1. The time the order received 2. Other work in progress 3. The size of the job, special stock requirements amound of bindery requirements.

**The ASAP COPY offers:** Copying of all your jobs, large & small. 20# white 8 1/2x11 1 plain or 3 hole drilled paper. Variety of colored paper and cover stock letter head. Transparencies. Stapling. Collating.

**Consulting service** on how to produce the most professional look at the most reasonable price.

- √ FLYERS
- √ BUSINESS CARDS

- √ Typesetting
- √ High-Speed Duplicating
- √ Fax service
- √ Self-Serve Copies
- √ Passport Photo
- √ Immigration Photo
- √ Resume
- √ Flyers

*MoneyGram*
*Money sent worldwide*
*Authorized MoneyGram Agent*

*We are located at Campus Plaza Mall across from Dekalb Book Store*

# With Gratitude!

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለቤተሰብ ለዘመድና ለወዳጅ ወደ አዲስ አበባ ለመላክ
ሲያስፈልግዎ በ2 ሰዓት ውስጥ አዲስ አበባ በሚያደርሰው

ፈጣንና አስተማማኝ በሆነው ድርጅታችን ይጠቀሙ።

| | |
|---|---|
| በግ (ከነቆዳው) | $39.99 |
| ኩንታል ጤፍ | $69.99 |
| ዶሮ | $ 5.99 |
| ውስኪ (ጆኒ ዎከር) | $29.99 |
| ሻምፓኝ | $19.99 |
| የተለያዩ ፍራፍሬዎች ለሕመምተኛ ለማቀበል (በ45 ደቂቃ) | $19.99 |
| ለእዝን እንጀራ ከሁለት ድስት ወጥ ጋር (በ45 ደቂቃ) | $59.99 |
| ኬክ | $15.99 |
| የማር ጠጅ | $ 9.99 |
| አበባ ቡኬ | $10.99 |
| ኪሎ ቡና እንዲሁም ኪሎ ስኳር | $14.99 |
| ጠበል ለሚፈልጉ ሰዎች በመኪና ማጓጓዝ | $እንደርቀቱ |

## ለሠርግ ስጦታ

| | |
|---|---|
| የተሟሉ የሻይ ሲኒ ከኬክ ሳህን ጋር | $59.99 |
| የተሟሉ የወይን ጠጅ (WINE) ብርጭቆዎች | $59.99 |
| የተሟሉ የጭማቂ ብርጭቆዎች | $59.99 |
| የተሟሉ የሻምፓኝ ብርጭቆዎች | $49.99 |
| የተሟሉ የምግብ ሳህኖች ከብርጭቆዎች ጋር | $129.99 |
| ሳምሰንግ 20 ኢንች ባለቀለም ቴሌቪዥን | $519.00 |
| ሰንጋ በሬ | $589.99 |
| ሰርገኞች ባህርዳር ለማዝናናት በአውሮፕላን እስከ 9 ሰው | $889.99 |
| ላንጋኖ ለንፋስ ቅየራ እስከ 9 ሰው —አዋሽ ላይ ነፃ ለስላሳ ብስኩትና ሻይ | $169.99 |
| ሶደሬ ለማናፈስ እስከ 9 ሰው— ሞጆ ላይ ነፃ ለስላሳ ብስኩትና ሻይ | $119.99 |
| ለአራስ ጥሪ | $59.99 |
| ከ2 እስከ 10 ዓመት ዕድሜ ለሆናቸው ልጆች የልደት ስጦታ | $69.99 |

ከዚህ በላይ በዝርዝር ካቀረብናቸው ሌላ የሚያስፈልግዎት ዕቃ ካለ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ያልገቡ ዕቃዎች ስላሉን በስልክም ሆ በፋክስ ቢጠይቁን ለመርዳት ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽን፣

አዲስ አበባ ቤተሰባችሁ በር ድረስ ስለምናደርስ ለስልክ ገንዘብ ከማባከን፤ በባህላዊ ሥነሥርዓት ቤተሰባችሁንና ዘመዶቻችሁን አስደስቱ።

የዚህ ሺያጭ ትርፍ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ለሚከፈተው ቤተ መጽሐፍት ይውላል።
እናመሰግናለን!!

አድራሻችን 13831 MENLO AVE GARDINA, CA 90247

**ስልክ (310) 532—4177**

**የጽሑፍ መልዕክት ቁጥር (FAX ) 310—532–4619**

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

5 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

7 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

11 የአንባብያን መልዕክት (ደብዳቤዎቻችሁ)

16 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

23 ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

26 "አዲሳባና አዲስ አበቤው ባዲሳብኛ" (ከጦራ ጦጦራ)

32 "የመከላከያ ኃይላችንን ለማሽመድመድ . . ." (ከምንተስኖት)

33 ማህበራዊ ጉዳይ
"መስቀል—መስቀል መንገዶች ሁሉ ወደ ጉራጌ አገር"

"ከሠርግ በፊት ስለሚደረግ ዕቅድ" (ከበደ ኃይሌ)

39 ዜና ቤተክርስቲያን

40 የግጥም ጉባኤ

42 ከዚህም ከዚያም

44 ከአበው — ትምህርት በምሳሌ (መጋቤ አዕላፍ መክብብ ይጥናው)

45 ቢስቁም ባይስቁም

46 የሰንጠረዥ ጨዋታ

47




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

ለሰላም
ለፍቅር
ለአንድነት
መደማመጥ
መቻቻል!


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1998

ላንዳፍታ
ሀዳር ፲፱፻፺፩
፭ኛ ዓመት ቁጥር ፩
LANDAFTA
DECEMBER 1998

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ
**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*
**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Saefu Bishaw*
*Rev. Mekbib Atnaw*
**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Getachew Metaferia*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*

## Distribution

Atlanta, GA
California Mart
Express Food Mart
H & B Shop
Merkato Market
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Denver, CO
Emebet Worku
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
London
St.Gabriel Ethiopian Delicatseen
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Santa Clara, CA
Nathan Graphics
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Lideta Market (Arlington)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል፤ ይኸው ስንንደፋደፍ ከርመን ብቅ ብለናል። እንዘግይ እንጅ አልቀረንም። የአለፈው እትማችን ትልቅ መልዕክት ይዞ ነበር የወጣው። "ብሔራዊ ዕርቅ" የመጥራቱን ጉዳይ በቀላሉ የምንመለከተው ጉዳይ እንዳልሆነ ገልፀናል። ወገናችን እሮይ ብለው ከጦርነት ይልቅ ስለሰላምና ብልፅግና እንዲያስቡ ማድረግ የሚቻለው "ብሄራዊ ዕርቅ" ሲሰፍን ነው። ጠብ ካለ ሰላም የለም፤ ሰላም ከሌለ ዕድገት የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በእኩልነት በአገሩ ጉዳይ ተሳትፎ ሊያደርግ የሚችልበት መንገድ ተግባር ላይ ካልዋለ ዕድገት ይኖራል ማለት ዘበት ነው። "በፍቅር፤ በሰላም በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥ፤ መቻቻል!" የምንለው የዕድገት መሠረቱ እሱ ስለሆነ ነው።

በአሁኑ እትም ብዙ ግልፅ የሆኑ የአንባብያን ደብዳቤዎች ወጥተዋል። እነኚህ ደብዳቤዎች ስህተቶቻችንን የሚጠቁሙ በመሆናቸው በቀና አመለካከት እንድናያቸው ይገባል። ሌላውን ለማረም የምንሻ ሁሉ እኛም ለመታረም ዝግጁ መሆን አለብንና የመጡትን የአስተያየት ደብዳቤዎች እንዳለ አውጥተናቸዋል።

ተከታታዩ የአብረኸት ታሪክ "ዕጣዬ" ባለፈውና በዚህኛው እትሞች ላይ ባለመውጣቱ ታሪኩ አለቀ ማለት አይደለም። በስልክና በደብዳቤ ለጠየቃችሁን አንባቢያን ታሪኩ ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ ይቀጥላል።

የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- landafta@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## ከወርቃየሁ (ሸገር)

ውድ ገብርዬ!

ለጤናህ እጅጉን እንደምን አለህ? እኔ/እኛ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ይመስገን በጣሙን ደህና ነን። ገብርዬ ለመሆኑ አዲሱ ዓመት እንዴት ይዞሃል? እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘመን መቁጠርና የርዕሰ አውደ ዓመትን በዓል ማክበር ከጀመረች እነሆ 1ሺህ 991 ዓመት ሆነ። አዲስ ዓመት የሰው ልጆች የአዲስ ተስፋና ሀገራዊ ራእይ መባቻ እንደመሆኑ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በልዩ ደስታና የትዝታ ስሜት ይከበራል ... ይዘከራል። ከዘመን ወደ ዘመን መሸጋገር ማለት በዕድሜ ላይ አንድ ዓመት መጨመር ማለትም ነው። ብዙዎች አዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ ቆም ብለው የኋላውን በትዝታ እያስታወሱ፣ የወደፊቱን በተስፋ እየተመለከቱ ራሳቸው ለራሳቸው ቃል ይገባሉ። ለመማር፣ ለማግባት፣ ለመሻሻል ይወስናሉ። ማህበራዊ ህይወታቸው የሚስተካከልበትን፣ ጎጂ ነገሮች የሚወገዱበትን የመፍትሔ ሃሳብ ይፈልጋሉ። የዘንድሮው ግን ትንሽ ለየት ይላል፤ ሁሉም ይህን አዲስ ዓመት የሚጠብቀው ከጦርነቱ መጀመር ጋር ነበርና ውስጡ ብዙም የደስታ ስሜት አልተሰማውም። ጦርነት የሰውን ህይወት ሳይቀስፍ የማይከናወን ድርጊት በመሆኑ እነዚህ ሰዎች ነገራቸውን በሰላም ይፈቱት ይሆን እያለ መመኘቱ አልቀረም። ሆኖም እስካሁን ጦርነቱም አልተጀመረም፣ ነገሩም በሰላም አልተፈታም፣ መሬታችን ግን ከ6 ወራት በላይ በሻዕቢያ እጅ እንዳለ ነው። ገብርዬ እንደ ዕድል ሆኖ ኤርትራውያን ሁሌ እንደጨፈሩብን ነው። ኤርትራ "ነፃ" ስትወጣ ጨፈሩ፤ ባድመ ሲያዝም ጨፈሩ፤ የመቀሌና የአዲግራት ህዝብ በክላስተር ቦንብ ስለታቃጠሉ ጨፈሩ። ይኸ ለእኛ የሚያስቆጭ ነገር ነው። ለእነሱ ግን ... ገብርዬ!

ወደ ጦር ግንባር ልውሰድህና ዛሬ ወታደሩ በባድማና በሽራሮ ጠመንጃውን እየወለወለ ጀምር የሚለውን ትዕዛዝ በመጠበቅ ላይ ነው። ሠራዊቱ በየዕለቱ ብረት መወልወሉ ብቻ ዋጋ የሌለው መሆኑ እየታወቀ ትዕዛዙን የሚሰጡት ወገኖች ምን እንደሚጠብቁና መቼ ይሁን እንዴት እንደሚሉ የሚያውቀው ያው ኢህአዴግ ብቻ ነው። የሆነ ሆኖ ዘማቹ ሠራዊትም ሆነ ህዝቡ እንዲሁም መንግስት ስለወቅቱ ሁኔታ የየራሱን ትርጉም ሰጥቶ ሁሉም በየፊናው ምክንያቱንና ግምቱን ይናገራል። ዘማቹ ሠራዊት ከመደበኛው የወያኔ ጦር በስተቀር በአብዛኛው ኑሮ የመረረው፣ አንዳንዱ ደግሞ ከዚህ በፊት ከኤርትራ ምድር በባዶ እግሩ ራቁቱን የተባረረና አንጀቱ የደበነ ዛሬ ያለመው ደርሶለት ቁጭቱን በሻዕቢያ ሊወጣ የሚፈልግ፣ አንዳንዱ ደግሞ ከነጭራሹ ለምንና ለማን እንኳን እንደሚዋጋ በደንብ ሳያውቅ በግዳጅ የመጣ ገበሬ ቊምር ይገኝበታል። ይህ በአጠቃላይ "ካልፈላ ሽሮ ይሻላል ሽራሮ"፣ "ከባድማ መልስ አለለት መለስ" ... በሚል የተለያየ ስሜት የዘመተ መሆኑ ይነገርለታል። በጦርነቱ አጀማመርና አሁን ያለበት ሁኔታ ላይ ጥርጣሬ ያለው ህዝብ ደግሞ ሠራዊቱ በጦር ሜዳ የሚደረግለትን መስተንግዶ በትዝብት እያየ "ከመቼ ወዲህ ነው ለጦርነት የሚዘጋጅ ሠራዊት እርጐ ጠጥቶ፣ ብርዝ ጠጥቶ፣ ትኩስ ፍየል አርዶ በልቶ ለጦርነት የሚሰለፍ፣ ኧረ ከደነደኑ እንኳን ጋራ ሽንተረር ለመውጣት ወድቆ መነሳትም ይቸግራል" እያለ የየራሱን ምክር አዘል ቅሬታውን ያስተጋባል። "የመንታ እናት ተንጋላ ትሙት" በሚለው ብሂል አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ደግሞ ለብቻቸው

"አንጀቴና ሆዴ ተጣልተውብኝ፣
አንተም ተው አንተም ተው ብዬ እንዳልለው
አንጀቴም አንጀቴ ሆዴም ሆዴ ነው፤
ለማን እፈርዳለሁ ፍርድ አያውቅም ሰው"

በማለት ማቀንቀን ጀምረዋል። ሌላው ጦርነቱ በተቀሰቀሰበት ሰሞን የሻዕቢያን ወረራ በተመለከተ ይሰጧቸው በነበሩ መግለጫዎች ሳቢያ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ስልጣን ለእሳቸው ይሰጥ እስከመባል ደርሰው የነበሩት አቶ ስዩም መስፍን (የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር) ዛሬ በአምስት ወር ልዩነት ውስጥ እንደገና ቃላቸውን አጥፈው ጦርነቱ ለምን ዘገየ? ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ "ሻዕቢያን በትዕግስት የምንጠብቀው ወረራው እንደማያዋጣው ተረድቶ ራሱ ይለቃል ብለን ስላመንን ነው፤ እናም የእኛ ትዕግስት በተለያዩ መንግስታት ስለተደገፈ እስከመጨረሻው ድረስ ትዕግስትን መከላከያ አድርገን እንጠብቃለን" ይሉናል። ጋሼ ትዕግስት!!

ገብርዬ!

በተደጋጋሚ እንደተወሳው ጦርነት በሁለት ጐራዎች መካከል የሚካሄድ ፍልሚያ ... አንዱ ሌላውን በኃይል ለማንበርከክ የሚካሂደው ትግል ጥቅምን ከሌላኛው ለማግኘት ነው ተብሎ ቢጠቀስም ግንቦት 4 ቀን 1990 ይፋ የሆነው የኢትዮ–ኤርትራ የድንበር ውዝግብ በተዘዋዋሪም ቢሆን እስካሁን ያልተስዋለን ቁም ነገር ሊያስጨብጠንና በጦርነት ሽፋን የራስን ጥቅም እንደምን ለመጠበቅ እንደተቻለ ያስገነዘበ ቊምር ነው ማለት ይቻላል። የዘወትር ህልሙ ወረራ የሆነውና ከወዳጁ ማርጀት የማያውቀው አብራተኛው ኢሳያስ ባድመና ከፊል ሽራሮን መውረሩ ከተገለፀ በኋላ የተነገረን አዋሳኝ ቦታዎችንም በስፋት ለመያዝ ያደረገው ሙከራ እንዲመክን መደረጉ እንጂ በኃይል ከያዛቸው ቦታዎች ለቆ እንዲወጣ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ አይደለም። ስድስተኛ ወሩን ባስመዘገበው በዚህ የድንበር ውዝግብ ሳቢያ ዙሪያ የኢትዮጵያ መሪዎች ያልነገሩንና ያላሉን ነገር እንደሌለ የምታውቀው ነው። መሪዎቹ ውዝግቡን በሰላም ስለመፍታት የሚያወሱት ጉዳይም ሆነ ውዝግቡን አስመልክቶ የሚነግሩን ሁሉ ራሳቸውን ከእለት እለት እያጋለጠ መምጣቱ ይፋ ከሆነ ሰንበትበት ቢልም አዲስ ሀሳብ አዲስ ዘዴም ተብሎ የተሞከረው ተስፋም ከፊተኞቹ ያልተለየ ሆኖ ተገኝቷል።

እንዲያውም የመጨረሻው ሳይቋጭ ሲተረተር ነው የሚታየው። የሰላም ፍለጋው ጥረት ቢሟጠጥም የሚሉት የማያጡትና ምክንያት መፍጠር የማይሳናቸው መሪዎቻችን ሻዕቢያ ወደደም ጠላ ከያዘው ቦታ ይለቃል ይሉናል። ዛሬም።

በምን መልኩ? ... በተአምር ...? ሰራዊቱ ሉዓላዊነቱን እንዳያስከብር ግዳጁን እንዳይወጣ እግር ተወርች ተቀፍድዶ በጥጥ ለቀማ፣ በመሰረተ ትምህርት፣ እርሻና በመሳሰለው ተጠምዶ እንዴትና እንደምን ሊሆን ይችላል? መሪዎቻችን ግን ለዚህም መልስ ለመስጠት የሚሳናቸው አይደሉም። "... ሻዕቢያ ወረራው የትም እንደማያደርሰው ተገንዝቦ ራሱ ይለቃል ... የኤርትራ ህዝብ በሚያደርግበት ተፅዕኖ" ይህን የመሰለ ምክንያት በመደርደር ለምን እስካሁን ወደ ጦርነቱ ዘልቀው እንዳልገቡ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም የተያዙትን ቦታዎች በኃይል ለማስለቀቅ ፍላጐት እንደሌላቸው በተዘዋዋሪ ሊያሳምኑን ዳር ዳር ይላሉ። ሻዕቢያ ወረራው የትም እንደሚያደርሰው ለመገንዘብ የሚያበቃው ምን አዲስ ነገር ተገኘ? የኤርትራ ህዝብ ተፅዕኖ ያደርግበታል የምትለዋን ምክንያት ማን ሹክ ብሏቸው ይሆን?

የኢትዮጵያ መንግስት መሪዎች በውዝግቡ መነሻ ዘለው ወደ ጦርነቱ ያለመግባታቸው ተደጋጋሚ ድጋፍ አግኝቷል። ከጦርነት ውድቀት እንጂ እድገት የለምና። ሆኖም ግን ሊገድል የመጣን ጠላት ሺህ ጊዜ ጌታዬ ቢሉት ቢያቀማጥሉት እንዳይምር እየታወቀ፣ የመጣውን ጠላት ተከላክሎ ግዛትን ያለማስከበር በኢትዮጵያ በኩል ጉልቶ ያለመስተዋሉ እንዲያውም ጥረቱ የሌለ መሆኑን ማንኛውም ለሀገሩ የሚቆረቆር ኢትዮጵያዊ ሲገነዘብ ወያኔ በሰላም ፈላጊነትና ትዕግስተኝነት ከሚፈረጅ በበለጠ በአንድ ወይም በሁለት ምክንያት ሻዕቢያ በኃይል ከያዛቸው ስፍራዎች ለቆ እንዲወጣ የኃይል እርምጃ መውሰድ እንደማይሹና ወደ ጦርነቱ ለመግባት እንደማይፈልጉ የሚጠቁም ነው።

ገብርዬ! ላስታውስህ የምፈልገውና ለዚህ ምክንያት ይሆናሉ የምላቸው ነገሮች አሉ። እነሱም 1) የውዝግቡ ኢላማ የሆነችው ትግራይ ባለፉት ሰባት አመታት ከጦርነት ተላቃ ፊቷን ወደ ልማት በመመለስ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክልሎች በተለየና በጐላ መልኩ የልማት እንቅስቃሴ አድርጋለች። ከአብራኳ የፈለቁትና አገሪቱንና ህዝቡን ሲላቸው የሚነዱት ሲሹ የሚያሽከረክሩት መሪዎች ያሰቡትን "የትግራይ ሪፐብሊክን" ለመመስረት ብዙ ብዙ ጥረውላታል። እናም ጦርነቱ ቢጀመር ሻዕቢያ እነኚህን በአጭር አመታት እውን ያደረገቻቸውን የልማት መሰረቶች ከማውደም ወደ ኋላ እንደማይል በእርግጠኝነት ያውቃሉ። ወሳኙ ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው እዚህ ገደማ ነው። መሪዎቻችን የሚለሳለሱትና የሰላም ተስፋ እንደጤዛ መትነኑን እያወቁ ነጋ ጠባ ስለ ሰላም የሚሰብኩት ምናልባት ከዚህ ስጋት በመነጨ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። የኢትዮጵያ መሪዎች ጉዳዩን ግልፅ ከማድረግ ይልቅ ሁሌም መሸፋፈን በለመደ አንደበታቸው የሌለ ተስፋ ከሚመግቡን ስጋታቸውን ይህ ከሆነ ግልፅ ቢያደርጉ ይመረጣል ባይ ነኝ።

2) እርዳታውን በተመለከተ፣ የእርዳታው መጠንና አይነት ተጠቅሶ የማያልቅ ነውና መግለፁ ባያስፈልግም ምናልባት ዛሬ ለሌላ ሌላ ኢህአዴጋዊ አላማ እየዋለ ያለውና በጦርነቱ ስም የሚሰበሰበው እርዳታ ጦርነቱ ከተጀመረ የማይታሰብና ቀጥታ ለታለመለት ለጦርነቱ ጉዳይ የሚውል ሊሆን ይችላልና ይህም ኢህአዴጋውያኑን የሚጎዳቸው ስለሚሆን በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጦርነቱ እንዲጀመር አይፈልጉም ብዬ የራሴን ድምዳሜ ሰጥቻለሁ። አንተስ? እናንተስ? ምን ትላላችሁ እውን ኢህአዴግ ሰላም ፈላጊ ነውን?

ውድ ገብርዬ!

ባለፈው ከኢትዮጵያ የተባረሩ ኤርትራውያንን ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ የጫነ መኪና ያሰማ የነበረውን ሙዚቃ ሰምቼ በጣም ድንቅ ብሎኝ ለትንሽ ደቂቃ ቆም ብዬ አደመጥኩት። ዘፈኑ ምን መሰለህ? የአስቴር አወቀ «አገር አገር ይላል ይኼ አገረ ብርቁ፣ እኔም አገር አገር አለኝ የሚታይ በሩቁ" የሚለው ነበር። እንደእኔው በሙዚቃው ምርጫ የተገረመች አንዲት መንገደኛ አንገቷን እየነቀነቀች ስትሄድ አይቼ እኔም እንደሷው አንገቴን እየነቀነቅኩ ከልቤ ጋር ብዙ ነገር ተጠያየቅኩ። እውን ይኼ ጦርነት የእውነት ነው? ማንን 'ው የሚጎዳው? ማንንስ ነው የሚጠቅመው? ያቀነባበረውስ ማነው? ለሚሉትና ለመሳሰሉት መልስ ላላገኘሁላቸው ጥያቄዎች ራሴን ሳፋጥጥ ቆየሁ። ግን መልሱን የሚያውቁ በነገሩ ያሉበትና የሁሉን ውስጠ ምስጢር የሚያይ አንድዬ ብቻ ነው። ግን ገብርዬ ልብ እንድትልልኝ የምፈልገው አንዳንዴ በዚህ በማባረሩ ሂደት ግልፅ ያልሆኑ ሁኔታዎች ይታያሉ። ለምሳሌ አብዛኛው ከኢትዮጵያ የተባረረው ኤርትራዊ በተራ ሰራተኛነት የተቀመጠ፣ ወይም ደግሞ አነስተኛ ነጋዴ የሆነ እንጂ ይሄ ቱጃር ቱጃሩ "ናፅነት" መምረጡና ኤርትራዊነቱ በግልፅ እየታወቀ ዛሬም እንደድሮው በማንአለብኝነት እግሩን ሁለት ቦታ እንፈራጠ ንግዱን ያጧጡፋል። እንዲያውም ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ አይነት ሆኖለታል። እንዲሁም በተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ላይ ያለውም ኤርትራዊ እንደዚሁ ማንም ሳይነካው ቁጭ ብሏል፤ ተባርሮ የነበረውም (ደሞዛቸው ግን ሳይሰሩ እየተከፈላቸው እንደነበር ሳልጠቅስ ማለፍ አልፈልግም) ደግሞ በምን ምክንያት እንደሆነ ሳይታወቅ እንደገና ስራ ገበታው ላይ ተሰይሟል። እና እነዚህንና ሌሎች ነገሮችን ስታይ የሚሰራው ድራማ ምን እንደሆነ ግራ ይገባሃል።

ወዳጄ ገብርዬ!

እስቲ ይህን ያልኩህን እውነታ ለማገናዘብ ይረዳህ ዘንድ ዛሬም "ኤርትራ የኛ ኢትዮጵያ የጋራ" ብለው የተቀመጡ ሰዎች መኖራቸውን የሚያስረዳ መረጃ ልስጥህ፤ በንግድ አለም ከተሰማሩት ኤርትራውያን ውስጥ በእርግጥ ብዙዎች የተባረሩ መሆናቸው ቢታመንም ዋና ዋና የሚባሉት በሬፈረንደሙ መሳተፋቸው በግልጽ የሚታወቅላቸው የ)ምሶን ዳቦ ቤትና የቀስተ ደመና ስፖንጅ ፋብሪካ ]ለቤት አቶ አቢሶሎም ይህደጉ፣ የያኮና ኢንጅነሪንግ ባለቤት አቶ ሮበርት ያኮና፣ የበላይ ተክሉ ኬክ ቤት ባለቤት አቶ በላይ ተክሉ፣ የሸዋ ዳቦ ቤት ባለቤት አቶ ዘሙይ ተክሉና የመሳሰሉት ንግዳቸውን ያለከልካይ በግልፅ ይነግዳሉ።

ህዝቡና ነፃው ፕሬስ በየመድረኩ በሚያሰማው

ጨኸት በመብራት ኃይልና በቴሌ ውስጥ በኃላፊነት የተቀመጡት ኤርትራውያን ቢነሱም በንግድ መርከብ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮና በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙ ኤርትራውያን ዛሬም በስልጣን ላይ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል። በአንድ ወገን ሶሪያዊ በሌላ ወገናቸው ደግሞ ኤርትራዊ የሆኑት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዋና ልዩ አማካሪና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ዶ/ር ፋሲል ናሆም ዛሬም በዚሁ በተጠቀሰው ስልጣናቸው ላይ እንደሚገኙ በተጨባጭ ማረጋገጥ ተችሏል። ዶ/ር ፋሲል ናሆምም የኑ ሚስታቸው የውጭ ሃገር ዜጋ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተሳስራቸው አንድም ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ሰውየው በዚሁ ስልጣን እንዲቀጥሉ ማድረጉ በእጅጉ አጠያያቂ ከመሆኑም ባገር ዶ/ር ፋሲል በደርግም ስርዓት ደርግን ሲያገለግሉ ቆይተው በወያኔ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታቸው ሌላው ጥርጣሬውን የሚያጉላው ጉዳይ ሆኗል።

በዚህ በዶ/ር ፋሲል ናሆም በሚመራው የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ውስጥ በምክትልነት የተሾሙት አቶ መስፍን እቁበ ዮሐንስም ኤርትራዊ መሆናቸውን በቅርብ የሚያውቋቸው በእርግጠኛነት ይናገራሉ። እንግዲህ ገብርዬ ልብ በልልኝ እነዚህ ሁለት ኤርትራውያን በበላይነት የሚመሩት ተቋም ነው የኢትዮጵያን ነባር ህጐችን የማሻሻሉ ተግባር የተጣለበት። አዲሱ የዜግነት ህግም በዚሁ ተቋምና በእነዚህ ሰዎች የበላይነት ተጠንቶ ለሚመለከተው አካል ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ እንደሚፀድቅም ይጠበቃል። ሌላው በኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ውስጥ በዋና ስራ አስኪያጅነት የሚመሩት አቶ አምባቸው አብርሃም ኤርትራዊ ቢሆኑም ቅሉ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ቦርድ ሊቀመንበር ከሆኑት ሜጀር ጄኔራል ፃድቃን ገ/ተንሳይ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስላላቸው የሚደፍራቸው ሰው አልተገኘም። በተጨማሪ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ የአውሮፓና አሜሪካ ዲስኮች ዳይሬክቴር በመሆን የሚያገለግሉት የቀድሞው የአኢወማ ከፍተኛ አመራር አቶ ሀሩይ አማኑኤል፣ እንዲሁም በዚሁ መሥሪያ ቤት ውስጥ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቀጥሎ ያሉና ከተለያዩ ዲስኮች የሚመጡ ሪፖርቶችን ተመልክተው ለሚኒስትሩ የሚያቀርቡትና ወሳኝ ስልጣን የያዙት የማነ ኪዳኔ(ጃማይካ) ሁለቱም ኤርትራውያን ናቸው። አቶ የማነ ኪዳኔ ቀደም ሲል የሻዕቢያ አባል የነበሩና ህወሐት ሲመሰረት በኢሳያስ አፈወርቂ ትዕዛዝ ህወሐትን ለመቆጣጠር የተቀላቀሉ ሰው መሆናቸውን ራሳቸው ወያኔዎች ባሳተሙት "ተራራውን ያንቀጠቀጠው ትውልድ" በሚለው መጽሐፍ ላይ መጠቀሱ ይታወቃል።

ገብርዬ!

እነዚህ የጠቀስኩልህ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም በእንደዚህ ያለ የመንግስት ኃላፊነት ቦታ ላይ እንዳሉ በስፋት ይነገራል። ታዲያ የሻዕቢያ ጦር የሚፈልገውን መሬት በእጁ እስኪያደርግ ስለሁኔታው በግልፅ እያወቁ አልሰማንም አላየንም ብለው የቆዩ "የኛዎቹ" ባለስልጣናት ዛሬም ትዕግስት ትዕግስት ቢሉን ምን ይደንቃል? በአንፃሩ እነ አባይ ፀሐዬና እነ ... እዛች እንደቀልድ አንድ ዛፍ ጥላ ስር የተፈራረሚትን ካርታ ጉዳይ ተግባራዊ ለማድረግ ሩጫው ሲጀመር፣ "ቁጭ ብለው የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ ይቸግራል" ቢሉ ዛሬ ማን ይሰማቸው!!

ውድ ገብርዬ!

ወደናንተው ልምጣና ባለፈው ከወደ አሜሪካ፣ ከአውሮጳና ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡት "ተወካዮች" የማን ተወካዮች እንደሆኑ ካነጋገራቸውና ከቋንቋቸው፣ ከጥያቄዎቻቸውና ከድጋፎቻቸው ለየናቸው "እንኳን ይቺንና የዘንብ ..." እናውቃለን ብለን ነገርናቸው። እንደው የደነቀኝ እዚህ ያለውስ ችግር ይሁት ለሆዱ አደረ እንበል እዛ ያሉት ደግሞ ለምን ብለው ይሆን ለመለስ መንግስት እንዲህ የሚሟገቱት? ያ ሁሉ ሙገሳስ ለምን አስፈለገ? እንዲህ በሰለጠነው ዓለም ኖረናል የሚሉት ሰዎች ለባለስልጣን ከንቱ ውዳሴ ይህን ያህል ማጉብደዳቸው ሊገባኝ አልቻለም። ባለፈው ከወደዚሁ ከአዲስአባ ጦራ ጦጦራ የወቀሳችሁ ለካ በእውነት ኖሯል እኔ መጀመሪያ ትንሽ ቅር ብሎኝ ነበር፤ አሁን ግን እነዚህ "ተወካዮችን" ሳይ ከጦራ ጦጦራ ጋር ግንባር ፈጠርኩ። በእውነት ገብርዬ አንተና አንተን መሰል ሰዎች ባሉበት አገር እንደነዚህ ያለ አገርና ታሪክ አስወቃሽ ሰው በመፈጠሩም ከልቤ አዘንኩ። እነዚህን በብርቱ ልትዋጓቸው ያስፈልጋል። በ1ወር ለብ ለብ ጉብኝት ኢትዮጵያን አወቅናት ሊሉን ፈለጉ። ባለስልጣኖች የነረጓቸውንም መልሰው ለእኛው እዚሁ ላለነው ሊነግሩን፣ የኢህአዴግን ደግነት ሊያስረዱን ሞከሩ። እነዚህ አገር አቋርጠው የመጡት ሰዎች እውነት የዕርዳታን ምንነት አውቀው ቢሆን ኖሮ ለዛ ሁሉ ሰው ለትራንስፖርትና ለሌላም ሌላ የወጣውን ወጪ አስቀርተው በባንክ ገንዘቡን ቢልኩትና "በጦርነቱ ለተፈናቀሉት ወገኖች" ቢሆን አይሻልም ነበርን? እኛ ግን አመጣጣቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ወደ እነሱ መምጣት ስለተሳናቸው ናፍቆት ይዟቸው እንደመጡ ከሚናገሩት ተረዳን። አንዱ "ተወካይ" አይኑን በጨው አጥቦ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እኔ እርስዎን ያየሁዎት የዛሬ 16 ዓመት ገደማ ጫካ ነበር ... ሲል እኔ ለእሱ አፍሬ ጤፍ አከልኩ። አሁን አሜሪካ ከኖረ ሰው ይሄ ይጠበቃል? ምናለ የውስጥ ገበናውን ባያወጣ? ብቻ ገብርዬ የእነሱ ነገር ቢወራ አያልቅም እንዲያውም ለበሽታ ይጥልሃልና በዚሁ ልተወው። ብቻ ለማንኛውም እኛ ከየትና የማን እንደሆኑ ለይተናቸዋል ብቻ ያሳዘነን እንዲህ ሌት ተቀን ለፍታችሁ ያገኛችሁትን ገንዘብ ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች "ተወካይ" ብላችሁ መላካችሁ ነው።

ገብርዬ!

ባለፈው ጽሁፌ የራሴን ወይም የአንጀቴን አውጥቼ ባላወጋህም አንድ ልቤን የነካው ብዕርተኛ የፃፈውን እየው ብዬ ልኬልህ እንደነበር አስታውሳለሁ። እና ታዲያ የአቶ ነብዩን ሃሳብ ወይም አስተያየት አሁን ካለው ሁኔታ ጋር እንዴት አየኸው? አንተም በዚህ በጦርነቱ ምክንያት እናንተ አካባቢ ያለውን የተለያዩ አስተያየቶች ወይም አመለካከቶች በአጭሩም ቢሆን ገልፀህልኛል። ገብርዬ ስታስበው የሁሉም ሀሳብ ለየራሱ የተለያየ እውነታ አለውና ለምን ይኼኛው ይህን አለ? ለምን ያኛው ይኼን አላለም ለማለት ያስቸግረኛል። ለምን ብትል የዚህ መንግስት የፖለቲካ ሁኔታ ራሱ በጣም አጠራጣሪና ወላዋይም ሁኔታ ስለሚታይበት ጦርነቱን በተመለከተ ከእነሱ ጋር ለመወገንም ለመተውም በጣም አስቸጋሪ ነው። እናም የኢህአዴግን ሙልጭልጭ የፖለቲካ ሂደት ቢያሳይህ በማለት በተለያዩ ጊዜያት የተዘገቡትን በአጭሩ ላቅርብልህና ልሰናበትህ። ለእነዛ "ተወካዮቻችሁም" አስነብብልኝ።

* * *

"ሻዕቢያ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሬታችንን ለቆ ካልወጣ የማያዳግም ትምህርት እንሰጠዋለን! ሻዕቢያ በኃይል ወሮ ከያዘው አካባቢ መልቀቅ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ላደረሰው ጥፋት ካሳ መክፈል ይጠበቅበታል። ... ከአሁን በኋላ የምንጀምረው ጦርነት ወደን ሳይሆን ተገደን የምንገባበት መሆኑን የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ይረዳልናል ብለን እናስባለን። ወደ ድርድሩ ከመምጣታችን በፊት በወረራ የተያዙት አካባቢዎችን መለቀቅ ብቻ አንጠብቅም። ቀድሞ የነበረው የኢትዮጵያ አስተዳደርም መመለስ አለበት"

<u>ውጭ ጉዳይ ስዩም መስፍን በነሐሴ ወር 1990 ከሰጡት መግለጫ</u>

"የኢትዮጵያ መንግስት የሠላም አማራጭን አሟጦ ለመጠቀም የሚጥረው ሻዕቢያ ግትር አቋሙ የትም እንደማያደርሰው አይቶ ራሱን ከመግደል ለመዳን ሲል ተገዶ ሊለቀው ይችላል ከሚል ተስፋ ነው።"

<u>ውጭ ጉዳይ ስዩም መስፍን በጥቅምት ወር 1991 ከሰጡት መግለጫ</u>

* * *

"ኢትዮጵያና ኤርትራ በጋራ ገንዘብ መጠቀማቸው የሚፈጥረው አንዳችም የኢኮኖሚ ቀውስ አይኖርም"

<u>ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በታህሳስ ወር 1990 (አዲሱ ብር ከመቂየሩ በፊት) በጋዜጣ ከሰጡት መግለጫ</u>

"እኛ በጋራ ገንዘብ መጠቀም ያልፈለግነው በውጪ ምንዛሪያችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያሳድርብን ስላወቅን ነው"

<u>ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በግንቦት ወር 1990 በሬዲዮ ከተናገሩት</u>

* * *

"ኤርትራ መሬቷን መጠየቋ ወራሪ አያስብላትም"

<u>የኢትዮጵያ ሬዲዮ "ኤርትራ ሀኒሽን በወረረችበት ወቅት" ያሰማው ሀተታ</u>

"በአሁኑ ወቅት የሻዕቢያ መሪዎች የጉረቤቶቻቸውን መሬት የመንጠቅ አባዜ ተጠናውቷቸዋል"

<u>የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጥቅምት 11 ቀን 1991 ከተናገረው</u>

* * *

"በትግል እንደወርቅ ከተፈተነው የትግራይ ጀግና ህዝብ በመወለዱ ኩራት ይሰማኛል።"

<u>ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ከተናገሩት</u>

"ፎገራን ጀግና ነው ፋርጣን ደግሞ ፈሪ ነው እያሉ አንዱን ከአንዱ ማበላለጥ ተገቢ አይመስለኝም።"

<u>ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቅርቡ ከውጪ ለመጡ ኢትዮጵያውያን ከተናገሩት</u>

* * *

ገብርዬ አየኸልኝ አይደል? "የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም" ወይስ "በአንድ አፍ ሁለት ምላስ!" ቢባልም የእኛዎቹ ግን ይኸው እንደፈለጉ በቀን በቀን ቃላቸውንም ሆነ አቋማቸውን እንደወቅቱ ይቀያይራሉ። እና ምናቸው ይታመናል? ብቻ አምላክ ለአገሩና ለህዝቡ ታማኝ የሆነ ለኢትዮጵያ አንድነትና ደህንነት የሚያስብ መንግስት ያምጣልን ከማለት በቀር ምን ይባላል?

ወዳጄ ገብርዬ!

ፅሁፌን ከመቋጨቴ በፊት አንድ ልለው የምፈልገው ነገር አለ። ኢትዮጵያውያን ኃይላችን ሌሎች ሳይሆኑ የውስጣችን ስምምነትና አንድነት ኃይላችን መሆኑን ትናንት በታሪክ ዛሬ ደግሞ በተግባር አይተነዋል። የአፍሪካ ሸምጋዮች ጦር አስናድተው ሉዓላዊነታችንን ሊያስከብሩ አይችሉም። የአውሮፖ ህብረትም ሆነ ዩኤስ አሜሪካ ለግዛታችን መከበር ከእኛ ጋር አይሰለፉም። እናም ጊዜው የጠበቀውን የትውልድ አደራ ለመወጣት ሁሉም ስለሀገሩ ያስብ። ይህ ከሆነ ሻዕቢያም ሆነ ሌሎች ጠላቶቻችን ሳይወዱ በግዳቸው የሀፍረት ሸማቸውን ይከናነባሉ። ስለሆነም መጪው ሉዓላዊነትን የማስከበሪያ እንቅስቃሴያችን የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነትና ህብረት መሰረቱ ያደረገ መሆን አለበት።

በቸር ይግጠመን ወርቃየሁ ነኝ – ከሸገር

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከገብርዬ

የኔ ውድ፦

ሀገርን ዳር እስከዳር ያናወጠው የጦርነት ወሬና ግርግር ለጊዜው ጋብ ያለ ይመስላል፤ በዚያን ሰሞን "ገንዘብ ያላዋጣ የማርያም ጠላት ነው" ሲሉ የቃጣቸው የወያኔ ደጋፊዎችና ችኩሎች ዛሬ ዝምታን መርጠዋል። ጦርነቱ ቢነሳ ወይም ቢቀሰቀስ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይመለከት ሁሉ ገንዘብ በማዋጣቱ ድምፃቸው ጉልቶ የሚታየው የወያኔ ደጋፊዎች ወይም አባሎች ነበሩ። ሀገር ቤትም እኛን "ወክለው" የመጡትን ኢትዮጵያውያን ሳትታዘብ የቀረህ አይመስለኝም። ለመሆኑ በየትኛው ስብሰባ ነው አሜሪካና አውሮጳ የሚገኙትን የወከሉት? ባለፈው እንደገለፅኩት ጦርነቱ ቢቀሰቀስ ተቃዋሚዎች ሁሉ ከትግራይና አፋር ህዝቦች፤ (ማለትም የጦርነቱን የመጀመሪያ ገፈት ቀማሽ ከሆኑት ወገኖቻችን ጐን) እንደምንሰለፍ ገልጠናል፤ በወያኔ መንግስትም በኩል ለዘላቂ እርቅና መፍትሄ መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሰሚ አላገኘንም እንጂ ጠቁመን ነበር። የተቃዋሚዎች ጥያቄ መልስ ካገኘ ማሰባሰቡና በጦርነቱ ማሳተፉ (mobilize ማድረጉ) ቀላል ነው። እውነተኛ አንድነትና መሰባሰብ ከልብና ከሀገር ፍቅር ስሜት የሚመነጭ ነው፤ እውነተኛ ውክልና ለፕሮፓጋንዳ ግብ ብቻ ሲባል በሸርና በውሸት የተቀመረ አይደለም። ዘላቂ (Durable) ነው። ተወክሎ ኢትዮጵያ መሄድና ሳይወከሉ ኢትዮጵያ መሄድ የዲክቴተርነትንና የዴሞክራሲያዊ ውክልናን ያህል በሌላም መልኩ እንደሚዳና ገደል የተለያየ ነው። ይህንን በዚህ ልተወውና በእኛ በተቃዋሚዎች ላይ ያለውን ድክመትም አንዳንድ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ሀሳቤን ለመግለፅ ፍቀድልኝ።

እኛ ተቃዋሚዎች በወቅቱ ያሉን ዓላማዎችና ፕሮግራሞች አንድ ናቸው። የልዩ ልዩ ፓርቲዎችና መድረኮች ውሳኔዎች በአንድ ሰው የተፃፉ ይመስላሉ። ሁሉም ለሀገሩ ይንገበገባል፤ ይቃጠላል። በተግባር ግን አንድ ላይ መጥተን የሚያመረቃ ሥራ መስራት አልቻልንም። በዚህ ውስብስብ የፖለቲካ መረብ የገነባነውን የስብስብ መድረክ (Concensus Forum) በግለሰብና በድርጅት ፉክክር የተነሳ መልሰን እንበጣጥሰዋለን። ባለፉት 7 ዓመታት በተካሄደው ፀረ ወያኔ ትግል በምዕራቡ ዓለም የመሸገው ተቃዋሚ የሌላውን የአፍሪካ ትግል በሚያስከነዳ ሁኔታ ጠንካራ የስብስብ መድረክን (concensus) መስርቷል። በሀሳብና በርዕዮተ ዓለም አቀራርቧል። ነገር ግን እርስ በርስ ስለሚጐናተል በተግባር ሽባ ሆኗል። በኢትዮጵያ ታሪክ ምሁሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በተደራጀ መልክ በኃይል ሳይሆን በአእምሮና በጽሁፍ ያጋለጠው የወያኔን መንግሥት ነው። የምዕራቡ ጫናና ማናናቅ (pressure and redicule) ሳይበግረው የዘርን ፖለቲካ አራማጆች ክስረት ለዓለም የህዝቦች አስተያየት ችሎት (World Public Opinion) አቅርቦ አስኮንኗቸዋል። ምሑሩ ይህንን ሲያደርግ እጅግ እያመመውና እየተሰቃየ ነው።

ወዳጄ ሆይ!

አንዱ ጥሩ ሲያደርግ ሌላው ይቀናል፤ አንዱ ድርጅት ራመድ ሲል ሌላው ጠልፎ ለመጣል ይራወጣል። አንዱ አዲስና የሚሰራ ነገር ይዞ ሲመጣ የሌላኛውም ወኔ "ከማን አንሼ" ይሆንና የካርቦን ኮፒ ነገር ይዞ ይመጣና ሰሚውን ግራ ያጋባል። አንድ ወሳኝ ስብሰባ አንዱ ወገን ሲያደርግ በዚያችው ሰሞን ወይም በጥቂት ቀናት ልዩነት ተመሳሳይ ኮምሲዮን ይሰየማል። በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩት አባት ጳጳሳት ህዝቡንና ምዕመናኑን በኢትዮጵያዊነት ሲያጠናክሩ ሌላ ስም ይሰጣቸዋል፤ እነርሱን ለማዳከም ሌላው ቀርቶ ከወያኔ ጋር ከሚሰሩ ከአንድና ሁለት ከማይበልጡ ጥቂት ካህናት ጋር አንዳንድ ምሁራንም በመጠቃቀስ የአፍራሽ ተልዕኮን ሚና ይጫወታሉ። ተደብቆ የሚኖር ነገር ስለሌለ ነገ ታሪክ ያጋልጠዋል። ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን የተደራጀን በጐ አድራጊና ለሀገርም ቅን አሳቢ ድርጅት በገንዘብና በጊዜ ከመርዳት ይልቅ ይበልጡን ለማፍረስ ስንረባረብ እንታያለን። ይህንን ደግሞ ካልተረዳን ግለሰባዊና ድርጅታዊ ተሃድሶ ማድረግ ይከብደናል። ጠላት ላይ ጣታችንን ከመቀሰራችን በፊት ራሳችንን በጥሞና መመርመር ይኖርብናል። እዚህ ላይ ለማስረገጥ የምፈልገው እኛም ዘንድ ያለው ችግር ወያኔም ዘንድ አለ። ደርግም ውስጥ ነበር። በኃይለሥላሴም ዘመን ይታይ ነበር። እነርሱ ግን ለዓመታት የገዙት ኃይል ስላላቸው ብቻ ነበር። ከተቃዋሚ ድርጅቶች በተለየ መንገድ ሀሳባቸው ተቀባይነትን በሚያገኝበት ወቅት ከውይይት ይልቅ መፍትሄያቸው ጠበንጃና ሥቃይ (torture) ስለነበር ነው። በኢትዮጵያውያን መካከል ውይይት በጥሬ ቃሉ መማማርን የሚያሳይ ሳይሆን ተለውጦ መጣላትን ነው የሚያስተጋባው። ስለሆነም እጅ በማውጣት የሚመረጥ ስብስብ ሁሉ ከድሉ ይልቅ አውዳሚነቱና አጥፊነቱ የበረታ ነው። ሆኖም ግን ይህ ድርጅት የግል (private) ቢሆን ለመጠናወት ማንም አይሞክረውም። በግለሰቦች ጥረት በግል የተቋቋመን ለምሳሌ እንደ የሀገር ወዳዶች ስልተ-መርህ (Tink Tank) ከማፍረስ ወይም ከመጠናወት በምርጫ የተቋቋመን የሃገር ወዳጆች ስብስብ መናድ ይቀላል። በግል የተቋቋሙ አብያተ ክርስትያናትን ከመበታተን እጅ በማውጣት የተመረጠውን አመራር መፈረካከስ ጊዜና ጉልበት አይወስድም። በአሜሪካ ለምሳሌ ብዙ ሚሊዮን የሙያና የህዝብ ስብስቦች አሉ። ብዙዎቹ በርካታ ዘመናት የቆዩ ናቸው። ለነገውም ትውልድ ቀጣይ ናቸው። ባህሪያቸው በግልና በህጋዊ መንገዶች ስለተደነገገ ማንም አይፈነጭባቸውም። በኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ግን ይህ ሁኔታ የለም።

ወንድሜ ወርቃየሁ፤

የኛ ድርጅቶች ግን ደካማውንም፤ ጠንካራውንም፤ አፍራሹንም፤ ምቀኛውንም በአንድ ላይ ስለያዙ ጠላትም ሰርጎ ለመግባት ቀላል ስለሚሆንለት የእኛም ታሪካዊ ሳይኮሎጂ በማዳከሙ ላይ ሚና ስለሚጫወት ከሌሎቹ የምዕራቡ ተቋሞች (Institutions) በተለየ መንገድ በቀላሉ ለአደጋ ይጋለጣሉ። ስለሆነም ትግላችን የእኛን ጠንካራ ሀገር ወዳድነት ራስን ከመመርመር ጋር አጣምሮ መልካሙን ብቻ መርጦ

ከምዕራቡ ዴሞክራሲ ጋር ማዋሃድ አለበት። በድምፅ ብልጫ ብቻ በየስብሰባው ውሳኔ በመወሰን እናት ኢትዮጵያን ከዘረኞች አላቅቃለሁ ማለት የዋህነት ነው። በአሜሪካም ቢሆን የድምፅ ብልጫና ህዝባዊ ተሳትፎ ልክ ቃሉ እንደሚያመለክተው አይደለም በሥራ የተተረጐመውና ይህ ዓለም የሚቀናበትን ሥልጣኔ ያመጣው። ያማ ቢሆን ሥልጣን በንዑሳን ኃይለኞች ሳይሆን በበርካታ የአብላጫ የህዝብ ስብስብ እጅ ትገባ ነበር። ዴሞክራሲን የምናውቃት ጌቶቻችን እንደነገሩን ነው። እነርሱ ዘንድ ለምን ነፍስ እንደምትዘራ ነገር ግን እኛ ዘንድ ስትመጣ ለምን ሞት እንደምትሆን አልተረዳንም። ዴሞክራሱ ራሱ የሸርሙጣ ፖለቲካ ነው። (ለአፀያፊው ቃል ይቅርታ!)። ዴሞክራሲ ማለት ሐቅ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል ሶቅራጥስ ወይም ኢየሱስ የሞተው ለእውነት እንጂ ለዴሞክራሲ አይደለም። በአሜሪካ ዴሞክራሲ ለቤት አጡና በረንዳ አዳሪው ቤት አይሆነውም፤ ለረሀብተኛው ዳቦ አይገዛም። ዴሞክራሲ ለነኢዲአሚን፣ ዩጋንዳ፣ ለነሞቦቱ ዛየር ህዝባዊ አልነበረችም። ዴሞክራሲ ለነመለስ ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔር ሳትሆን የብሔር ልዩነትና ቅራኔ የሚንፀባረቅበት ሀገር ናት። ዴሞክራሲ ከሚያጐናፅፈው መብት መካከል መንግሥትን መመርመርና ማረም ወይም መታገል እንጂ መሰደብን አይጨምርም። አንድ የእሪበከንቱ ወጣት የአሜሪካንን መንግሥት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ፣ (እናቱንም ሳይቀር ቢሳደብ) የኮሌጅ ዲግሪ ያገኛልን?

ለአንዳንዶቻችን ዴሞክራሲ የፊቸል ድለቃ (Gangster rapp) ሊመስለን ይችላል። ዎል እስትሪት (Wall street) እና የኒውዮርክ ዘመን (New York Times) ዴሞክራሲን የሚያዩት በተለየ መንገድ ነው። መለስ ዜናዊም "ዴሞክራሲ" ሲል ይህንን ዴሞክራሲ የሚተነትነው ከራሱ የዘር ፖለቲካ አንፃር ነው። ተቃዋሚ ኃይሉም ዴሞክራሲን አወናብዶናል፤ ከእኛ ታሪካዊ ባህል ጋር ተደባልቆ ራሳችንን መልሶ እያቃጠለን ነው። በነፃነት ቀናዒነት የታወቀው ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ጥያቄ በመንግሥት፣ በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ አወናብዶታል። ይህ ከራሱ ባህል ጋር ያልተዛመደ አዲስ መጤ አስተዳደር ላለፉት አርባ ዓመታት ደመነፍሱን ገዝግዞታል። ሆኖም ምቀኝነትና ቅናት በማንም ህዝብ ላይ የሚታዩ ሰይጣናዊ ጠባይ ቢሆኑም በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ አይለው እንደሚታዩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ይናገራሉ። በቤተክህነት በዜመኛ ቀዳሽ ላይ መመቅኘት፣ በዘመነ መሳፍንት ጊዜና በኋላ በተከሰቱት ታሪካዊ ሁኔታዎች እርስ በርስ የመጠፋፋት ባህል ማደግ፣ በዘር ወይም በጐሳ ውርዴ የተነሳ መነካከስ፣ በረዥም ጊዜ ድህነትና ኋላቀርነት ለጥቂት ሐብት ከፍተኛ የሆነ የርስበርስ ግጭት ማድረግ (Competition for Limited resources)ና የአውሮጳውያን የከፋፍለህ ግዛው ዘይቤና ትምህርት የዴሞክራሲ ባህላችንን አላሳደጉም።

ስለሆነም ትግል በምናደርግበት ወቅት ከጐታች ባህሎችና አስተሳሰቦች ራሳችንን ማንፃት አለብን። አንድ ምሳሌ ልጥቀስልህ። አሜሪካ በርካታ ሀገራቸውን የሚወዱ ምርጥ ምሁራን ዶክተሮች አሉ። በአንድ ስቴት ብቻ በማዕከላዊ ቁጥር (average) 18 ይገኛሉ። ከነዚሁ በአንዱ ስቴት አንድ ከፋፋይ ተንኮለኛ አራቱን ይገናኛል። በስደት በምትገኘው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥላቻ ስላለውና ግለሰቡም በስራው ስለተገለለ ለነዚሁ ምሁራን እየደወለ የጳጳሳቱን ስም ያጠፋል። እነዚህም ዶክተሮች ምርምር አድርገው እውነቱን ከመረዳት ወደ 40 የሚጠጉ አብያተ ክርስትያናት የሚመሩትን ፓትርያርክ ባለመገናኘትና አንድ ወጥ ፕሮፓጋንዳ በመስማት ለዚህም የወያኔ ደጋፊ ሳያውቁት ድጋፍ በመስጠት በጭለማ ሲዳክሩ ይታያሉ። በሚነግራቸው ወሬ ሳያውቁት ከጠላት ጋር ተሰለፉ፤ ከፋፋዩን አቅፈው ያዙት። እጅግ አሳዛኝ ሞት ነው። ምሑር ማለት ተመራማሪ፣ ሐቁን በመብራት ፈልጐ የሚያገኝ፣ በዘር ፕሮፓጋንዳ የማይወናበድ አንቂ መብራት ነበር። የሚሰማውን የሚጠይቅና ማስረጃ ፈላጊም ነበር። ይህ ነው እንግዲህ የባህላችን ዝቅጠት! ዘር ቆጥሬ ይኼ ጐንደሬ ወይም ሸዌ ባልኩ ቁጥር ዳኝነቴ የሚዛባ ከሆነ መላምትን (Hypothesis) ለማረጋገጥ በርካታ ግምቶችን ወስጄ የምመራመር እኔ ሳይንቲስቱ የምሳሳት ከሆነ ከኔ ትምህርት የደንባራ እውር ምርኩዝ አይሻልምን? የዚህ ዓይነቱ የቁም ሞት ራስንም ገሎ ሀገራችንንም ይቀብራል።

ውድ ወገኔ! ፈውስ ያላገኘ በሽተኛ ከህመሙ አይፈወስም። በርግጥም የምዕራቡ ዓለም በኑሮና በጊዜ ጥበት አስቸጋሪ በመሆን በነበረን ሳይኮሎጂ ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ እርስ በርስ ለመበላላትና ለመላላጥ ምክንያት ቢሆንም ትልቁ የትግላችን ጠርና እንቅፋት እኛው ራሳችን ነን። ትግላችን በመልካም ሁኔታ ግብ የሚመታው ግለሰባዊ ተሃድሶ (attonment) ስናደርግና የራሳችንንም ህሊና ስንመረምር (soul searching) ነው። ይህን ተሃድሶ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ ማድረግ አለበት። ተራ ግለሰብም ቢሆን በድርጅቶችና በአመራር ላይ እያማኻኘ ከደሙ ንፁህ ነኝ ማለቱን ማቆም አለበት። ካለብዙኃኑ ድጋፍ ድርጅቶችም ሆኑ መንግሥት ምንም ሊያደርግ አይችልም። አምስት ሳንቲም ያላዋጣ ሁሉ ድርጅቶችን ሲሳደብ ይሰማል። የርሱን ድክመት ግን በፍፁም አያየውም።

ወርቃየሁ! አንዳንዴ ብዙኃኑም ቀጣፊ ነው። ግለሰብ ያደረገውን ስህተት ብዙኃንም ያደርገዋል። ኢየሱስ እንዲወገር ያደረገው ብዙኃኑም ጭምር ነው። ሒትለር 6 ሚሊዮን አይሁዶችን በጋዝ ምድጃና (oven) በሥይል (torture) ሲፈጅ ይደግፈው የነበረው ብዙኃን ነው። ብዙኃን ማለት የግለሰብ ክምችት ነው። ጆርጅ ዋላስ በ1960ዎቹ ዓመታት ጥቁሮች ማግለልን አስመልክቶ "ልዩነት አሁን፣ ልዩነት ለዘለዓለም" ሲል የደቡብ የአሜሪካ ነጭ ህዝብና ክርስትያን ነጮች ደግፈውት ነበር። መለስ ዜናዊንም በአጠቃላይ መልኩ የጐሳ የክልል ፖሊሲውን በማራመድ ምኒሊክ ቤተመንግስት ሲገባ 100% የትግራይ ህዝብ ደግፎት ነበር። ስለሆነም በአሜሪካ የሚገኘው ብዙኃን ኢትዮጵያዊ ራሱን ነፃ አድርጐ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ብቻ ሊወቅስ አይችልም። ይኸስም ይብዛም ለድክመታችን እርሱም አስተዋፅዖ አድርጓል። እንዲያውም በየስብሰባው የሚለመነው፣ የሚረብሸውና የሚያንገራግረው የብዙኃኑ ክፍል ነው። ንቃልኝ ተብሎ ደጅ የሚጠናው ይኸው ክፍል ነው። የጠላት የስለላ ድርጅት ተቃዋሚ ኃይሎችን ለመቦደስ የሚራመድበት ድልድይ ብዙኃን ነው። በየስብሰባው በጊዜ እንዲገኝና የቁጥሩ ድጋፍ እንዳይቀር የሚወተወተው ይህ ክፍል ነው። መጽሔቶችን እንዲገዛ፣

ቤተክርስቲያን እንዲመጣ፣ በራሪ ወረቀቶችን እንዲያነብ የሚጠየቀው ብዙኃኑ ነው። ሁሉም የሚያቆላምጠው ብዙኃኑን ነው። ግን አንዳንዴ ነቅቶ እያለ ያልነቃ ይመስላል፣ ቀሰስተኛ ሆኖ በሰበብ አስባቡ ስብሰባ ላለመገኘት ምክንያት ይደረደራል። አልምጥም ነው። የነማርክስና የነጀፈርሰን ማጅሪቲ ለእኔ ከአብዮ ታዊነቱ ይልቅ ሁኔታዎች እንዳይናጉ ማዕከላዊ ሚዛኑን የሚጠብቅ ካስፈለገም ሃቅ ይዞን የተነሳ ተሸናፊን ከአሸናፊ ጋር ሆኖ አብሮ የሚደቁስ ዘመነኛ ነው። ከባለጊዜ ጋር ይዶልታል፣ ቀን በጨለመ ቁጥር አድማ የሚመታው እርሱ ነው። በሞቡ፡ የድል ዋዜማ ፓትሪስ ሉሙምባን ያወገዘው እርሱ ነው። አየንዴን በዚያች ክፉ ሌሊት ቤቱን ከቦ አብሮ ለፍትህ ከመሞት በፋሽሽቱ አውጊስቲኖ ፒኖሼ ያስበላው ብዙኃን ነው። ብዙኃን መንግስት መደገፍ ከቻለ ግለሰብንም መደገፍ ይችላል። ይህ የብዙኃንና የድርጅቶች ኃላፊነት በርካታ ንትርኮችን ሊያስነሳ ይችላል። የሰለቸው የትጥቅ ነገር ሊነሳ ይችላል። መንግስት ስለታጠቀ በአፈሙዝ ኃይል ብዙኃኑን ማንበርከክ ስለሚችል ብዙኃኑ ጉልበት የለውም ይባላል። እንግዲያው የብዙኃን ታሪክ ሰሪነቱ የቱ ላይ እንደሆነ አይገባኝም። አንዱ ምናልባት የማርክስን ዳዊት (Des Capital) እና የምዕራቡንም መፃህፍት እንዳላነበብኩ አድርጉ ለዚህ ደብዳቤዬ መድፍነ–ፀር ሊጥፍ ይችላል። ሁሉንም አይቼዋለሁ። የምፅፈው ግን ካየሁት ተመክሮና ከኔ ልምድ ተነስቼ ነው። ህዝብ የኃጢአተኛውም የፃድቁም ክምችት ነው። እንዲያውም በክምችቱ ኃጢአተኛው ይበዛል። ስለሆነም ድርጅቶችም በመጠኑም ቢሆን የብዙኃን ስብስቦች ናቸው። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ትግል ሁሉም በክፉም ሆነ በደጉ አስተዋፅኦ አላቸው። ይህን ሁኔታ በተመለከተ አንድ ጣሊያናዊ ፈላስፋ እንዲህ ይላል፡ “አንዲት የዝናብ ጠብታ ስለጉርፉ መጥለቅለቅ ኃላፊነት የለብኝም ልትል አትችልም፣ ጉርፉ የብዙ የዝናብ ጠብታዎች ክምችትና ውጤት ነውና”። እነሆ ትንሽ ግጥም፡–

## የህሊና በረኪና ተሐድሶን
## እንደበረዶ ያነጣል!

ታዲያ ማን ሊሞርደን ዘመዴ
ማን ሊወቅሰን በሙት አጥንት
ወንድም ጋሼ የኔ ጉራዴ
ማንስ ሊገስፀን በእውነት
ስማ የኔ ሸበላ፥ አባ መላ የልብ ጓዴ
ያባቴ ህንፃ መሰረት
የእውቀት እርሻ ሁዳዴ።
ሲዘፍኑ እሰማ ነበር በመሰንቆ
ወግ ሲያወጉ በማለዳ
ነጮች ሲያንቁን በሸምቀቆ
ታዲያ ምነው ሆንክብኝ ባዳ፣
ጉምዝዞህ እንደእንቆቆ
መረን ለቀህ ሳትነዳ
እያለከለክ እንደፈቆ
ስሜትህ ሳይሸፍጠኝ ፥ እኔን ሳይከዳ
ሰውነቴ ከህሊናዬ ርቆ
ሁለንተናዬ ሳይሆን ገዳዳ።
እባክህን ድረስልኝ ፥ ፍታውያንን ማነቆ
የደም እምባዬ ሳይቀዳ
ዳግም ፈልቶ ተፍለቅልቆ
እኔነቴን ሳያሰናዳ
የልቤን ጅማት ሰርስሮ ፍቆ።
ምነው ተረስተን በቀረን
በረሳን ያለም ሥልጣኔ
እዚያው ሳይሰማ ድምፃችን
ገርጥተን እንደጠመኔ
ረሃብ እርዛት ረጋግጦን
ድብን አድርጉን የድርቅ ጠኔ።
ስማኝ ብዬ ልጠይቅህ
ዴሞክራሲ የሚሉት ጣጣ
ያርባ ዓመት የቁጣ ዕልህ
የአጣብቂኛቸው ፈንጣጣ
ያልበቀለ ከሀገርህ
እንዴት ደዌ ይዞ ይምጣ?

አንተም ከጥንት ዋግምትህ
ከዚያ የደም መጠጣ
እፈልጋለሁ እንዳይህ
እንድትነፃ – ከምቀኝት ብጥበጣ።
ከራፉን ምታው እየነዘርህ
ርገጠው ያንን ዳንኪራ
ድኝ እንደሆነ ጠምቶህ
ምስህ ይሁን በሥራ
እዶከበሬህ ያንዘፍዝፍህ
አንተ ምሑር ደረቅ ገራራ
በድምፃቸው ይሁንብህ
ለፍትህ ስትል – እባክህን ተገራ።
ስማኝ ግዴለም ጋሼ
ተሃድሶ ምጡቅ ነው
የማይጠራ በሞክሼ
ረቂቅ መንታ የሌለው
የኔ የምለው ታጋሼ
ህሊናዬን የሚቧጥጠው
ሰማኝ ግዴለም ጋሼ
ዓለም ሁሉ ኃላፊ ነው።
ባረመምን ቁጥር ተናንቆን
ማንቁርታችንን የሚያብተው
ሲለው ኦክሲጅን ነፍጉን
ሥራችንን የሚያፍነው
ታሪክ ይመዝገብልን
ይኸው ምቀኝነታችን ነው።
ይህን ካላደረግን ግን
ካልዘመትን በኛ በተለይ
በጀግንነት ካልተቃቀስን
ይቅምም የኛ ስቃይ
አይቆምም ልቅሶና ብካይ።
ሆኖም ተስፋ ’ሚሰጥን
የመተራረማችን ሲሳይ
መፍትሔ ለውድቀታችን
ለተጠናወተን ሁሉ ሥራይ
እናጠፋለን መጠራጠርን
ጠራርገን ከህሊናችን ላይ
መጪው እንዲበራልን
እንዲፈካልን እንደፍኩይ።
====== // =======

ቸር ይግጠመን
ገብርዬ (አትላንታ፣ ጆርጂያ)

# ደብዳቤዎቻችሁ




## አሁንስ በዛ!! ደግሞ ወዴት ወዴት?

ይህ የስደት ኑሮ ብዙ አስተምሮናል፤ ብዙ አሳይቶናል። ለአገራችን ነፃነትን፤ ብልፅግናን ለወገናችን እኩልነትን ዕድገትን እንመኛለን፤ ለዚህም እንታገላለን የምንል ሁሉ የምናልመው ግብ አንድ ሆኖ ምን እንደሚያነታርከን፤ ለምን እንደምንጣላ ሁሌ ይገርመኛል። መግባባት ባለመቻላችን ለአገር አንድነት እናስባለን የምንል ተበጣጥቀንና ተከፋፍለን እንታያለን። ይህንን በመመልከት መስመር ያሲዙናል የምንላቸው ምሁራኖቻችንም ቢሆኑ ለችግሩ መፍትሔ በመሆን ፋንታ እነሱ ራሳቸው ችግር ፈጣሪዎች እየሆኑ መምጣታቸው የአደባባይ ምስጢር እየሆነ ነው። መለስ ብለን ካለፉት ስድስትና ሰባት ዓመታት ጀምሮ በውጪ በተለይ በአሜሪካ ያለውን የኢትዮጵያውያንን ትግል የተመለከተ እንደኔው የታዘበው አንድ ነገር ይኖራል ብዬ ገምታለሁ። በትግሉ አካባቢ ይታወቃሉ የሚባሉ አንቱ የተባሉ አንዳንድ ምሁራንን ዝም ብላችሁ እንቅስቃሴአቸውንና ድርጊታቸውን ብትከታተሉ የምላችሁን ትረዳላችሁ። የሚተዋወቁ የተወሰኑ ምሁራን ይሰባሰቡና አንድ ስብስብ በመፍጠር ድርጅት ብጤ ይፈጥራሉ። ተከታዮችም ያበጃሉ። ትንሽ ይቆዩና እርስ በርሳቸው ይጣሉና (ምን እንደሚያጣላቸው ሁሌ ይገርመኛል) በመለያየት አንድ የነበረው ድርጅት ሁለት ሆኖ ተከታዮችም የእነ እከሌ ___ የእነእከሌ በመባባል ይከፋፈልና መበላላት ይጀምራል። ከአንድ አምስት ዓመት በፊት ጀምሮ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ እናደርጋለን በሚል መጀመሪያ ከተቋቋመው ኮሚቴ ጀምሮ ስንት ኮሚቴ እየተከፋፈለ እንደተቋቋመና በዚያው መጠን ስንት መሰበጣጠር እንደተፈጠረ ዓይኑን አውቆ የጨፈነ ካልሆነ በስተቀር ይህን መገንዘብ አያቅተውም። ስማቸውን ብጠቅስ ደስ የሚለኝ (ግን ለጊዜው ልተወው) ጥቂት እጅግ ጥቂት ምሁራን የሚገቡበት ቦታ ሁሉ ብጥብጥና ጭቅጭቅ አያጣውም። እነሱ የሚፈልጉት ነገር ካልሆነ መበጥበጥ፤ ንቀት ማሳየት አወቂነት ለነሱ ብቻ እንደተፈጠረ በመቁጠር የሌላውን ሃሳብ ማንኳሰስና ማቅለል ነው ተግባራቸው። ይህን ስል ብዙ መረጃዎችን ይዤ ነው። አንድ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ደህና ተካሄደ ሲባል የሚገቡበት ቀዳዳ አያጡም፤ ይገቡና ትርምስምሱን ያወጡታል። እንደኔው ይህን ሁሉ ጊዜ ጠብቆ ለማጋለጥ የተዘጋጀ ሊኖር ይችላል። እኔ ግን አላስችል ስላለኝ መድረኩን ላንዳፍታ ከፈቀደችልኝ ልተንፍሰው። እነኚህ የምላቸው ጥቂት ምሁራን ለአገር አንድነት የተሰባሰቡትንና መሰባሰብ የሚፈልጉትን ሁሉ አበጣብጠው ጨርሰው አሁን የቀራቸውን በቤተክርስቲያን አካባቢ የተሰባሰበውን ሕዝብ መከፋፈል ጀምረዋል። እዚያ አካባቢ የጀመሩትን ልብ ብላችሁ ያጤናችሁ ካላችሁ እነኚህ በጥባጮች ዓላማቸው ምን እንደሆነ ግራ ያጋባል።

1ኛ. በኢንተርኔትና በአንድ መጽሔት በአሁኑ ጊዜ በስደት ያሉትን ሕጋዊውን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዮስን መነካካት ጀምረዋል። ቅዱስነታቸው በስደት አገር ከለቀቁ ቆይቶ ሳለ አሜሪካ ሲገቡ ጀምሮ በሆነው ባልሆነው ስለቅዱስነታቸው ያልተገባ ሐሰት የተመላበት ወሬ ለማሠራጨት የተነሱትን በጣም ጥቂት ምሁራን ማጋለጥና ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግ ያስፈልጋል። እነሱ ደግም ሌላ ፓትርያርክ ሊሾሙልን እንደሆነ አልገባንም።

2ኛ. በስደት እንዲሁ አገራቸውን ለቀው በባዕድ አገር የሚንከራተቱትን አባት ጳጳሳትና አበው መነኮሳትን ለመከፋፈልና ለሚፈልጉት ግትር ዓላማ መሣሪያ ለማድረግ ሲዳክሩ ይታያሉ። ባለፈው የኢትዮጵያ ሬጂስተር መጽሔት ላይ "በሕግ አምላክ ጳጳሳት" በሚል ርዕስ በዘገባው ክፍል የቀረበውን ጽሑፍ የተመለከተ ሁሉ ምን ያህል እንደሚያዝን ግልፅ ነው። ከሁሉ የሚያሳዝነው አባቶችን በጎጥ ለመከፋፈል ዘጋቢው የተጠቀሙበት ኃይለ ቃል ነው። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አባ ጳውሉስን እንጀት ለማራስ ካልሆነ በስተቀር ምን ጥቅም ሊሰጥ እንደሚችል ሊገባኝ አልቻለም።

በመጨረሻ የምለው ነገር ይኖረኛል። 1ኛ. እስቲ ይህንን ነገር አጣሩና ሁኔታውን አሳውቁን 2ኛ ደግሞ እነኚህን ሰዎች "እባካችሁ ቤተክርስቲያኒቷን ተዉዋት! የእምነት ቦታ እንጅ የናንተ እንካ ሰላንትያ ቦታ አይደለችም" የሚል መልዕክት አስተላልፉልን። ሌላው ትልቁ ነገር "እባካችሁ በዚህ ትልቅ ዕድሜያቸው አገራቸውን ትተው በስደት ያሉትን ሽማግሌ አባቶቻችንን ፓትርያርኩንና ጳጳሳቱን እዘኑላቸው፤ ምን አድርጉ ነው የምትሉዋቸው? ሃይማኖትና እምነት ይግዛችሁ። አባትን አክብር የሚለውን ትዕዛዝ አትርሱ" በሉልን። እስቲ ስንት ማተኮር የሚገባ ብዙ ነገር እያለ በሰላም እተካሄ ያለውን ማበጣበጥ ይገባል፤ ኧረ እግዜርን ፍሩት!

ማሩ ለገሠ ነኝ (አርሊንግተን)

## "ኧረ እነሱው በሕግ አምላክ!!"

ውድ ላንዳፍታዎች

ሥራችሁ ማንነታችሁን እያሳወቀ ስላለ ስለምታበረክቱት አስተዋጽዖ በርቱበት ብቻ ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር ይስጣችሁ እላለሁ። በዚህ አጋጣሚ ለማንሳት የምወደው ነገር አለ። ተማረ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከማስተማርና ከማደራጀት ይልቅ ማደናገር ይቀናዋል ልበል። ሁሉንም በጥምል እንዳላልኩ ተረዱልኝ። ብዙ ሸጋ ሸጋ ተግባር

የሚያከናውኑትን ያህል ከኛ በላይ የተማረና ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላሣር ነው በማለት ሁሉንም የተቃዋሚ ተቋሞች ለመቆጣጠር በየጊዜው ችግር የሚፈጥሩ አተካራቸው የወያኔን ፕሮፓጋንዳ የሚያራምድና የተራቀቁና የታገሉ የሚመስላቸው የድንጋይ ዘመን የመጠፋፋት ፖሊሲን የሚነድፉ አንዳንድ ምሑራን በአሜሪካ ምድር አሉ።

መማር ማለት የሕዝብን የመግባባት ባህል አሳድጎና አገናኝቶ ለአንድ ጠቃሚ ዓላማ እንዲታገል ማድረግ ነው፤ መማር ማለት ሕዝባችን ሚዛናዊ አስተሳሰብን እንዲከተልና የጋራ መድረክ እንዲፈጥር ሳያሰልሱ መቀስቀስ ነው፤ መማር ማለት ጥሩ ዜጋ፤ ሞራላዊና ግብረገባዊ ባሕርይ ያለው ነዋሪ ማፍራት ማለት ነው። መማር ተመራምሮ ጎጂ ባህሎችንና ኋላ ቀርነትን የሚያጠፋ መድሐኒት ነው። ከኛ ምሁራን መሐል አንዳንዶቹ በተለይ ዶክተር የሚል ተቀጽላ ያላቸው ታዋቂ ናቸው የሚባሉት አሁንስ አበዙት። የወጣቱን ትግል ያጥላሉ፤ የጥንቱን የተማሪዎች ትግል ሲያንኳስሱት ይደመጣሉ፤ አንድ ድርጅት ብቅ ሲል ለእነርሱ የማይገዛ ከመሰላቸው በኢንተርኔትና በየመጽሔቱ አደናግረው ያጠፉታል። ትንሽ የሚቋቋማቸው ብቅ ካለ የገፀ ባህሪይ ግድያ (CHARACTER ASSASINATION) ያካሂዱበታል። በዶክተርነታቸው ታማኒነትን ስለሚያተርፉ ያሳድሙበታል። በንትርካቸው ስንቱን ከትግል ሜዳ አሸሹት፤ ስንቱ ማህበር፤ ስንቱ ድርጅት በነሱ ንትርክ ሳቢያ ፈረሰ። በዚሁ ንትርክ በብዙ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ የተመሠረተውን ኢትዮጵያ አገራዊ ጉባኤን (ኢሀጉ)ን የንትርክና የጭቅጭቅ መድረክ በማድረግ በብዙሃን ድምጽ የተመረጡትን ተመራጮች አላሠራ አሉ። የተመራጭነት መብት የሌላቸው አንዳንድ ምሁራን በሕዝብ የተመረጡትን ሹማምንት ለመሻር እስከመቃጣት የሞከሩም ነበሩ። የፓሪሱን የተቃዋሚዎች ስብሰብ ተቃወሙ። ሁሉንም ተቃወሙ፤እንግዲህ ለነሱ የሚበጅ ምን ይምጣ?

ይህ አልበቃ ብሉአቸው አሁን ደግሞ በስደት ወዳለችው የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዞር ብለዋል። ቤተክርስቲያኗ በአባቶችና በምዕመናን ጥረት እያደገች በግፍ የተባረሩትን ቅዱስ ፓትርያርኩን ይዛ እያደገች ባለችት ወቅት በእነርሱ መዳፍ ያልተንበረከኩትን አባት ጳጳሳትና ካህናት አንገት ለማስደፋት (INTIMIDATE ለማድረግ) መሳደብና ስም ማጥፋት ጀመሩ። ጳጳሳቱን ለመከፋፈል ለረዥም ጊዜ ሲያደርጉት የነበረው ተንኮል እየተጋለጠ መጥቷል። ይህ ያደረጉት ተንኮል በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ ይዞ በተደጋጋሚ እንደሚገለፅና ስማቸውም ይፋ እንደሚወጣ ጥርጥር የለኝም፤ ስንት ታሪክ ዘጋቢ እንዳለ መዘንጋት አያሻም። እነኝህ በስደት ያሉትን ጳጳሳት በመከፋፈል በወያኔ መንግሥት የተሾሙት አባ ጳውሉስ አንጀት ለማራስ ነው ይህ ሁሉ? በአሁኑ ጊዜ ከፖለቲካ ድርጅቶች ይልቅ በስብስብ የተጠናከረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አካባቢ ያለው ኢትዮጵያዊ ነው። ይህ ኃይል በእምነቱና በአገር አፍቃሪነቱ የበረታ በመሆኑ ወያኔንና ከፋፋዮችን ክፉኛ አስደንግጧል። ይህ ኃይል ለተሸመደመደ ዓላማ በቀላሉ የሚገዛ ክፍል ስላይደለ ደካማ ለሆነው ለዚህ ምሁር ክፍል በቀላሉ የሚበገር አልሆነም። ስለዚህ ወይ የአባቶችን ስም በማጥፋት ወይም አባቶችን በመከፋፈል "ይኸው አባቶች የምትሉዋቸው የሚሠሩትን" በማለት ሕዝቡን ለመከፋፈል በመሞከር ላይ መሆናቸውን በቅርቡና ቀደም ሲልም "ኢትዮጵያ ሬጂስተር" በተሰኘው መጽሔት ላይ የወጡት ቤተክርስቲያኒቷን የሚነኩ ጽሑፎችን ለመረጃነት መመልከት ይበቃል።

እነኚህ በጣም ጥቂት የሆኑና ተደማጭነት አለን የሚሉ ምሁራን ከሁለትና ከሶስት የማይበልጡ ካህናትን በመጠቀም በየቦታው ያለውን የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ሳሚ ምዕመን ሲያበጣብጡ ይታያሉ። እነኚሁ ካህናትና ምሁራን የቦታው ስልክ በመደወል ምዕመናንን የሚከፋፍል ፕሮፓጋንዳ በድብቅ ሲረጩ ከርመው አሁን በይፋ መጽሔት ላይ መጻፍ ጀምረዋል። እነኚህ በወያኔ የስለላ መረብ በተራቀቀ መንገድ መሣሪያ በመሆን ላይ ያሉት ጥቂት ምሁራንና የሚጠቀሙባቸው ከሁለት የማይበልጡ ካህናት ቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዓን ጳጳሳት የአንድ አካባቢ ብቻ ናቸው በማለት ሁኔታውን ሌላ አመለካከት ለመስጠት ይሞክራሉ።

በNOVEMBER 98 የኢትዮጵያ ሬጂስተር መጽሔት ገፅ 41 ላይ "...ከጳጳሳቱ ጋር በግል በመተዋወቅና የጎጥ ልጅ በመሆን በማህበሩ ስብሰባ ላይ በማደም ከሆነ አባ ጳውሎስንና ሺሚዎቻቸውን ወያኔዎችን ጥፋተኛ የሚያደርግ ሳይገድ አይቀርም።" በማለት ከአንድ አባት ምሁር የማይጠበቅ አሽሙር የተመላበት መርዝ በዘጋቢው ተጽፎ ሲታይ አቅጣጫው ወዴት እንደሚያመራ መገመት አያዳግትም። ምን ለማለት እንደፈለጉ ግልፅ ቢሆንም እነኚህ ሕዝብ የሚያተራምሱት የጽሑፉ አዘጋጆች ምሁራንና ተከታዮቻቸው እነሱ ሌላውን የሚከሱበት የጎጥ አመለካከት እንዳሰባሰባቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። እነኚህ ምሁራን አመጣጣቸው ከአንድ ጎጥ ለመሆኑ በቂ መረጃ አለን። ነገሩ "የአብዬን ለእምዬ . . ." መሆኑ ነው። ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው እነኚህ ምሁራንና አቋቋምን የሚሉት ማህበር ያዘጋጀው ስብሰባ ላይ ቅዱስ ፓትርያርኩና ጳጳሳት አልተገኙም የሚል ክስ ሲመሠርቱ ለመሆኑ ሲኖዶሱ የማያውቀው በአባቶች ተሳትፎነት ያልተገነባ ማህበር እንዴትስ ለምንስ ሊቋቋም በቃ፤ ዓላማውስ ምንድነው? የትኞቹን ቤተክርስቲያናት ነው የሚወክሉት? ከሁሉ በላይ የዚህ ማህበር ጉባኤ ውሳኔዎች ናቸው ተብለው በዚሁ መጽሔት ላይ ከገፅ 31 እስከ 34 የተዘረዘሩት ውስጥ ለተለያዩ ሃላፊነት የተመረጡት ዶክተሮች ምንድናቸው? የቤተ ክህነቱ ሰዎች ናቸው? ከሁሉ በጣም ያስገረመኝ ከውሳኔዎቹ ገፅ 33 ላይ የተገለፀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የዓለም ቤተክርስቲያናት ማህበር አባል በመሆኗ በዓመታዊ ጉባኤ ላይ የሚገኙት ተብሎ ስማቸው የተጠቀሰው ፕሮፌሰር በማን ተወክለው ነው? በስደት ላይ ያሉት ቅዱስ ፓትርያርኩና ጳጳሳት ያሉበት ሲኖዶስ ሳያውቃቸው እኚህ ፕሮፌሰር እንዴት ሊወክሉ እንደቻሉና በዚያው ውሳኔ ላይ ለተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች የተመረጡት ዶክተሮች ስናይ ማህበሩ የቤተክርስቲያን መሆኑ ያጠራጥራል። ውሳኔዎቹ በይፋ ሲታዩ ደግሞ የሲኖዶስ ውሳኔዎች ይመስላሉ።

ላንዳፍታዎች፤ ይህንን መልዕክቴን በመጽሔታችሁ ካወጣችሁ በነኚህ ሰዎች አማካይነት የሚደርስባችሁን ስም የማጥፋት ዘመቻ ካሁኑ ገምቱት። ቀደም ሲል በእነኚሁ ሰዎች በአንድ መጽሔት ላይ የተደረገው ሴራና አድማ በኛም ላይ ይደርስብናል ብላችሁ ከፈራችሁ ለናንተ የሚኖረኝ ግምት ዝቅተኛ ይሆናል። አትፍሩ እውነት እያደር ነው የሚጠራው፤ ሐቅን ከያዛችሁ የሚያስፈራችሁ ነገር አይኑር። ስለዚህ አንዳንድ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የሚጎዳ ሁኔታ የሚያስፋፉ ምሁራንን ሳትፈሩ ማጋለጥ አለባችሁ፤ ማስተማርም አለባችሁ።

ጌታቸው ሃብቴ
(ከሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ)

---

## ዝንጀሮ መላጣዋን ብታይ . . .

ጤና ይስጥልኝ ላንዳፍታዎች የመፅሔታችሁ ታዳሚ ነኝ። በፅሁፍ ስሳተፍ ግን ይህ የመጀመርያዬ ነው። እንደሚሆን እንደሚሆን አድርጋችሁ አቅርቡልኝ አደራ።

በላንዳፍታ መፅሄት 7ኛ ዓመት ቁጥር 1 "ደብዳቤዎቻችሁ" ዓምድ ስር አትላንታ ወይስ አትላንታዬ በሚል ርዕስ ኑር ሁሴን የተባሉ ግለሰብ ከዳላስ የጣፉትን የተንደገደገ ፅሁፍ አነበብኩ። እኚህ የተንደገደጉ ሰው በተንደገደገ ፅሁፋቸው የዳላስን ስፖርት ክለብ፣ አስቴር አወቀንና በአትላንታው ስፖርት በዓል የባህል ምሽት ላይ ንግግር ባደረጉ አንድ ኢትዮጵያዊ ላይ ግልብ የሆነ ትችት ለመሰንዘር ሞክረዋል።

ከፅሁፋቸው በመነሳት ራሳቸውን ላሳያቸው እሞክራለሁ። እንደዝንጀሮዋ ...

በመጀመሪያ እርሳቸው እንዳሉት ጆርጅያ ከተማ ለመድረስ ገና የ2 ሰዓት የመኪና መንገድ ሲቀራቸው አትላንታ የሚል የመኪና ሰሌዳ ቁጥርና ትላልቅ ህንፃ በማየታቸው ጆርጂያ ከተማ ይህ ነው በማለት የስፖርት ሜዳውን ለማግኘት ብዙ እንደዳከሩ ገልፀዋል። ለዚህም ስህተት የሰጡት ምክንያት የሆቴል ስምና የስፖርት ሜዳው ስልክ ቁጥር ስላልነበራቸው "በቅንፍ (ስላልተነገረኝ) ነው ብለዋል። ይህ በጣም ጮርቃ ምክንያት ነው። እንዲያውም የሆቴል ስም አለማወቃቸው ጠቀማቸው እንጂ ከዳላስ ወጣ እንዳሉ ተመሳሳይ ሆቴል ዘው ብለው የዳላስ ስፖርት ቡድን አባሎችን ("ግሩፖቼ")ን ውለዱ እንደሚሉ ጥርጥር የለውም። በመጨረሻም በስንት ጠቋሚ ያሉበት አገር ወይም ከተማ ጆርጅያ እንዳልሆነና ወደጆርጂያ የሚወስደው መንገድ ተጠቁሟቸው ከድክረት እንደወጡ ገልፀዋል። የሚገርመው ከአራቱ ጓደኖቻቸው(የሡፈር ልጆች) አንድ እንኳ ካርታ ማንበብ የሚችል አለመኖሩ የሚመርጧቸው ጓደኞች ምን አይነት እንደሆኑ መገመት ይቻላል። ብቻ እርስዎን ለዚህ ሁሉ ድክረት ያበቃዎት ከኔ በላይ ላሳር ፀባይዎ እንጂ የዳላስ ስፖርት ማህበርም ሆነ ሌላ አካል የስፖርት ሜዳ ስም ስልላሰጠዎ ወይም የሜዳ ስም ባለማወቅዎ አይደለም። ትልቁ ችግርዎት አትላንታ የጠቅላይ ግዛት ስም፣ ጆርጂያ የከተማ ስም መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባት ይመስለኛል። ለዚህም ነው ምክንያት ሲሰጡ አትላንታ የሚል ሰሌዳ ሳይ ከተማው ይህ ነው ብዬ የወሰንኩት የሚሉት።

አቶ ኑር ሁሴን ቀጥለው የተቹት በአንድ ስብሰባ ላይ ለብዙ ዓመታት ውጭ ስለቆየሁ አማርኛ ያጥረኛል በማለት ራሳቸውን አስተዋውቀው መድረክ ላይ ንግግር ሲጀምሩ አማርኛና እንግሊዝኛ ቀላቅለው በመናገራቸው በተሰብሳቢው ጪኸት ንግግራቸው በተቋረጠ ሰው ላይ ነው። በመሰረቱ ሰውየው የቋንቋ ችግር እንዳለባቸው አስቀድመው ከተናገሩ በተቻለ መጠን የንግግራቸውን ፍሬ ሀሳብ እንደምንም ለመረዳት መሞከር የጨዋ ወይም የአዋቂነትና የኢትዮጵያም ባህል ነው። እንግሊዝኛና አማርኛ ቀላቀልክ ብሎ መጮህ ግን በእኔ እምነት ስርአተ አልበኝነት ነው። ሰውየው ከናካቴው ደንቆሮ ወይም ድዳ ቢሆኑ እንኳ በአስተርጓሚም ቢሆን ሃሳባቸውን የመግለፅ መብት ያላቸው ይመስለኛል። ሌላው ስለዚሁ ሰው ካሉትና ከተገረምኩበት ... "የሚፅፍልህ ካጣህ ለማለት የፈለግከውን ለእንደኛ ላለው በላንዳፍታ በኩል ጠይቀህ ማፃፍ ይሻላል እንጅ ..." በማለት ራሳቸውን የንግግር ፅሁፍ አርቃቂ አድርገውት እርፍ ይላሉ።

ከየትኛው የቋንቋ ተቋም እንደተመረቁ ባላውቅም የአረፍተ ነገር አስካክም የተከተሉበት የስዋሰው ህግና ከፅሁፍዎ ውስጥ ያሉት የባዕድ ቃላቶችን ከተጠቀሙባቸው አረፈት ነገሮች ጋር ሳዛምድ ብዙ ነገር እጠራጠራለሁ።

ምሁር ኑር ሁሴን ቀላቅሎ መናገር ደግ አይደለም እያሉ እርስዎ ግን የባዕድ ቃላቶችን በብዛት ተጠቅመዋል። አንዳንዶችማ ምን ቃላት ለመተካት እንደተጠቀሙበት ግር ይላል። ለምሳሌ "አክቲቪቲዎች" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ አብዝተው ምን ለመጠቀም እንደፈለጉ ግልፅ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ "ግሩፖቼ፣ ሪዘርቭ፣ ለሲዝኑ፣ ሬስቶራንቶች፣ ጋዝ ቴሽን፣ ለስፖንሰሮቿ፣ ሲቲ፣ ታርጋ፣ ወዘተ" እና የመሳሰሉትን የባዕድ ቃላት ተጠቅመዋል። ታድያ እርስዎ ይህን ሁሉ የባዕድ ቃል በዛች አነስተኛ ደብዳቤ ውስጥ ተጠቅመው በምን መመዘኛ ነው ራስዎን እንደ አማርኛ ቋንቋ ሊቅ ቆጥረው መናገር የፈለከውን ንገረኝና እኔ ልፃፍልህ ብለው ራስዎን የሚክቡ፣ የሚቆልሉና የሚከምሩ።

ራስዎን ቆንጆ፣ ራስዎን ምሁር፣ ራስዎን የሰጠ ባለሚና፣ ራስዎን የፅሁፍ ረቂቅ አውጭ፣ ራስዎን የደካሞች ጠበቃ፣ ራስዎን ምርጥ ስፖርተኛ፣ ራስዎን እንዲህና እንዲያ እያሉ የሚንደገደጉት ከምን ተነስተው ነው?

ኑር ሁሴን አስቴር አወቀንም ይወርፋሉ። በዚህ ጉዳይ እንኳ ብዙዎቻችን ልንነጋገርበት የሚገባ ይመስለኛል። አስቴር በሙዚቃ አፍቃሪዎች ዘንድ ተወዳጅና በጣም ታዋቂ ነች። ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምክንያቱ በውል ሳይጤን ይህችን ብርቅ የኢትዮጵያ ልጅ በተለያዩ ቦታዎች በመጥፎ ሲያነሷት እሰማለሁ። ትልቁ ወንጀሏ አዲስ አበባ ጃንሜዳ የነበሩ ተፈናቃዮችን አስነስታ መዝፈኛ አድርጋዋለች ነው። አስቴር ይህን የመሰለ ወንጀል እንደማትፈፅም ልቦናችን ያውቃል። ከዚህ በፊትም የላንዳፍታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል ቃለ ምልልስ አድርጉላት ስሜቷን ትኩሷቷን ተናግራለች። ሆኖም ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅና ቢናገሩ ይሰማሉ የሚላቸውን ታዋቂ ግለሰቦች በሆነ ባልሆነው

ከሕዝብ ጋር ለማላተም የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። ለዚህ የጥቃት ዒላማ ከተጋለጡት ውስጥ አንዷ የኢትዮጵያ ታላቅ የኪነት ሰው አስቴር አወቀ ነች። አስቴር ኢትዮጵያ በሄደችበት ወቅት በኤምፔሪያል ሆቴል፣ በኢግዚቢሽን ማዕከልና በጃን ሜዳ ለብዙ ሺህ ህዝብ የሙዚቃ ዝግጅቷን አሳይታለች። በዚህ ቆይታዋ ወቅት ወያኔ ኢትዮጵያ በሚል ስም እውቅናን ያገኙና የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠሩ ታዋቂ ግለሰቦችን ደብዛ ማጥፋት ስለሚፈልግ ስለአስቴር አዲስ አበባ መግባት ስለዝግጅቷና ስለማንኛውም የእርሷ እንቅስቃሴ መንግስቱ የሚቆጣጠረው ሬድዮም ሆነ ጋዜጣ አንዲት ቃል አልተነፈሰም። በአንፃሩ መንግስት በተቃዋሚነት የፈረጃቸው ነገር ግን የህዝብ ወገን የሆኑ ነፃ ጋዜጦች ስለአስቴር ብዙ ፅፈዋል፣ ቃለመጠይቅም አድርገውላታል። ይህ መሆኑ እየታወቀ እኛ ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በወያኔ ቦለቲካ ተሸንፈን ምንም ሳናገናዝብ ይህችን ብርቅ የኢትዮጵያ ልጅ ወገን ለማሳጣት የምናደርገው ጥረት መገታት አለበት። አስቴር ምናልባት ከአንዳንድ የፖለቲካ ወይም የጐጥ ድርጅቶች አለመግባባት ፈጥራ ከሆነ በኢትዮጵያዊነቷ መብቷ ነው የፖለቲካ መስመርዋን የመምረጥ መብት አላት። ከኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ጋር እስካልወገነች ድረስ።

አቶ ኑር ሁሴንም በዚህ ቅጥ አምባሩ በጠፋበት ድጋፍ ይሁን ተቃውሞ ለይቶ ባለየለት ፅሁፋቸው አስቴርን ከማዶናና ዊትኒ ጋር ለማወዳደር ይሞክራሉ። ስለማዶናና ዊትኒ የሚጨነቅ ይጨነቅበት፤ እነሱ ለእኛ ምናችንም አይደሉም። አስቴር ግን ለእኛ ለኢትዮጵያውያኖች ማዶናም ሆነች ዊትኒ ሊወዳደሯት የማይችሉ ታላቅ አርቲስታችን ነች።

አቶ ኑር ሁሴን ለሰው ንግግር አርቃለሁ እያሉ እሳቸው ግን አስቴርን ለመተረብ ተራ ፅሁፍን ተጠቅመዋል "እስቶ፣ እስቱ፣ እስቲ፣. .." ይህ የበረንዳ ቋንቋ ነው። ሌላው በጣም የሚገርመው አቶ ኑር አስቴርን እንደራስሽ ሁኚ ይላሉ። ጉድ እኮነው እሳቸው ያልሆኑትን ሆንኩ እያሉ ራሳቸውን ከታላቅ የስነፅሁፍ ሰዎች ጋር፣ ራሳቸውን ከህግ ጠበቆች ጋር ያለምንም ዲፕሎም ወይም የምስክር ወረቀት እየደመሩ አስቴርን ራስሽን ሁኚ ይሏታል። ኧረ ግድየለዎትም አቶ ኑር ሁሴን አይደግደጉ እንደዝንጀሮዋ ምንና ምንዎን ይዩ እላለሁ።

በመጨረሻ ላንዳፍታዎች የምፈልገውን ብያለሁ። ከዚህ በላይ ለመተቸት አቅሙም፣ ችሎታውም የለኝም ብቻ እናንተም ብትሆኑ መፅሔታችሁን እንባቢ እንዳይርቃት ግርድፉን አድቃችሁ፣ ምርቃውን አብስላችሁ፣ የሚንተከተከውን አስከናችሁና ከሽናችሁ ለንባብ ማቅረብ እንደሚኖርባችሁ ይሰማኛል።

ቸር ይግጠመን።

መኮታው ከአርሊንግተን – ቴክሳስ

============ / / ==============

ሰላም ላንዳፍታዎች

እንደምን ሰንብታችኋል?

የዛሬዋ ደብዳቤዬ እንደባለፉት የሰንጠረዣችሁን መልስ አይደለም ይዛ ብቅ ያለችው። ያው እንደምታዩት ትንሽ የምትለው አላት። እናም ቁምነገሯ ጥሟችሁና ሚዛኗ ከብዶ ለህትመት ብታበቋት ደስታዬ ወደር አይኖረውም።

## ጅራፍ ራሱ ተጋርፎ ራሱ ...

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ነኝ ባዩ ወያኔ/ኢህአዴግ ኢትዮጵያን እንዳመቸውና እንዳሻው ማስተዳደር ከጀመረ እነሆ ዓመታትን አስቆጠረ። ታዲያ በነኝህ ለግፍ ተቀባዩ የኢትዮጵያ ህዝብ የመከራ የረሀብና ከምንጊዜውም በበለጠ የስቃይ ዘመናት ውስጥ ወያኔ/ኢህአዴግ ግብሩንና ዓላማውን ለማሳካት ብዙ ጥሯል። ጊዜ ጥሎለትም የተቃዋሚ ኃይሎችን እንቅስቃሴ በኃይልና ኢሰብአዊ በሆኑ ድርጊቶች በማፈን ለመቋቋም በመቻሉ ትውልድና ጊዜ የማይረሷቸው አያሌ ጥፋቶችን ፈፅሟል። በከፋፋይ ፖሊሲውና በጐሳ ዘረኝነቱ ወያኔ/ ኢህአዴግ ለአንድ ብሔር በመወገን የህብረ ብሔረሰብ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያን ለጋና ልንጭጭ በሆነ የርዕዮተ ዓለም ፍልስፍናው አንድ ትውልድ ለማይመልሰው የጐሳ እርስ በርስ ጥልና አደገኛ የመበታተን አደጋ ውስጥ ዘፍቋታል።

ለዚህ እኩይ ዓላማው ማሳኪያ ይሆነው ዘንዳም አያሌ ኢሰብአዊ የሆኑ ድርጊቶችን ፈፅሟል። ህዝብን በማነቃቃት ለዓላማዬ መሰናክል ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ብርቅዬ የሀገሪቱ ምሁራን ከሙያቸው አግሏል፣ አስሯል፣ ገድሏል፣ ሀገሪቱን ለቀው እንዲሰደዱ አድርጓል። ሀቁን መስካሪና እውነታን ለህዝብ አሳዋቂ በመሆንና 'ህዝብ የማወቅ መብት አለው።' በማለት ከልብ የሚጥሩ ጋዜጠኞችንና የእርሱ ዓላማ ደጋፊ ያልሆኑ የፖለቲካ ሰዎችን ወህኒ ቤት በማጎር እስር ቤቶችን አጣቧል። በዚህም የተነሳ ቤተሰቦቻቸው በመንገላተታቸው ለስቃይ ሰለባ እንዲሆኑ ዳርጓል። – እንዲያ እያደረጉ ነው እንጅ ከህዝብ የወጣሁ መንግስት ነኝ ማለት!!

ወያኔ/ኢህአዴግ ያ–ሁሉ አልበቃህ ብሎት ዛሬም በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ለዚያ እንዳሻው ሲረግጠውና ሲበድለው እኔ የምልህን ብቻ ስማ፣ እኔ በምመራህም ብቻ ተከተል ብሎ መብትና ፍላጐቱን ነፍጐት ለኖረው ህዝብ መንስዔውንና ዓላማውን በሚገባ የማያውቀው ጦርነት አምጥቶለታል።

ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት እንዲሉ ዛሬ ወያኔ አቅም ሲያጥረውና ያለ ህዝብ ተሳትፎና ድጋፍ ታግሎ አሸናፊነት የማይገኝ መሆኑን ሲረዳ ያን መከረኛ ህዝብ በአጉል አሉባልታዊ ዲስኩሩና በማያልቅ ፕሮፓጋንዳው ሀገርህ ተወረረ፣ ድንበርህ ተደፈረ፣ ወገንህ ተበደለ፣ ተሰቃየ፣ ተባረረ መሬትህ ተቆረሰ ወዘተ ... በማለት ወደ እንደገና እልቂት ይገፋፋዋል።

ለነገሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ድንበሩ የተደፈረው፣ መሬቱ የተቆረሰው፣ ወገኑ የተሰደደው፣ የተሰቃየው፣ ግፍና በደል የደረሰበት መች ዛሬ ሆነና!!

የኢትዮጵያ ህዝብ የተናቀው፣ የተበደለው፣ የተዋረደው በራሱ በወያኔ/ኢህአዴግ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ድንበሩ የተቆረሰውና የተከፋፈለው በወያኔ/ ኢህአዴግ ያኔ – ከሰባት ዓመታት በፊት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ይረሳዋል ተብሎ ይሆን ዛሬ ጅራፍ ራሱ ተጋርፎ ራሱ ይጮሃል የተሆነው።

በአመፅ በንቅናቄና በለውጥ ወቅት ለሁለቱ ተቃራኒ ወገኖች ከሁሉም በበለጠ ኃይል የሚሰጣቸውና የህዝብ ድጋፍ የሚያጐናፅፋቸው ከሀቀኛ ስራቸው ባሻገር ለህዝቦቻቸው የሚያደርጉት ዲስኩርና ፕሮፓጋንዳ ነው። ነገር ግን ይህ ዲስኩርና ፕሮፓጋንዳ በስልትና

በጥናት ለታዳሚው ህዝብ ካልቀረበ ጉዳቱ ከጥቅሙ በልጠና ለተቃራኒው ቡድን ኃይል በመሆን ከህዝብ ጋር ያራርቃል ይህ ደግሞ ሽንፈትን ያስከትላል።

ታዲያ የዘመናችን የሀገራችን መሪና ብቸኛ በትረ–ስልጣን ሲጨብጥ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ግፍና በደል ተፈፅሞባቸውና ሀብትና ንብረታቸው ተዘርፎ ከኤርትራ ሲባረሩ የድርጊቱ አጋዥ በመሆን ለመላው የዓለም ህብረተሰብ ይህንን የመሰለ ኢሰብአዊ ድርጊት ማሳወቅ ቀርቶ ሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ሁኔታውን እንዳያውቅ ከፍተኛ ጥረት ያደረገው እፍረት አጣሹ ወያኔ/ኢህአዴግ ዛሬ በመቶዎቹ የሚቆጠሩና የእርሱ ዓላማ ደጋፊ የሆኑ የአንድ ብሔር አባሎቹ ከኤርትራ ተባረሩብኝ በማለትና የአዞ እንባውን በመርጨት ለዓለም ህብረተሰብ የአስመሳይና የራስ ወዳድ ፕሮፓጋንዳውን ይነዛል።

ዛሬ ሁለት መንደሮች ተወረሩብኝ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰች ብሎ ስሞታውን ለዓለም ህዝብ የሞኸው ወያኔ/ኢህአዴግ ትናንት በማን አለብኝነቱና ጠያቂ የለብኝም በሚል ትዕቢቱ የጐንደር ለም መሬቶችን በመክለል ለትግራይ ክ/ሀገር በገፀ በረከትነት ሲለግስ ጠያቂ ይሆናሉ ብሎ የፈራውን ክፍል ጥያቄውን እንዳያነሳ አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጥ ችግር በመፍጠር ለጊዜውም ቢሆን አንደበቱን አዘግቶት ነበር። ቅሉ ሐቅ ትመነምናለች እንጅ አትበጠስም እንዲሉ ያ–ብችግርና በስቃይ የተለጐመ አንደበት ሁሌም እንደተዘጋ አይቀርም ብዙ ቆይቶም አንዴ ሲከፈት ጩኸቱ ወሰን ያጣል።

በአሁኑ ወቅት የወያኔ/ኢህአዴግን ውድቀት መቃረቡን የሚያረጋግጠው የሚያደርገው ጠፍቶበት ሁኔታዎችን ከመምራት ይልቅ በሁኔታዎች መመራት መጀመሩ ብቻ ሳይሆን ጠባብና ያላዋቂ አስተሳሰቡ ማለትም መብቱን ነፍጉና ህልውናውን አሳጥቶት እንዳሻው ሲገዛው የነበረው ህዝብ ዛሬ ከገባበት ውጥንቅጥ ችግር ውስጥ ጦርነት ገብቶ ታግሎ ቆስሎ ደምቶና ህይወቱን ሰውቶ ከስልጣኔ ያቆየኛል፣ ከዛም እንደገና እንዳሻኝ አደርገዋለሁ ብሎ በማሰብ አጉል ፕሮፓጋንዳውን መጀመሩ ሞምር ነው። እያ ወያኔ/ኢህአዴግ መቸ ይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግፎት እንደማያውቅ የሚረዳው? ከመቸስ ወዲህ ተበዳይ በዳዩን ሲደግፍ ተስተዋለ? በዳይስ የበደሉን ዋጋ ማግኘቱ አይቀሬ መሆኑን በእጁ ውስጥ ባሉና ራሱ ፈራጅ በሆነባቸው የደርግ ባለስልጣናት ታሪክ ሁኔታው ግልፅ አልሆነለት ይሆን?

አብይ – ከሎስአንጀለስ ካሊፎርኒያ

============ / / ============

ለላፎንቴኖችና . . .

በቅድሚያ ለዝነኛዋ የላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? ከዚሁ ከባህር ማዶ ሁኜ ይህችን ፅሁፌን ስልክላችሁ ለህትመት እንደምታቀርቡልኝ ተማምኜ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው እንደሚታወቀው በዓለም ላይ ከፍተኛ አድናቆት ያተረፉ ሙዚቀኞች እንዳሉና እንደነበሩ እናውቃለን። በሀገራችንም ውስጥ ይህን አድናቆት የተሸለሙ አያሌ ሙዚቀኞች ነበሩ፣ አሁንም አሉ፣ እንዲሁም በመምጣት ላይ ናቸው።

መቸም አገራችን ካፈራቻቸው ዝነኛ አርቲስቶች ውስጥ እከሌና እከሌ ብዬ ለመዘርዘር ቦታና ጊዜውም አይበቃም። አገራችን የራሷ የሆነ የሙዚቃ ዜማ፣ ባህል ወይም እስታይል እንዳላት ቢታወቅም ለምሳሌም ከጥንቱ የአለማየሁ እሸቴ፣ ከጥንቱ የኤፍሬም ዘፈኖች፣ ወዘተ በመነሳት እስከ አዲሱ ዘፈኖቻቸው ያሉትን ብንመለከት የምንሰማው ያንኑ አንድ ባህልና ስታይል፣ ፍፁም ተመሳሳይና መጠነኛ ለውጥ የሌለበት ነው። እዚህ ላይ ለማለት የፈለግኩት የነዚህ ዘፋኞችም ሆነ የሌሎቹ ተወዳጅ አይደለም ማለቴ አይደለም። እንዲያውም የአንዳንዶቹ ዘፈኖች እስከሚቀጥለው ጄኔሬሽን ታዋቂ የሚሆኑ አሉበት። ነገር ግን ሁሌ በአንድ ስታይል መቀጠሉ ለሙዚቃችን እድገት አያስገኝም ለማለት ነው።

ከላይ ወደጀመርኩት ልመለስና በአሁኑ ሰዓት ትኩስ ዘፈኖችን በተከታታይ በማሰማት ላይ ስላሉት ላፎንቴኖች አድናቆትም ትችትም አለኝ። ከአድናቆቴ ልጀምርና በሚያቀርቡት አዘፋፈን ልዩ ፈጠራና ስታይል ስለሚያስደስቱኝ ሳደንቃቸው፤ የተዘፈነን ዘፈን ደግሞ በመዝፈናቸው (አገር ቤት ፍራሽ አዳሽ ነው የሚባሉት እንደነዚህ አይነቶቹ) ቅሬታ ይሰማኛል።

ስለዚህ ውድ አርቲስቶቻችን እስኪ ወደፊት የምታሰሙንን ያን ጣፋጭ ድምፃችሁን ለየት ባለና በተቀየረ መልኩ በመቀላቀል ለማቅረብ ሞክሩ እያልኩ በመጨረሻ ግን ይህንኑ የአገራችንን ዘፈን ወደ ሌላ አዲስ ሌሚል በማሸጋገርና ለወጥ ያሉ ዘፈኖችን በማቅረብ ላይ ላሉት ለንዋይ፣ ለዳዊት(መሳይ)፣ ምንም እንኳ አሁን ድምፁ ለጠፋው አጀማማሯ ላስደሰተኝ ለቻቺና ለታዳጊዋ ጂጂ – ኪፕ አፕ ዘ ጉድ ወርክ እላለሁ።

የናንተው መሐመድ ነኝ – ከቴክሳስ

============ / / ============

ለላንዳፍታ አዘጋጆች፣

እንዴት ናችሁ? እየበረታችሁ ነወይ? ያለፈው እትማችሁ አብዛኛው ያተኮረው በአገራችን የተከሰተውን የጦርነት ሁኔታ በማስመልከት በመሆኑ በጣም ጥሩ ነበር። በይበልጥ ደግሞ እያንዳንዱ ምሁር ስለጦርነቱና ስለግጭቱ ሁኔታ የሰጠውን አስተያየቶችና ምክር አዘል ጽሁፎች በተመስጦ በማንበቤ የነበረኝን የተመሰቃቀለ አመለካከት ላጠራና ትክክለኛ አቋም ልይዝ ችያለሁ ለዚህም ላንዳፍታን፣ ምሁራኖችንና የፖለቲካ ሰዎቻችንን ላመሰግን እወዳለሁ።

ሌላው ሳልጠቅስ የማላልፈው እባካችሁ መጽሔታችሁ አይዘገይ፤ በተቻለ መጠን ቶሎ ቶሎ ለማውጣት ሞክሩ። ቢቻል በየወሩ አለበለዚያ ደግሞ በሁለት ወሩም ቢሆን ወቅቱን ጠብቆ ይውጣ። በተለይ ይህ ወቅት ስለአገራችን ሁኔታ ወሬ(ዜና) የምንፈልግበት ጊዜ ነውና ትኩረት ልትሰጡት ይገባል። በተረፈ በርቱ እያልኩ የምሰናበታችሁ – አቤ ነኝ ከኦሃዮ።

# ከዜና ማኅደር

# እንዲህ ሆነ!

ውድ አንባብያን፤ የዜና ማህደር አቀራረባችንን በተመለከተ አንዳንድ ያደረግነው ለውጥ አለ። ያለነው ወጭ አገር በመሆኑና ድርጊቶች በሚከናወኑበት አካባቢዎች ባለመኖራችን የምናቀርባቸው ዜናዎች ከሌሎች የዜና ምንጮችና ጋዜጦች እያጠናቀርን መሆኑን እንገልፃለን። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሔታችን የምትዘጋጀው በየሁለት ወሩ በመሆኑ በአብዛኛው የምናተኩርባቸው ዜናዎች መጽሔቷ በምትወጣበት አካባቢ ያሉትን እንደሆነ ለመግለጽ እንወዳለን። ስለአቀራረባችን የተሻለ አስተያየት ልትሰጡን የምትፈልጉ እባካችሁ አነጋግሩን።

## ኢትዮጵያና ኤርትራ በከባድ መሳሪያና በእግረኛ ሠራዊት እየተዋጉ መሆኑን "ቻናል አፍሪካ" ዘገበ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሸምጋዮች ጥረት ለውጥ እያመጣም የሚል ምላሽ ሲያስደምጥ የነበረው የሻዕቢያ መንግስት ከጥቅምት 26 ቀን ጀምሮ ተከታታይ የከባድ መሣሪያ ተኩስ መፈፀሙንና በኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል በኩልም አፀፋዊ የተኩስ እርምጃ እየተወሰደ ነው ሲል የአካባቢውን ወታደራዊ ምንጮች የጠቀሰው ቻናል አፍሪካ አስታወቀ። ቻናል አፍሪካ በማከልም በተኩሱ ማየልና ተፋጠው የሚገኙት የሁለቱም ተዋጊዎች የሚያደርጉት የተኩስ ልውውጥ ያሰጋቸው በጦር ቀጠናው የሚገኙ 30,000 ሰላማዊ የሆኑ ነዋሪዎች ከሁለቱም ድንበሮች አካባቢ ቀያቸውን እየለቀቁ ነው ሲል አስታውቋል።

የሁለቱም አገሮች ባለስልጣኖች በከረረ ፕሮፓጋንዳ ምልልስ ላይ መሆናቸውን ዘገባው አመልክቶ ከሁለቱም ወገኖች የሚደመጠው ንግግር ውዝግቡን በሰላም ለመፍታት የነበረውን ተስፋ የሚያጨልም ነው ሲል ገልጿል። እንደወታደራዊ ጠበብቶች ገለፃ ደግሞ ሻዕቢያ የኢትዮጵያን መሬት በኃይል ይዟል። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትም ከተያዘው የኢትዮጵያ ግዛት ወዲህ የመከላከያ ምሽጉን መስርቷል። ሻዕቢያም በተመሳሳይ የመከላከያ መስመሩን አጥናክሯል። በወራሪው ኃይል አስገዳጅነት ብቻ ሳይሆን ለሰላሙ ጥረት ዋጋ በመስጠት ኢትዮጵያ እስካሁን የመልሶ ማጥቃ ውጊያ አላደረገችም። ወራሪውን ኃይል አስቀድሞ ለጥቃት የሚያንደረድሩ የከባድ መሣሪያዎች ተኩስ ማድረጉ ተጨማሪ የመሬት ይዞታ የመያዝ ፍላጐት እንዳለው በግልጽ ያስረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

ዳሩ ግን በመከላከል ላይ ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት የሻዕቢያን ወታደራዊ ጥቃት ከመከላከል ይልቅ የመልሶ ማጥቃቱን እርምጃ በፍጥነት ሊያደርግ ይገባል ይሉና በአካባቢው ያሉት ወታደራዊ ባለስልጣናት የጨበጡት ወታደራዊ ስትራቴጂ ምን እንደሆነ ማወቅ ባይቻልም ከእንግዲህ ግን ሰራዊቱ በመከላከል ውጊያ መወሰን የለበትም ሲሉ ከአጠቃላይ ወታደራዊ ትንታኔ ተነስተው አስተያየታቸውን መግለፃቸው ታውቋል።

እነዚሁ ወታደራዊ ጠበብቶች የጠቀሱት የማጥቃት እርምጃው ይህ ነው ተብሎ በሚታወቅ ወይም በሚገመት አቅጣጫ ላይደረግ ይችላል። የሻዕቢያ መከላከያ ወረዳ በሚሰጠው ጠቃሚ መረጃ ላይ የተመረኮዘ ሊሆን እንደሚገባው ገልጸው የሻዕቢያ ተዋጊ ኃይል ካለበት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ ችግር አንፃር ጊዜ ሳይሰጠው የሚወሰድ ወታደራዊ ርምጃ ዋጋ ሊያስገኝ እንደሚችል ተናግረዋል።

## የኤርትራ መሪዎች አክሱምንና ሁመራንም ይመኛሉ

የኤርትራ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሱም የኤርትራ ጥንታዊ ሥልጣኔ ማዕከልና ከኢትዮጵያ ይልቅ የኤርትራ መሬት መሆኑን የገለጡት በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በስትራተጂክ ጥናቶች ማዕከል ባደረጉት ንግግር በሜይ ወር 1998 በትግራይ ነዋሪዎች፤ ታሪካዊ ስፍራዎች፤ በልማት ተቋሞች፤ የትምህርትና የህክምና አገልግሎት ሰጭዎች ላይ ክላተስር ቦምቦችን ስለመጣላቸው አስተያየትና ጥያቄ በቀረበላቸው ወቅት በሰጡት መልስ ነበር። ሚኒስትሩ ኤርትራ ክላስተር ቦንብ እንደሌላትና ዓላማ ያደረገችውም በወታደራዊ ተቋማት ላይ መሆኑን ለማመልከት ሞክረዋል። ይህ አባባላቸው ደግሞ ቀደም ሲል ኢሳያስ አፈወርቂ በሰላማዊ የትግራይ ተወላጆች ላይ ያደረሱትን ጉዳት በማስመልከት "ስህተት ተፈጽሟል" ያሉትን የሚቃረን መሆኑ ተነግሮላቸዋል።

የኤርትራ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በስትራተጂክ ጥናቶች ማዕከል ባቀረቡት ሪፖርት የኢትዮጵያ የተወካዮች ምክር ቤት በአገራቸው ላይ ጦርነት ማወጁን፤ የኢትዮጵያ ጦር የኤርትራን ህጋዊ ዳር ድንበር መውረሩን፤ አሥመራን በአየር መደብደቡን፤ 30 ሺህ የሚበልጡ ኤርትራውያንና የኤርትራ ደም ያላቸው ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ በኢሰብአዊ መንገድ መባረራቸውን ከተጻፈ ንግግር አቅርበዋል። በተጨማሪም ኤርትራ ለሰላም መቆምዋንና የኢትዮጵያ መንግስት ግን በጦረኝነት መንገድ ለመግፋት መፈለጉን ገልጠዋል።

በተጨማሪም ስለ ሩዋንዳና የአሜሪካ የእርቅ ፎርሙላ፤ ስለአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሰላም ድርድር ሀሳቦች ያላቸውን አመለካከት ሲገልጡ በኤርትራ በኩል ተቀባይነት እንደሌላቸውና ኤርትራ የምትቀበለው የቀድሞው የአሜሪካ ብሔራዊ ፀጥታ ኃላፊ ሚስትር አንቶኒ ሌክ ያላቸውን አዲስ "ፎርሙላ" መሆኑን ገልጠዋል። በንግግሩ ፍጻሜ ላይ ኢትዮጵያውያኑ ተሰብሳቢዎች የደረሱበት ድምዳሜ ኤርትራ በወረራዋና በተስፋፊነትዋ እቅድ ውስጥ አክሱምን በይገባኛልነት ማስገባትዋን ነበር። የኤርትራ መሪዎች በጦረኝነት ፖሊሲያቸው እየገፉበት መሆኑን ሌላው ምልክት በሰሜን ምዕራብ በሁመራ አካባቢ ከፍተኛ ጦር እያከማቹ መሆኑ ነው።

በሌላም በኩል የኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ በኤርትራ መገናኛ ብዙኃን በሰጡት

መግለጫ ... የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሚያቀርበው አዲስ የመፍትሄ ሀሳብ አይኖርም፤ ያው ተኩስ ይቁም፣ ድንበሩን ለማመላከት የሚበጅ ሁኔታ ይመቻች ከሚለው ውጪ ሌላ መጠበቅ አይቻልም። ይህም ቢሆን በወያኔ መሪዎች ተቀባይነት ስለማይኖረው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊመጣ የሚችል መፍትሄ አለ ብሎ መጠበቅ በእጅጉ አዳጋች እንደሚሆን ገልፀው፤ የኤርትራ መንግስት መሬቱን ትቶ፣ ሉዓላዊነቱን አስደፍሮ፣ ይህን የመሰለ ነገር ማለትም ኮንሲሽን ያደርጋል የሚል ተስፋ ካላቸው ተስፋ ሊቆርጡ የሚገባ ጉዳይ ነው። ወያኔዎች እንደው ጊዜ ለማጥፋት የሚሉት ካልሆነ በስተቀር ተጨባጭ ይዘት ያለው ጉዳይ አይደለም በማለት የቀድሞ አቋማቸውን አጠናክረዋል።

## በተባረሩት ኤርትራውያን ላይ አፋር አካባቢ በተከፈተ ተኩስ ሁለት ሰዎች ቆሰሉ ኤርትራውያን ትላልቅ ነጋዴዎችና ባለስልጣናት ዛሬም በኢትዮጵያ አሉ

ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ተሰባስበው ጥቅምት 2/91 በቡሬ ግንባር በኩል የተሸኙ ኤርትራውያን ላይ አፋር ክልል ውስጥ ማንነቱ ያልታወቀ ኃይል ጥቅምት 3/91 በአውቶብሳቸው ላይ በከፈተባቸው ተኩስ ሁለት ሰዎች ሲቆስሉ በሌሎች ተጓዦች ላይ ግን ጉዳት አለመድረሱን ከወደዚያው የተገኘው ዜና ያስረዳል። ታጣቂዎቹ በጥቃቱ ብዙ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ኤርትራውያኑን በማጀብ የተንቀሳቀሱት ፖሊሶች ባደረጉት መከላከል ታጣቂዎቹ በመጡበት መመለሳቸውን ዜናው ያብራራል። በኤርትራውያኑ ላይ ጥቃቱን የሰነዘሩት በኤርትራውያን ላይ የመረረ ጥላቻ ያደረባቸው አፋሮች ይሆናሉ የሚል ግምት ቢንፀባረቅም ሻዕቢያ ከፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታና ለዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ እንዲህ ያለውን ውንብድና ሊፈጽም እንደሚችል ግምታቸውን የሚያሳርፉ ጥቂት አይደሉም።

በሌላ በኩል የማባረሩ እርምጃ መቀጠሉ የህዝብን ስሜት ያረካ ቢሆንም የቤት እመቤቶችንና ጡረተኞችን እያባረረ የሚገኝ መንግሥት ኤርትራውያንን ዛሬም በስልጣን ላይ ማስቀመጡና ታላላቅ ነጋዴዎችንም በዝምታ መመልከቱ የዚህን መንግሥት አቋም አጠራጣሪ አድርጐታል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። በንግድ አለም ከተሰማሩት ኤርትራውያን ውስጥ በእርግጥ ብዙዎች የተባረሩ መሆናቸው ቢታመንም ዋና ዋና የሚባሉት በሪፈረንደሙ መሳተፋቸው በግልጽ የሚታወቅላቸው የሳምሶን ዳቦ ቤትና የቀስተ ደመና ስፖንጅ ፋብሪካ ባለቤት አቶ አቢሶሎም ይህደጐ፣ የያኮና ኢንጅነሪንግ ባለቤት አቶ ሮበርት ያኮና፣ የበላይ ተክሉ ኬክ ቤት ባለቤት አቶ በላይ ተክሉ፣ የሸዋ ዳቦ ቤት ባለቤት አቶ ዘሙይ ተክሉና የመሳሰሉት የንግድ ድርጅት ባለቤቶች ንግዳቸውን ያለከልካይ እንዲነግዱ በመፍቀድ ላይ ያለ መንግሥት በዝቅተኛ ኑሮ በሚገኙ ኤርትራውያን ላይ የሚወስደው እርምጃ ለሃገር ደህንነት በማሰብ ነው ለማለት ያስቸግረናል የሚሉ ወገኖች ቁጥር እየበረከተ ነው። በተጨማሪም ጡረተኞችን ጨምሮ የሚያባርረው ይሄው መንግሥት ዛሬም ኤርትራውያንን በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ማስቀመጡ ሌላው አጠያያቂና ጥርጣሬውን የሚያበረታና ግራ የሚያጋባ መሆኑን ታዛቢዎች ይናገራሉ። በነፃው ፕሬስ ያልተቋረጡ ጉትጐታና ህዝቡም በየመድረኩ በሚያሰማው ጩኸት በመብራት ኃይልና በቴሌ ውስጥ በኃላፊነት የተቀመጡት ኤርትራውያን ቢነሱም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮና በአንዳንድ ቁልፍ ቦታዎች የሚገኙ ኤርትራውያን ዛሬም በስልጣን ላይ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል።

## ከ30 ሺ.ህ በላይ ኤርትራውያን ተሸኝተዋል 28 ሺህ ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ተባረዋል

የኤርትራው ሻዕቢያና የኢትዮጵያ የኢህአዴግ መንግስት ወደ ጦርነት ለመግባት እየተጠበቁ ባሉበት ወቅት ጋብ ብሎ የነበረው አንዱ የሌላውን ዜጐች የማባረሩ እርምጃ በቅርቡ በሁለቱም አገሮች በስፋት እየተከናወነ መሆኑን የዜና አውታሮች እያስደመጡ ነው።

እስካሁን ከኢትዮጵያ የተባረሩት የኤርትራውያን ብዛት 30 ሺህ መድረሱን የሻዕቢያ ሬዲዮ ገልፆ የማባረሩ እርምጃ ይገታ ዘንድ መማፀኑ ታውቋል። በተመሳሳይም ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በግፍ የተባረሩት ኢትዮጵያውያንም ቁጥር 28 ሺህ ሁለት መቶ መድረሱን ለመንግስት ቅርበት ያለው የፕሬስ ውጤት መዘገቡ ሲታወቅ፤ መንግስት በበኩሉ በጅቡቲ ጠረፍ በኩል የተባረሩት ኢትዮጵያውያን ብዙ ስቃይና ግፍ እንደደረሰባቸው ገልፆ ዕርምጃው ሰብዓዊ ክብርን የደፈረ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግስት በመግለጫው ማመልከቱ ታውቋል። ይህ በሁለቱም መንግስታት የሚታየው እርምጃ ውዝግቡን በሰላም እንፈታለን ለሚሉት ሽምጋዮች ተስፋቸውን የሚያሟጥጥ ነው ተብሏል።

ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚባረሩት የኤርትራ ሰዎች ህይወት ያሰጋኛል ሲል ኢትዮጵያን በሰብአዊ መብት መጣስ የወቀሰው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ባሰራጨው ዘገባ እጅግ መፀፀታቸውን የጽ/ቤቱ ባለስልጣን ወ/ሮ ሮቢንሰን መግለፃቸው ሲታወቅ፤ ይሁን እንጂ መስሪያ ቤታቸው ከኤርትራ በግፍ ስለሚባረሩት ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ መብታቸው መደፈር እስካሁን የሰጠው መግለጫ ባለመኖሩ የወ/ሮ ሮቢንሰን መስሪያ ቤት ዛሬም ኢትዮጵያውያንን አስመልክቶ ያለው አመለካከት የተዛባ መሆኑን አመልካች ነው የሚል አስተያየት አስከትሏል።

## ሻዕቢያና የመን አዲስ ግንኙነት እየመሰረቱ ነው

የሻዕቢያ መንግስት በኃይል የያዛቸውን የሃኒሽ ደሴቶች በዓለም ፍ/ቤት ለቆ እንዲወጣ ከተወሰነበት በኋላ ሃኒሽን በእጁ ካገባው ከየመን መንግስት ጋር አዲስ ወዳጅነት ለመፍጠር ፕሬዚዳንት ኢሳያስና ባለስልጣኖቻቻቸው ከየመን መንግስት ጋር ተከታታይ ግኑኝነት እያደረጉ መሆናቸውን የዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች ዘገባ ያስረዳል።

በጥቅምት ወር መጨረሻ አካባቢ ባለስልጣኖቻቸውን አስከትለው የመን የገቡት አቶ

ኢሳያስ አፈወርቂ የየመንን ወታደራዊ ዕርዳታ ለማግኘት መማፀናቸውን የዜና አውታሮቹ ዘገባ ያስረዳል። ኢሳያስ አፈወርቂ ከየመኑ ፕሬዚዳንት አሊ አብደላ ሳላህ ጋር ባደረጉት ውይይት ኤርትራና የመን የጋራ ኢኮኖሚያዊ ትብብር መፈራረማቸውን ሲገለፅ ከዚሁ ጋር ወታደራዊው ስምምነት አብሮ እንደተከናወነም የዜና አውታሮቹ ጠቆም አድርገው ያለፉት የሃኒሽ ደሴቶችን ወርሮ በኃይል ከያዘው ከሻዕቢያ ኢሳያስ ጋር አዲስ የፈጠረችው ግኑኝነት ኢትዮጵያን ከወራሪው ኃይል ጋር በመሆን ወንጀለኛ አድርጋ በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት ገትራ የረታችውን ኃይል ለምን ወዳጅነት እንደፈለገች በግልጽ የወጣ ማስረጃ ባይኖርም በአካባቢው የአረብ አገራትን የበላይነት ለማስፈን ፍላጐት ካላቸው ከአረብ ሊግ አባል ሃገራት በተደረገ ግፊት መሆኑን የፖለቲካ ተንታኞች ያስረዳሉ።

## የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሐሰን አሊ እንደወጡ ቀሩ

ለህክምና ወደ እንግሊዝ አገር የሄዱት ምክትል ፕሬዚዳንት ሃሰን አሊ ህክምናቸውን ጨርሰው ወደ ሃገር ቤት የመመለሻ ጊዜያቸው ያለቀ ቢሆንም እስካሁን ወደ አገር ቤት ያልተመለሱት ለህክምና በሄዱበት አገር ለንደን ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ በመሆናቸው ነው ሲሉ ለንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያኖች መግለፃቸው ታውቋል።

አንዳንድ ለእሳቸው ቅርበት ያላቸው ወገኖች እንደሚሉት አቶ ሐሰን አሊ ከኢፌድሪ ምስረታ በፊት የኦሮሚያ ፕሬዚዳንት እንደነበሩ ሲታወቅ ከምስረታው በኋላ ደግሞ የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው መሾማቸው ቅሬታ አሳድሮባቸው እንደነበረ መናገራቸውን አስረድተው፣ በማያያዝም አቶ ሃሰን በመምህርነት ሙያ እያገለገሉ ባሉበት ወቅት ኢህአዴግ ደርግን ጥሎ በትረ ስልጣኑን እንደያዘ አፈላልጐ የኢህአዴግ ጣምራ ለሆነው ኦህዴድ ያለ ምንም ቅድመ ትግል ለአባልነት ያበቃቸው በመሆኑ በነባርና በትጥቅ ትግል በበቁ በኦህዴድ ካድሬዎች ብዙም ተቀባይነት በማጣታቸው በስራቸው ላይ ደስተኛ እንዳልነበሩ ይጠቅሳሉ።

አቶ ሐሰን አሊ በሥልጣን ዘመናቸው ፈፅመዋል ተብለው በሚጠረጠሩበት የሙስና ተግባር ለችግር እጋለጣለሁ ብለው ይስጉ እንጂ በአንዳችም ፖለቲካዊ ምክንያት ጥገኝነት ሊጠይቁ እያደርጋቸውም የሚል አስተያየት ከእነዚሁ የቅርብ ምንጮች ተሰጥቶበታል። የአቶ ሐሰን አሊ እንደወጡ የመቅረት ዜና ከእነዚህ ቅርበት አለን ካሉት ወገኖች ተሰማ እንጂ መንግስትም ሆነ የክልሉ ቢሮ ለህክምና ሄደዋል ከማለት በቀር ሌላ ምላሽ መስጠት እንዳልፈለገ ታውቋል።

## የፓሪሱ ጉባዔ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አዲስ አበባ ተከፈተ

በፓሪስ ከተማ ህብረትና የትግል ሰነድ ጨብጦ ለሰላማዊ ትግል ራሱን ያዘጋጀው የተቃዋሚዎች ኅብረት በአዲስ አበባ ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መመስረቱን የኅብረቱ አስተባባሪና የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት ሊቀመንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ገለፁ።

ኅብረቱ ዘላቂ ሰላምና የተሟላ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መፍጠር ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከተቃዋሚዎች ጋር አብሮ ለመስራትና ፈቃደኛ መሆን ያልቻለው የተጠናከረ ተቃውሞና ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ የተቃውሞ የፖለቲካ ኃይሎች እንቅስቃሴ አለመኖሩ ነው። የተቃዋሚዎች በጋራ በኅብረት ከመቆም ይልቅ ተነጣጥለው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለገዢው ፓርቲ ጉልበት መፍጠር መሆኑን አምነውበት ካለፉት የትግል ተሞክሮዎች በመነሳት አዲስ የትግል ስልት ለመቀየስ መነሳታቸው በሃገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ህይወትን ለመፍጠር ላቅ ያለ ድርሻ ሊያበረክት እንደሚችል ዶ/ር በየነ ገልፀዋል።

አያይዘውም ኅብረቱ ከተመሰረተ ሁለት ወራት ያልሞሉት ቢሆንም በዚህ አነስተኛ ጊዜ ውስጥ የማይናቅ ተግባር ሲያከናውን ቆይቷል። በተለይ በዓለም አቀፉ ዲሞክራሲያዊ ጥረት ውስጥ ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝ፣ ከኔዘርላንድና ኖርዌይ መንግስታት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር በሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ሰፋ ያለ ንግግርና ውይይት ማድረጋቸውንና ታላቅ ተስፋ መጨበጡን ዶ/ር በየነ ገልፀዋል። በተለይም እነዚህ የህብረቱ አስተባባሪ ሃገሮች ለጋሽ ሃገሮች እንደመሆናቸው መጠን በሃገሪቱ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድተው ዘላቂ ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባት ግፊት ያደርጉ ዘንድ ከበቂ በላይ ግንዛቤ እንዳገኙ አስታውቀው፣ በአውሮፓና በአሜሪካ የህብረቱን ጽ/ቤት ለመክፈት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንደተመቻቹና በተጨማሪም የህብረቱ ሰነዶች ለሚመለከታቸው ክፍሎችና የህብረቱ ዓላማ ላልገባቸው ኃይሎች እንዲደርስ ተደርጓል። በአውሮጳም ሆነ በአሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን የህብረቱን መቋቋም በእጅጉ ደግፈዋል። በመንግስቱ በኩልም የህብረቱን ምስረታ ለማደናቀፍ አለመሞከሩ በጐ ሆኖ ቢታይም መንግስት ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችለውን ግልጽ አቋም በይፋ ማሳወቅ ይጠበቅበታል ሲሉ ዶ/ር በየነ አሳስበዋል።

መጪውን የምርጫ ዘመንም አስመልክቶ የህብረቱ ተሳትፎ ምን እንደሆነ ሲያስረዱ በመጪው ምርጫ እንሳተፋለን ወይም አንሳተፍም የሚል መልስ መስጠት አይቻልም። ከምርጫው በፊት አንዳንድ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በድርድር መፈታት አለባቸው። ለዚህም ህብረቱ የብሄራዊ ውይይት ሃገራዊ ጥሪ አስተላልፈዋል። በመንግስት በኩል ግን እስካሁን ምንም ምላሽ አልተሰጠም ብለዋል።

## አቡነ ጳውሎስ በሌብነት 7 ዓመት ለተፈረደባቸው ግለሰብ ሹመት ሰጡ

በ1973 ዓ.ም. በሰሜን ጐንደር ዞን ለሚገኙ የገዳም መነኮሳት ከአንድ የውጭ ድርጅት የተበረከተ 15 ቦንዳ አቡጀዲ ልብስ በ20 ሺህ 214 ብር በመሸጥ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ግለሰብን አቡነ ጳውሎስ ሹመት እንደሰጧቸው ተገለጠ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች በነበሩ መምህራን እየተዘጋጀ የሚወጣው "ሐዋርያ" የተባለ ጋዜጣ ነው ይህንን የአቡነ ጳውሎስን ድርጊት ያጋለጠው። እንደጋዜጣው ዘገባ እኚህ በአቡነ

ጳውሎስ የቤተክርስቲያኒቱ የህግ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊነት የቀበሉት መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ ከላይ በተጠቀሰው ወንጀላቸው ግለሰቡ ክስ ተመስርቶባቸው የ7 ዓመት ጽኑ እስራትና የ500 ብር መቀጫ እንደተጣለባቸውም አስፍሯል። ጋዜጣው በተጠቃሹ ግለሰብ ማለትም በመሪጌታ ጥሩነህ ላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ብይን ሙሉ ቃልም በጋዜጣው ላይ አስፍሯል። ጋዜጣው ዘገባውን በመቀጠል ግለሰቡ ይኸው እኩይ ድርጊታቸውን በመድገም ባለፈው ዓመትም የፈፀሙትን የማጭበርበር ተግባር ሲያጋልጥ፤ ጥቅምን በህገወጥ ለመሻት የማታለል ተግባር ፈጽመዋል ተብለው በወረዳ 14 ፖሊስ ጣቢያ በምርመራ ላይ መሰንበታቸውንና በወንጀል መከሰሳቸውን ዘርዝሮ፤ አቡነ ጳውሎስ በወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ የተጠቀሱትንና በይፋም ፍርድ ቤት የቀጣቸውን ግለሰብ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ የህግ አገልግሎት ኃላፊ አድርገው ማስቀመጣቸው ታዛቢዎችን ሁሉ ግራ ያጋባ ጉዳይ ሆኗል። ይህም ድርጊታቸው ባለባቸው ኃላፊነት የሚፈጽሟቸውን እኩይ ድርጊቶች ለመሸፈን ይተባበሩኛል በሚል መንፈስ እንዳስቀመጧቸው ግምታቸውን የሚያሳርፉ ወገኖች የበረከቱ መሆናቸውን ዘገባው አክሎ ጽፏል።

## አቶ ታምራት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስና ጄኔራል ፃድቃን እንዳስፈራሯቸው ለፍ/ቤት ተናገሩ

የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና መከላከያ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጥፋተኛ ነኝ ብለው እንዲያምኑ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ሁለት ባለስልጣኖች እንዳስገደዷቸው ይፋ አደረጉ። አቶ ታምራት ጥቅምት 25ና 26 ቀን 1991 ዓ.ም. ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት ጥቅምት 19 ቀን 1989 ዓ.ም. በምክር ቤት ውስጥ ጥፋተኛ ነኝ ብለው እንዲያምኑና ምክር ቤቱን እንዲለቁ ግፊት ያደረጉባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና በወቅቱ የርሳቸው የበታች የነበሩት ጄኔራል ፃድቃን ገ/ተንሳይና ሌላ ሶስተኛ ሰው ቤታቸው ድረስ በመሄድ ይህንን ማስጠንቀቂያ እንደሰጧቸው ለፍ/ቤቱ ይፋ አድርገዋል።

በዚሁ ረቡዕ ጥቅምት 25 ቀን 1991 ዓ.ም. በተሰየመው ችሎት አቶ ታምራት ይህንን ከላይ የተቀመጠውን ቃል ለፍ/ቤቱ ከመግለፃቸው በተጨማሪ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የህግ ክፍል ኃላፊ የሆኑትን አቶ መስፍን ለማን በመከላከያ ምስክርነት አቅርበዋል። እኚህ ከአቶ ታምራት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ዘመን አንስቶ እስካሁንም ድረስ በጠ/ሚኒስትር ቢሮ የህግ ክፍል ኃላፊ የሆኑት ግለሰብ ኢትኮ በተባለው ካምፓኒ እና በመንግሥት መካከል ተፈጥሮ የነበረው ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን ተናግረዋል። የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ባለፈው ሚያዝያ ወር 1990 ውስጥ በጥበቃ ኃላፊዎች በጥፊ መመታታቸውን ለችሎቱ ማሰማታቸው ይታወሳል።

## የቀድሞ ሠራዊት አባላት ወደየመጡበት እየተመለሱ ነው

ከሻዕቢያ ወራሪ ጦር የተሰነዘረውን ጥቃት ለመከላከል መንግስት ላደረገው ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ይሰሩበት ከነበረው ሥራቸው በመልቀቅ ወደ ጦር ካምፕ የገቡ የቀድሞ ሠራዊት አባላት በኢህአዴግ መንግስት ባለመታመናቸው ወደየመጡበት እንዲመለሱ እየተደረገ መሆኑን ማዕበል የቶስኘ የነፃ ፕሬስ ጋዜጣ ዘግቧል። ጋዜጣው ከስፍራው ተመለሱ ያላቸውን አባላት ቁጥር ጠቅሶ እንደዘገበው ከቀድሞው ሠራዊት መካከል የምድር ጦር ማመላለሻ አባላት ከነበሩት 170 የሚሆኑት ማዕከላዊ ዕዝና አዋሽ አርባ ከ2 ወር በላይ የኢህአዴግን የርዕዮተ ዓለም ትምህርትና የሚሊተሪ ሳይንስ ተሐድሶ ሲከታተሉ ከነበሩት ውስጥ 130 የሚሆኑት ወደየመጡበት እንዲመለሱ ተደርገዋል። አባላቱ እንዲመለሱ የተወሰነባቸው በኦሮሞነታቸው በአማራነታቸውና እንዲሁም ፍጹም የሆነው ኢትዮጵያዊ አቋማቸው እምነት እንዳይጣልባቸው በማድረጉ መሆኑን ጋዜጣው አስረድቷል።

## የኦነግን ሠራዊት ለመጨረሻ ጊዜ ለመምታት ኬንያ ጦሯን አሰለፈች

ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ድንበር በመጣስ አንዳንድ አካባቢዎችን ከተቆጣጠረ ወዲህ በአገሪቱ የተለያዩ የድንበር አካባባዎች የሚታየው የወረራ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መምጣቱን ካለፈው ሳምንት ጀምሮ የተደመጡት የተለያዩ የዓለም መገናኛ ብዙኃን እየዘገቡ ነው። ፀረ–ኢትዮጵያ አቋም በመያዝ ከሻዕቢያ ጋር ወግኖ የነበረው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በጥቅምት ወር በኬንያና በኢትዮጵያ ድንበር ላይ በሰነዘረው ማጥቃት 150 ሰዎችን በመግደል በሶስት ሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ወደ ጐረቤት አገር ኬንያ እንዲሰደዱ ምክንያት መሆኑን የቢቢሲ ሬዲዮ አመልክቷል።

ይኸው ዋጂር በተባለች ከተማ ላይ የተቃጣው ወረራ በቦረናና በአካባቢው ላይም በመቀጠል ንፁሐን ዜጐችን አደጋ ውስጥ መክተቱን ዘገባው ይጠቁማል። የሁኔታውን አሳሳቢነት የተረዳው የኬንያ ፖሊስ ኮሚሽን የአካባቢውን ደህንነት ለማስከበር አፋጣኝ እርምጃ ወሰዷል። ከሁለት ወራት በፊት የኦነግ ጦር በአካባቢው በመታየቱ የተነሳ ወደ ኬንያ አቅንተው የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከኬንያው ፕሬዚዳንት ዳንኤል አራፕ ሞይ ጋር ተገናኝተው ከተወያዩ በኋላ ኦነግ ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት በጋራ ለመከላከል ስምምነት ማድረጋቸውን ይታወሳል። ይሁንና የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ከሻዕቢያ መንግስት የተሰነዘረበትን ጥቃት ለመከላከል በግዳጅ ላይ በመሆኑ የኬንያ መንግሥት ጉዳዩን እንደራሱ ደህንነት በመቁጠር ሠላም የማስከበሩን ተልዕኮውን እንዲወጣ ሁለቱም መንግስታት እንደገና በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ ከስምምነት መድረሳቸው ተገልጿል።

በዚሁም መሰረት የኬንያ መንግሥት በአካባቢው የነበረውን የፖሊስ ኃይል ቁጥሩ ባልተጠቀሰ ወታደራዊ ኃይል መተካቱንና አካባቢውን የማረጋጋት

ጥረቱን መጀመሩን የጠቀሰው የቢቢሲ ዘገባ፣ በተወሰኑ የቦረና አካባቢዎች፣ በሁለቱ አገሮች የጋራ ድንበር ላይ በሚገኘው ስቴፋኒ ተብሎ በሚጠራው ሐይቅ አካባቢ፣ ሜጋና ከድንበር በታች ዋጂር ተብለው በሚጠሩ የድንበር ከተሞች አካባቢ የሚታየውን የኬንያ ጦር ሠራዊት ቁጥር ለመገመት ቢያስቸግርም፣ ከቀላል እስከ ከባድ መሣሪያ የታጠቁና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች የተጠናከሩ መሆናቸውን አትቷል።

ይህ በዚህ እንዳለ የኬንያው ፕሬዚዳንት ዳንኤል አራፕ ሞይና የኬንያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ቦያና ጉዳና በኦነግ ታጣቂ ኃይል የተጉዳችውን የዋጅርን ከተማ በመጐብኘት ከተማዋን መልሶ ለመገንባት ህዝቡ እንዲረባረብና ጥረት እንዲያደርግ መጠየቃቸውን የቢቢሲ ሬዲዮ ዘገባ አረጋግጦ፣ በከተማዋ የደረሰውን እልቂት የፈፀመውን የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ለመጨረሻ ጊዜ ለመምታት ተፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን ከጉብኝቱ ፍፃሜ በኋላ ፕሬዚዳንቱ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ማብራራታቸውን ሬዲዮው ገልጿል።

## የሻዕቢያ መንግስት ዓለም አቀፍ የወደብ ህግን በመጣስ ለንደን ላይ ክስ ተመሰረተበት

ኢትዮጵያ የሻዕቢያ መንግስት ዓለም አቀፍ ህጐችን ጥሶ በኃይል አግቶ ያስቀራቸውን ንብረቶች በተመለከተ ክስ መስርታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ የወደብ ስምምነት ባለስልጣን ክሱን እየተመለከቱት መሆኑን ከኢትዮጵያ መገናኛ ሚኒስቴር የተገኘው ዜና ገልጿል።

ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ድንበር በኃይል ከያዘ ወዲህ በምፅዋና በአሰብ ወደብ በመቶ ሺህ ቶን የሚገመት የኢትዮጵያ መንግሥትና የግል ባለሀብቶች ንብረት አግቶ ስለመያዙ ያሰማው የእምነት ቃል የለም።

የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ንብረቶቻቸው የታገተባቸውን ባለሐብቶች ዝርዝር በማሰባሰብ ጉዳዩን ለሚያዩት ዓለም አቀፍ ኃይሎች ያቀረበ ሲሆን፤ እነዚህ ከ5 ወራት በላይ ያስቆጠሩ ንብረቶች፣ የኢንዱስትሪ ግንባታ ቁሳቁሶች፣ መድኃኒቶችና ሌሎች ለንግድ የመጡ ሸቀጦች በሻዕቢያ መንግስት እምቢተኛነት ታግተው ይህን ያህል ጊዜ በወደቡ ላይ በመቆየታቸው ብልሽትና ጉድለት ሳይደርስባቸው እንደማይቀር ይገመታል።

የሻዕቢያ መንግስት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያፀደቀውን ቻርተር ጥሷል። ከዚሁ ጋር በአባሪነት በፈፀመው ውንብድና በአለም አቀፍ የወደብ ስምምነት መሰረት ተጠያቂ ሊያደርገው እንደሚችል ቢታወቅም፣ ኢትዮጵያ ክሱን የመሰረተችው በጣም ዘግይታ በመሆኑ እስካሁን ፍርድ ሳይሰጥበት መቆየቱ ታውቋል። ክሱ በአለም አቀፍ የባህር ህግ አካላት እየታየ መሆኑ ቢታወቅም በተጓዳኝ አለም አቀፍ የመድን የጠለፋ ዋስትና ያላቸው የሀገር ውስጥ መድን ድርጅቶች በኢትዮጵያውያን ንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት አስመልክቶ የየራሳቸው እንቅስቃሴም እንደሚጠበቅባቸው የህግ ባለሙያዎች ሳይገልፁ አላለፉም።

## ዓለም አቀፍ የመምህራን ማህበር ዛሬም የምናውቀው እነ ዶ/ር ታዬን ነው አለ

በዓለም አቀፍ የትምህርት ድርጅት የአፍሪካ ኮርዲኔተር የሆኑት ሚ/ር ቶማስ ቢዲያኮ እና ምክትላቸው ሚ/ር ኢማኑኤል ፋቱማ የአንጋፋውን ኢመማ ችግሮች አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለስልጣናት ጋር የተሳካ ውይይት ማድረጋቸውን ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልፀዋል።

የትምህርት ዓለም አቀፍ የልዑካን ቡድን በሪፖርቱ ላይ ካቀረባቸው መካከል የአንጋፋውን የመምህራን ማህበር ችግሮች በቅርበት እየተከታተለ መሆኑን፣ በህግ የተያዙት የዶ/ር ታዬና የማኅበሩ ጉዳዮች ለህግ የሚተዉ መሆናቸውን በመግለፅ እያይዞም ማህበሩ እስካሁን ለነፃ የሙያ ማኅበራት መብት መከበር የከፈለውን መስዋዕትነትና ያሳየው መልካም አርአያነት በመላው ዓለም በሚገኙ እቻ የሙያ ማኅበራት ትልቅ አድናቆት የተቸረው መሆኑን በሪፖርቱ ላይ ማስፈሩ ታውቋል።

ይህ ዓለም አቀፍ የመምህራን ማኅበር በዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት ከሚመራው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ውጭ ዕውቅና እንዳልሰጠ መግለፁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና ያብራራል።

## ኢነጋማ ተጠናክሮ ሊደራጅ ነው

በቅርቡ ኢትዮጵያን ከጐበኙ የዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽንና ዓለም አቀፍ የፕሬስ ኢንስቲትዩት ልዑካን ጋር በተደረሰ መግባባትና የኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በገቡት ቃል መሠረት የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር ራሱን አጠናክሮ እንደሚያደራጅ ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር አስተባባሪ ኮሚቴ በጥቅምት ወር ባወጣው መግለጫ ሂደቱን "አዲስ የትግልና የአንድነት ምዕራፍ" ብሎታል። የአስተባባሪው ኮሚቴው ባወጣው መግለጫ፤ ከተቋቋመ 6 ዓመት ያስቆጠረው የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር በየወቅቱ በሚደቀኑበት መሰናክሎችና ፈተናዎች ምክንያት ዓላማውን ሙሉ በሙሉ ከግብ ለማድረስ እንዳልቻለና ከሁሉም በላይ ደግሞ በየዓመቱ በርካታ አባላቱ ለእስራት እንግልትና ስደት መዳረግ እንቅስቃሴውን የበለጠ የገታውና ያጓተተው መሆኑንም ገልጾ፤ እንዲሁም መንግስት ለማኅበሩ ህጋዊ ዕውቅና ባለመስጠቱ የነፃው ፕሬስ አባላት የመሰባሰቢያና የመማማሪያ መድረካቸውን አጠናክረው መብታቸውን በማስከበር በህግና ህጋዊነት ከለላ ሙያዊ ግዴታቸው በሚገባ ለመወጣት እንዳይችሉ መሰናክል እንደሆነባቸው ገልጧል። በመጨረሻም በተለይም ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን ብራስልስ፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቋም ለንደን፣ ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢው ተቋም–ፓሪስ፣ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ኮሚቴ–ኒውዮርክ፣ ሂዩማን

ራይትስ ዋሽግንተን፡ እና ሌሎችም አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ብሶታችንን በማስተጋባት፣ የኢህአዴግ መንግስት በነፃው ፕሬስ ላይ ጫና ከማሳደር እንዲገታ፣ ጋዜጠኞችን እንዲፈታ፣ ለሙያ ማኅበሩ ህጋዊ እውቅና እንዲሰጥ፣ የፕሬስ ህጉ እንዲሻሻልና የማኅበሩን የአመራር አባላት በሰበብ አስባብ ከማዋከብና ከማሰር ይልቅ፣ ተቀራርቦ በመስራት የሃገሪቱን የፕሬስ ነፃነት በተጨባጭ እውን ለማድረግ ግዴታውን እንዲወጣ በመምከር፣ በማሳሰብና አቤቱታ በማሰማት የወሰዷቸውን ገንቢ እርምጃዎች ሁሉ በአድናቆት እናያቸዋለን ሲል በመግለጫው ላይ አውጥቷል።

## የአየር መንገድ መካኒኮች ተቃውሞ እያሰሙ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከማርች 1998 ጀምሮ ለፓይለቶች ያደረገው የደመወዝ ጭማሪ ያስነሳውን ቅሬታ ለማካካስ ከኦክቶበር 1998 ጀምሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ለመካኒኮችም 36 ከመቶ ጭማሪ እንደሚያደርግ በይፋ ቢያስታውቅም ሠራተኞቹ አሰራሩ ፍትሐዊነት የጐደለውና አድሏዊነት የተንፀባረቀበት ነው በማለት ያማረሩ ሲሆን ማኔጅመንቱ ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ ካልሰጠው የኢንዱስትሪ ሠላም መናጋት እንደሚያሰጋው የአካባቢው ምንጮች ገለጡ።

ለአየር መንገዱ የህዝብና የዕቃ ማጓጓዣ አውሮፕላኖች እንዲሁም ለሌሎች አየር መንገዶች የተሟላ ጥገና በማድረግ ለድርጅቱ ገቢ ማደግና ህልውና ጠንካራ ክንድ የሆነው የጥገና ክፍል እንደ አልባሌ ሥራ ታይቶ በማኔጅመንቱ ዝቅተኛ ግምት መሰጠቱ በጣም ያሳዘናቸው መሆኑን የጠቀሱት እነዚሁ ሰራተኞች ሁኔታው በጥሞና ተመርምሮ የደመወዝ ስኬሉ አፋጣኝ ማሻሻያ ካልተደረገበት ውጤቱ አስከፊ ሊሆን እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

ይህ የተባለፈው 36 ከመቶ ጭማሪ 30 ከመቶው የመነሻ ደመወዝ መለወጫ ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በፀደቀው የህብረት ስምምነት ውስጥ የነበረ፡ ቀሪው 6 ከመቶ ደግሞ በቅርብ አለቃ በጐ ፈቃድ የሚሰጥ እንጂ እንደ መብት መቆጠር እንደሌለበት በየክፍሉ ስብሰባ ተደርጐ ለሠራተኛው መነገሩ የስራ ተነሳሽነትን ከመቀነሱ በስተቀር የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ የጠቆሙት ምንጮች በዚህ ቅሬታ የገባው ሠራተኛ ከዋና ሥራ አስኪያጅ ጀምሮ አቤቱታውን የሚቀበል ክፍል በማጣቱ ሁለት ቅዳሜና እሁድ ስራ ከመግባት ለመቆጠብ መገደዱን አስታውቀዋል።

## በጦርነቱ ሳቢያ የሁመራና የተከዜ ነዋሪዎች በመንግስት ትዕዛዝ ወደ ጎንደር ተንቀሳቀሱ

የሻዕቢያ የጥቃት ዒላማ በሰላማዊው ህዝብና ተቋማት ላይ እንደሆነ ያሰጋው የኢትዮጵያ መንግሥት በአውደ ግንባሩ አካባቢ ያሉትን ሰላማዊ ነዋሪዎች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ እያደረገ መሆኑን የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ከተከዜ ማዶ የሻዕቢያ ወራሪ ኃይል የተከማቸ መሆኑ ሲታወቅና ከተከዜ ወዲህ ደግሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ምሽግ ሰርቶ እንደሚገኝ ሲገለፅ፤ ጦርነቱ ለይቶለት ከተጀመረ ሻዕቢያ በአካባቢው ሰላማዊ ዜጐች ላይ የከባድ መሳሪያና የአየር ጥቃት ሊያደርስ እንደሚችል ያለፉት ተሞክሮዎች የሚያስረዱ በመሆናቸው ነዋሪውን ህዝብ ከውጊያ ቀጠና ማራቅ አስፈላጊ እንደሆነ የአካባቢው ባለሥልጣናት እምነታቸው መሆኑ ታውቋል።

## የኤርትራ ወራሪ ጦር የኢትዮጵያን ምድር ለቅቆ እንዲወጣ ሱዳን አስጠነቀቀች

የሻዕቢያ መንግስት በኃይል የያዛቸውን የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበሮችን በአስቸኳይ ለቆ ካልወጣ ሱዳን ግዛቷን ለማስከበር፣ ከኤርትራ የተሻለ አቅም እንዳላት የሱዳን ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አስጠነቀቁ። ባለስልጣኑ የኤርትራ የኃይል እርምጃ ለበርካታ የሱዳን ዜጐች ህይወት መጥፋትና ለነዋሪዎች መፈናቀል ምክንያት እንደሆነ አሳስበው በተመሳሳዩ ሻዕቢያ ከኢትዮጵያ ጋር የቀሰቀሰው የድንበር ግጭት በሰላም ካልተፈታ የአካባቢውን ሰላም የከፋ አደጋ ላይ ይጥለዋል ሲሉ አስጠንቅቀው፣ የመንግስታቸው አቋም ኢትዮጵያና ኤርትራ ውዝግቡን በሰላም ይፈቱ ዘንድ በተባበሩት መንግስታትና በአአድ የመሪዎች ጉባኤ የቀረበው የሰላም ሀሳብ ዋነኛ መፍትሄ ነው ሲል መቀበሉን በዚሁ ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ አስደምጠዋል።

ሚኒስትሩ ኢትዮጵያና ሱዳን የነበራቸውን የታሪክና የባህል ግኑኙነት ለማደስ በተሻለ እንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ ጠቅሰው በቅርቡም የሁለቱ አገሮች አየር መንገዶች ወደየሃገሮቻቸው እንዲበሩ ስምምነት ላይ መደረሱ ለግኑኙነታችን መዳበር አንዱ ማስረጃ ነው ብለውታል።

ሚኒስትሩ ሻዕቢያ የኢትዮጵያን መሬት በኃይል ወሮ ይዞአል። የሱዳንም መሬት በሻዕቢያ ተይዟል። ይህንን የጋራ ሰላም አደፍራሽ ጠላት አግልለው ሁለቱ መንግስታት የፈጠሩት አዲስ ግኑኙነት አካባቢውን በጋራ ለመጠበቅ የሚያስችል ወታደራዊ ቅንጅት ለመፍጠር ያመቻል የሚል አስተያየት መስጠታቸውም ታውቋል።

ሱዳን ሻዕቢያና ኢህአዴግ በትጥቅ ትግል ላይ በነበሩበት ወቅት ከፍተኛ ወታደራዊ ድጋፍና ቤዝ በመስጠት ትብብር ታደርግ እንደነበር ቢታወቅም ሁለቱም ነፃ አውጭዎች ለመንግስትነት ከበቁ ወዲህ ግን ከሁለቱም ቡድኖች ጋር የነበራት ግንኙነት ደፍርሶ እስከ ጦር መማዘዝ መድረሳቸው ይታወቃል።

## የቀድሞ የብር ኖቶች በሶማሌ ጠረፍ ተፈላጊነታቸው ጨምሯል

በደርግ ዘመነ መንግሥት ያገለግሉ የነበሩ የተለያዩ የኢትዮጵያ የብር ኖቶች በሶማሌና ሞያሌ ጠረፍ አካባቢዎች ከፍተኛ ተፈላጊነት እንዳላቸው ታውቋል። የቀድሞው አንድ መቶ ብር ኖት በአሁኑ 60 ብር፣ የ50 ብር ኖቱ ደግሞ በአሁኑ 30 ብር ይሸጣል። እነዚህን ብሮች ከአዲስ አባባና ከሌሎችም ከተሞች ወደ አካባቢው የሚንቀሳቀሱ የከባድ መኪና ሾፌሮች እየገዙ

እንደሚያቀርቡላቸው የመረጃ ምንጮቹ እየጠቆሙ፣ ይህ ሁኔታ ከጀመረ ከ6 ወር በላይ ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱን የገንዘብ ልውውጥና ንግድ የሚቆጣጠር አካል እስካሁን እንዳላጋጠማቸውም ገልጠዋል።


## አሜሪካ የምትሰጠው የምግብ እርዳታ እንደቀጠለ ነው

ለኢትዮጵያ የተላከው ተጨማሪ የምግብ ዕርዳታ ጅቡቲ ወደብ መድረሱን አዲስ አበበ የሚገኘው የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት አስታወቀ። የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት በዚህ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ሊያጓጉዝ ካቀደው 50 ሺህ ሜትሪክ ቶን ስንዴ ጅቡቲ ደርሶ ወደ ኢትዮጵያ እየተጓጓዘ መሆኑ አስረድተው፣ የምግብ እርዳታው በገንዘብ ሲተመን ወደ 10 ሚሊዮን እንደሚደርስም አክለው ገልፀዋል።

## የኢትዮጵያ እሥረኞች ጉዳይ ኮሚቴ ሱዳንን ተማፀነ

ተቀማጭነቱ ጀርመን የሆነው የኢትዮጵያ እስረኞች ጉዳይ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ሱዳን በአሁኑ ጊዜ ከወያኔ ኢህአደግ ጋር የጀመረችውን አዲስ ፍቅር በማጤን በልዩ ልዩ የአገሪቱ ወህኒ ቤቶች ያሉትን እስረኞችና ስደተኞች አሳልፋ እንዳትሰጥ ተማፀነ። ድርጅቱ ስጋቱን ሲያስረዳ በአሁኑ ጊዜ ጄኔራል መለስን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን የሱዳን መንግስት እሥረኞች በመሆን የእንቅስቃሴ ነፃነት ተነፍጉአቸው ይገኛሉ። በመሆኑም የጄኔራል አልበሽር መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ፍቅሩን የበለጠ ለማጠናከር ሲል እስረኞቹን አሳልፎ እንዳይሰጥ ለሱዳንም ሆነ ለሌሎች ዓለም አቀፍ ዴሞክራቲክ ድርጅቶች ሁሉ ድምፁን አሰምቷል።

በሌላም በኩል የወያኔና የሱዳን ጊዜያዊ ወዳጅነት በማስመልከት የአህአፓ ከፍተኛ አመራር አካል የሆኑት አቶ ኢያሱ አለማየሁ ጦማር ለተሰኘ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታተም ነፃ ፕሬስ ጋዜጣ ባደረጉት ቃለ ምልልስ የሱዳንና የኢህአዴግ መንግስት ስምምነት መፍጠር የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ኃይሎች ሊገታ እንደማይችል ገልጸው ወሳኙ የህዝቦችን ትግል ማገርና ምሶሶው ራሱ ህዝባችን በመሆኑ የሱዳን የፖለቲካ ገጽታ ትግሉን አይለውጠውም በሚል ሰፋ ያለ ትንታኔ የሰጡበት ሲሆን ሱዳን ደገፈ አልደገፈ የትጥቅ ትግል መደረግ ካለበት መደረግ፣ መቀጠል ካለበት መቀጠሉ አይቀርም ካሉ በኋላ ዛሬ አስከፊው ስርዓት ራሱ ቀባሪዎቹን ፈጥሮ ለግብዓተ መሬት ራሱን እንደሚያመቻች አስረድተዋል።

# A TO Z


ELECTRONICS & GIFTS

TV. - VCR. - Cameras - Phones - Stereos - Fax Machines


Watches - Luggage - Toys -Gift Items - Perfumes

ኤ ቱ ዚ ኤሌክትሮኒክስ

ከፓል ሴካም ወደ ኤን ቲሲና ከኤን ቲሲ ወደ ፓል ሴካም ቪዲዮ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መሥራት የሚችሉ ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ



1713 Church St. Suit A-1
Decatur, GA 30033
(Kroger Shopping Center)
Jayendra Patel & Dipa Patel
Tel/Fax: (404)299-9196



*Hours:*
*Tuesday to Sunday*
*11:00 am - 8:00 pm*
*Monday Closed*

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን እንኳን በደህና ወደአሜሪካ መጡ እያልን ይህን ቃለመጠይቅ እንድናቀርብልዎ በመፍቀድዎ ከልብ የመነጨ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥያቄዎች በመጽሔቱ አንባቢዎች ዘንድ የሚመላለሱ በመሆናቸው እርሶ የሚሰጧቸው መልሶች ትልቅ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው እናምናለን።



# ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ጥያቄ፦

ከኢትዮጵያ ወጥተው ወደ ባእድ አገር እንዲሰደዱ ያደረገዎትን ምክንያቶች፣ እንዴት ከአገር ሊወጡ እን ደቻሉ፤ በስደት ወቅት የኑሮዎ ሁኔታ እንዴት እንደነበር፤ በስደት ላይ በነበሩበት ወቅት ያጋጠምዎትን ችግሮች በአጠቃላይ ስለ ስደት ኑሮዎ መግለጫ ቢሰጡን?

መልስ፦፣፣

ከኢትዮጵያ እናት ሀገሬ ወጥቼ ወደ ባእድ አገር ልሰደድ የቻልኩበት ምክንያት የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ዋይታ፣ የቋንቋ የዘር የልብ ድካም በሽታ የሆኑት የዘመኑ መኳንን ቶች እኔ በነበርኩበት ወንበር ላይ የራሳቸው የሆነ ሰው ለማስቀመጥ ስለፈለጉ በአደረሱብኝ ግፍና በደል ለመሰደድ ችያለሁ፣፣ ነገር ግን ከእናት ሀገሬ ወጥቼ ብሰደድም የደረሰብኝ ችግር የለም። ቢሆንም ስደት በኔ አልተጀመረም። እራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በህፃንነቱ ተሰዶ የሰጠን ፀጋና በረከት ስለሆነ በህይወቴም ሆነ በኑሮየ ምንም ያጋጠመኝ ችግር የለም።

ጥያቄ፦

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አሁን ያለችበትን ሁኔታ እንዴት ያዩታል? እርስዎ ህጋዊ ፓትሪያርክ ሆነው ሳለ አባ ፓውሎስ እንዴት ሊመረጡ እንደቻሉና አሁንም ከህግ ውጪ በያዙት ስልጣናቸው የሚሰጡትን አመራር እንዴት ይመለከቱታል? በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘን ድስ በምን መልክ እየታየ ያለ ይመስልዎታል?

መልስ፦

ከህገ ቤተ ክርስቲያን (ከቀኖና) ቤተ ክርስቲያን ውጭ ፓትሪያርክ እያለ ፓትሪያርክ መሾም አይገባም። በሀገር ውስጥ ያለው ሲኖዶስ ከህገ ቤተ ክርስቲያን (ከቀኖና) ቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለሆነ ህገ ቤተ ክርስቲያን (ከቀኖና) ቤተ ክርስቲያንን የአወቁ የተረዱ የሃይማኖት መሪዎች ሊቃነ ጳጳሳት በስደት ሀገር ጥንታዊውን የሀዋሪያትን ሲኖዶስ በመከተል ቤተ ክርስቲያናችንም ሀዋሪያዊት እንደመሆኑ መጠን ያንኑ ሲኖዶሳዊ ጉባኤ በውጭ ሀገር በማካሄድ ይገኛል፣፣ ይህንንም ሲኖዶሳዊ ጉባኤ በመደገፍ ቀደም ሲል ፓትሪያርክ እያለ ፓትርክ መሾም አይገባውም በማለት ተቃውሞ አቅርበው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ካህናትና ምእመናን አሁንም በፅሁፍ ብቻ ሳይሆን በማህተም የተደገፈ መልክታቸው እየደረሰን ሲኖዶሳዊ ጉባኢያችን በማካሄድ እንገኛለን።

ጥያቄ፦

በአንድ ወቅት በቅዱስነትዎ ላይ በወያኔ መንግስት አማካይነት የተበተኑት ወረቀቶችና እንዲሁም የቅዱስነትዎን ስም እያነሱ የሚከተሉትን ክስ በመሰንዘር የሚያስወሩቦት እን ዳሉ እርስዎም ሳይደርሱበት የቀሩ አይመስለኝም፤ ለነኚህ የሚወሩት ወሬዎች ቅዱስነትዎ የሚሰጡት መልስ ካለ፤ አቡነ መርቆሪዎስ ከሻለቃ ተፈራ ጋር አብረው ሰርተዋል። ሰው ለማሳለም ሲሉ መስቀል አወጣሁ ብለው ሽጉጥ መዘዙ። ለደርግ መንግስት መሳሪያ መግዣ የገንዘብ እርዳታ ሰጥተዋል — የተሾሙት በደርግ እንጂ በቤተ ክርስቲያኒቱ አይደለም።

መልስ፦

ከሻለቃ ተፈራ መልአኩ ተፈራ ጋር አብረው ሰርተዋል ለሚለው ምን ለማለት ፈልገው እንደሆን ከወዲሁ መረዳት ይቻላል። በቀይ ሽብር ጊዜ እኔ የነበርኩት አዲስ አበባ የብስራተ ቅዱስገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ እን ደነበርኩ ካህናትና ምእመናን ያውቃሉ፤ ምስክሮች ናቸው። ከዚህም በኋላ ኤጲስ ቆጶስነት የተሾምኩ በ71 ዓ. ም. ሲሆን የተሾምኩትም ክፍለ ሀገር ሀረርጌ ነበር። በዓመቱ በ72 ዓ. ም. ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ተዛወርኩ። በዚህም ወቅት ምን ም የሚሰማና ምንም የሚታይ ነገር የለም ነበር። አብሮ ሰራ የሚባልበት እዳ በደል ግን ምን ይሆን? ሰው ለማሳለም መስቀል አወጣለሁ ሲሉ ሽጉጥ መዘዙ ይባላል? መስቀሉ ይህ ነው። ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል። ለመሆኑ ይህን መስቀል በኪስ ለመያዝ ይቻላል? አንተ ራስህ መፍረድ

ትችላለህ።

እኔ ለመሳሪያ መግዣ ገንዘብ አልሰጠሁም። መስጠትም አይገባኝም። ለተቸገሩ ወገኖቻችን ግን ቀደም ሲልም በኋላ የገንዘብ ርዳታ መሰጠቱ ግልፅ ነው። ይህውም ገንዘብ የሚሰጠው የሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበሩት ነው። ይህም ቢሆን ከላይ እስከታች፣ ከታች እስከላይ በእግዚአብሔር ጥሪ እንጂ በሰው እንዳልሆነ በመፅሀፈ ሳሙኤል 1ኛ ም16 ቁ5 ያለውም ኃይለ ቃል ቢመለከቱት በቂ ማስረጃ በሆናቸው ነበር። ነገር ግን እነዚህን ቃላቶች የሚአወሩ የሚአስወሩም በኃጢአት አረቁ የሰከሩ፣ ሀሰትን እንጂ እውነትን የማይናገሩ፣ ኣይነ ልቦናቸው የታወረ፣ እዝነ ልቡናቸው የደነቆረ፣ መላ ሰውነታቸው በመጥፎ ነገር የደነዘዘ፣ በተንኮልና በሀሰት ልስን ድስቅ ብሎ ሰውነታቸው ተመርጎ የመንፈስ ቅዱስ ጮራ መግቢያ አጥቶ የሚቃትቱ፣ ቅንኣት በተባለው ወተት የጎለመሱ፣ ምቀኝነት በተባለው ቅብኣት የለሰለሱ ስጋዊ ዜግነታቸውን ለዲያቢሎስ በማስመዝገብ የተሰለፋበትና ትጥቃቸውን የታጠቁበት ጊዜ ነበር።

ስለዚህ እነዚህ ሰማእተ ሀሰት ማለት የሀሰት ምስክሮች የተለያየ የነገር እንክርዳድ ይዘራሉ። ነገር ግን ስንዴውን ከእንክርዳድ ለይቶ አበጥሮ፣ አንጠርጥሮ ማወቅ ከእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ይጠበቃል።

ጥያቄ፦

በዚህ በውጪ አገር ደግሞ ያሉ አንዳንድ ሰዎች በደርግ ዘመን ያ ሁሉ ግፍ ሲሰራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዝም ብላ ነበር ይሉና ለዚህ ቅዱስነትዎን እንደ ምክንያት ለማቅረብ ይሞክራሉ። በቅርቡም ይህን ኑ በመጥቀስ "የኢትዮጵያ ሬጅስተር" በተሰኘ መፅሄት ይከው ተሰተጋብቶ አይተናል። ቅዱስነትዎ በደርግ ወቅት በፓትሪያርክነት የሰሩት ለጥቂት ጊዜ ሆኖ ሳለ ይህን ለማለት ምን ያነሳሳቸው ይመስልዎታል?

መልስ፦

ምንም የኔ ፓትርያርክነት ወደመጨረሻው ቢሆንም በፊትም ሆነ በኔ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ ሰላም በቤት፣ ሰላም በጎረቤት፣ ሰላም በሀገር አቀፍ፣ ሰላም በኣለም አቀፍ፣ ከሆነ ለሀገርም ለህዝቡም ከፍተኛ በረከት የሚገኝበት መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን፣ የስልምና፣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት መሪዎች ካንድ ላይ በመሆን ለብዙ ኣመታት ስለ ሀገራችን ስለወገናችን ጥልቅ ረቂቅ የሆነ ውይይት አድርገን ለሚመለከተው ሁሉ አስተላልፈናል። እን ዲሁም በመጨረሻው በአፍሪካ አዳራሽ የኣለም አቢያተ ክርስቲያናት ተወካይ በተገኙበት ውይይት አድርገን ለኣለም ሰላም ወዳድ ወገን ለሆነው ሁሉ አስተላልፈናል። በተጨማሪም ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት መጥተው ለነበሩት ለካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ (የእንግሊዝ) በአልክሳን ድርያ ተቀማጭ ለነበሩት ለግሪክ ፓትሪያርክ፣ ለካናዳ አብያተ ክርስቲያናት ተወካይ ለሆኑት እና ለሌሎችም ስለ ሀገራችን ስለ ወገናች፣ ስለቤተ ክርስቲያናች ስለሃይማኖታችን የነበረውን ችግር ሁሉ ማስተላለፋችን በጊዜው በወጡት መፅሄቶችና ጋዜጦች መመልከቱ ይጠቅማል። በቂ መረጃም ይሆናል ብለን እናምናለን። ምክንያቱም የሀገር ሰላም የቤተ ክርስቲያን ሰላም ነው፤ የሀገር ነፃነትም ለሃይማኖት ነፃነት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንዝም ብላ ያየችበትና የተመለከተችበት ወቅትና ጊዜ የለም፤ ሊኖርም አይገባም። ይሁን እንጂ እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ሬጅስተር የተሰኘው መፅሄት ያወጣው ግን ፅድቅን በኃጢአት፣ እውነትን በሀሰት፣ አምልኮትን በክህደት፣ ወንጌልን በኦሪት የሚለውጡትን ከለዩዋቸው ኢሊህ አምኖ ከሚገኘው ተሰፋ የወጡ ናቸው የሚለው አምላካዊ ቃል ቋሚ ምስክር ሊሆን ባቸው ይገባል።

ጥያቄ፦

የህወሃት የጎሳ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል አገር ቤት ሆነው መታገልና ህዝቡን መምራት ሲኖርባቸው ለምን ስደትን መረጡ ለሚሉዎት ምን ይሏቸዋል? በስደት ላይ በቆዩበትም ወቅት በሃይማኖትም ሆነ በሃገር ጉዳይ ላይ ድምፅዎን ለረጅም ጊዜ ለምን አላሰሙም ለሚሉዎትስ?

መልስ፦

ስለሀገርም ሆነ ስለሃይማኖት ከወጣሁበት ጀምሮ ጥያቄ ቀርቦልኝ ሰፋ ያለ መልስ ሰጥቼበታለ። ነገር ግን የባእድን ወሬ ተከትለው፣ የሀገር ታሪክ ወደኋላ ጥለው የኢትዮጵያንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ክብር ለመቀነስ የሚናገሩ አፈብልጦች ካልሆኑ በቀር አሁንም ወደፊትም ስለ ሀገራችን፣ስለቤተ ክርስቲያናችን፣ ስለጥንታዊ ቅርሳችን እኔ ብቻ ሳልሆን የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች የሆነ ሁሉ መናገርና ማስረዳት፣ መጠበቅና ማስጠበቅ ወገናዊና ታሪካዊ ግዴታ ነው።

ጥያቄ፦

አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ህልውናዋ አደጋ ላይ የወደቀበት ጊዜ በመሆኑ ህዝቡ አገሩን ለማዳንና መብቱን ለማስከበር ከመቼውም የበለጠ የመንፈስ ፅናት እንደሚያስፈልገው ይታመናል። በቅዱስነትዎ የሚመራው ሲኖዶስ ኢትዮጵያን ከወያኔ የጎሳ አገዛዝ ለማዳን እንዲሁም ከሻቢያ ወረራ አገሪቱን ለማዳን ምን ኣይነት ሚና እየተጫወተ ነው? ምንስ ለማድረግ እቅድ አለ?

መልስ፦

እባብና ዲያቢሎስ ተያይተውና ተስማምተው ባመጡት ጣጣ በፍሬው ላይ የታጢአት ዋግ የመታው፣ የመቅሰፍት የሞት ትል የበላው፣ ጠላት የዘራው እንክርዳድም ተገኘበት፤ በዚህም ምክንያት ዘሩ ሁሉ ቅድስና ሊአገኝ አልቻለም። ሀገራችን ኢትዮጵያም በአሁን ወቅት ህልውናዋ ከመቸውም በበለጠ ከአደጋ ላይ የወደቀችበት ወቅት በመሆኑ ከወደቀችበት ፈተና አልፋ፣ ከመርገም ወጥታ ወደ በረከት ገብታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋን ቋ ልዩነት የሌለበትን ክብር ተጎናፅፋ፣ በኦሮዋ መለዋወጥ፣ በመንግስት መገለባበጥ ሳይኖርባት እንድትኖር ባለፈው ሲኖዶሳዊ ስብሰባችን ዳር ድንበሯ ተከብሮ ለኖረችው ሀገራችን ስለ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችንና ቅርሳችን

ስለ ተዋህዶ ሃይማኖታችን ሰፋ ያለ መልእክት አስተላልፈናል።

ጥያቄ፦
ኢትዮጵያ ውስጥ የቤተክርስቲያን ንብረትና ታሪካዊ ቅርሶች እየጠፉ፣ የሃይማኖት መሪዎችና ምእመናን ግፍ እየተፈፀመባቸው መሆኑን እንሰማለን፣ እናያለን። ይህን ን ሁኔታ ለማስተካከል ቅዱስነትዎና የቤተክርስቲያኒቷ መሪዎች ምን እቅድ ይዛችኋል? በውጭም ላለው ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ወገናችን ቅዱስነትዎ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ።

መልስ፦
በአበው ልቡና ተዘርቶ በአሪት በቅሎ በወንጌል ከፍተኛ ፍሬ ይሰጥ የነበረው ተዋህዶ ሃይማኖታችን፣ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ታሪካዊ ቅርሳችን፣ መሰረታዊ ድን በራችን፣ የት መጪውን የሚናገሩ፣ የት ነበሩን የሚአወሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ወንድሞቻችን ግፍ እየተፈፀመባቸው መሆኑን የአደባባይ ምስጢር ነው። ከግፋም ብዛት፣ ከመከራው ፅንነት የተነሳ ብዙዎች የሀይማኖት አባቶች ሃይማኖታቸውን እየለወጡ ፈጣሪቸውን እየካዱ ወደሌላ ሃይማኖትም መሄዳቸውን ተረድተናል። ስለዚህም እስቃቂ በሽታ ፍቱን መድኃኒት ለማግኘት ባለፈው ሲኖዶሳዊ ጉባዔያችን ውሳኔ አስተላልፈናል። ውሳኔውም በሥራ ተተርጉሞ ችግሩ በቅርብ ጊዜ እንደሚወገድ እምነታችን የፀና ነው።

ጥያቄ፦
በፓትሪያርክ ላይ ፓትሪያርክ አይሾምም የሚለውን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ህግ በመጣስ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርክ ተብለው መሾማቸውን ያልተቀበሉ የሃይማኖት መሪዎችና ጳጳሳት በእርስዎ የሚመራ በስደት ላይ ያለ ሲኖዶስ እንዳቋቋሙ ይታወቃል። ብዙ አብያተ ክርስቲያ\ናትም በውጭ አገር የእርስዎን አመራር ተቀብለው በመሥራት ላይ እንዳሉ እናውቃለን። እነኚህ በውጭ አገር ኖረው የእርስዎን ሕጋዊነት ተቀብለው ያሉ ቤተክርስቲያናት ስንት ይሆናል? ስም ዝርዝራቸ ውን ማግኘት ይቻላል? ከዚሁ ጋር በማያያዝ አባ ጳውሎስን የሚቀበሉ ጥቂት እንዳሉም ይታወቃል። እነዚህስ ምን ዓይነቶቹ ናቸው? ቅዱስነትዎን ሆኑ አባ ጳውሎስን ስለማይቀበሉ ጥቂት ቤተክርስቲያናት ምን የሚያስተላልፉት መልዕክት አለዎት?

መልስ፦
በኒቂያ፣ በቁስጥንጥኒያ፣ በኤፌሶን ጉባዔ፤ በሦስቱም ጉባዔያት ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዲከበር አንድነትን ለማፅናት ሕገ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጠብቆ እንዲኖር ውሳኔ በውግዘት ተላልፎአል። ስለዚህ ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ የተሰየመውን መቀበል ሕገ ቤተ ክርስቲያንን መጣስ ይሆናል። ውግዘቱንም እን ደሻረ ይቆጠራል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የግል ክብርን ለመሻት በሚአደርጉት ደካማ አስተሳሰብ በአን ድ በክርስቶስ ደም የተመሰረተችውን ቤተ ክርስቲያን በመለያየት ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን እርስ በርስ ከመወጋገዝ መከባበርን፣ ከመራራቅ መቀራረብን፣ ከመቻቻት መመካከርን የመሰለ ከፍተኛ ጸጋና በረከት የሚገኝበት መሆኑን አውቀው፤ አንድነታቸውን አጽን ተው፤ሃይማኖታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ መልክታችን እናስተላልፋለን::

> ይህ ቃለ መጠይቅ የተካሄደው በላንዳፍታና በኢትዮጵያ ሪቪው መጽሔቶች ነው።

## የሕሊና እስረኞችን የማስፈታት ዘመቻ አስተባባሪ ግብረ ኃይል

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ መንግሥት በሰብአዊ መብት ረጋጭነት ከማንኛውም አገር በቀደምትነት እየታወቀ መምጣቱን አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቅርቡ አስታውቋል። በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የሕሊና እስረኞች በየእስር ቤቱ እየማቀቁ ይገኛሉ። ብዙዎቹ የሕይወት ዘመናቸውን ለሰብዓዊና ህዝባዊ አገልግሎቶች ያዋሉ እንደ እውቁ ፕሮፌር አሥራት ወልደየስና ዶክተር ታየ ወልደ ሰማያት ያሉ ይገኙበታል። እነኚህን የሕሊና እስረኞች ወገኖቻችንን ጥር 1 — 2 ቀናት 1991 ዓ.ም. (ጃንዋሪ 9 — 10, 1998) በዓለም ዙሪያ በሚደረግ ጸሎት እንዲታሰቡ ለሃይማኖት መሪዎችና ድርጅቶች ጥሪ ተላልፏል። እርሰም የፀሎቱ ተካፋይ እንዲሆኑ በሕሊና እስረኞች ወገኖቻችን ስም ጥሪ እናቀርባለን።

አክብሮት ከተመላበት ወገናዊ ሰላምታ ጋር

ዶ/ር እምሩ አሰፋ

የሕሊና እስረኞችን የማስፈታት ዘመቻ አስተባባሪ ግብረ ኃይል

# አዲሳባና አዲስ አበቤው – ባዲሳብኛ

(ከጦራ ጦጦራ)

አዲሳባ! ... ሁሉም ነገር አለ።

ሁሉም ደግሞ የየራሱ ድንበርና ወሰን አለው። ሁሉም የየራሱን ክልል መስርቷል። የራሱን ተራ፣ የራሱን በረንዳ ... የየራሱን መንደርና ሰፈር ቆርቁሯል።

የራሱን ቀጠና ዘርግቶ፣ ቀበሌ አበጅቶ፣ ራሱ ለራሱ የቤት ቁጥር ሰጥቶ ... ለራሱ ራሱ ስም አውጥቶ! ... የማንነት መታወቂያ አዘጋጅቶ ... በየተራው በየበረንዳውና በየሰፈሩ ከትሟል።

አውቶቡስ ተራ፣ ቦምብ ተራ፣ በርበሬ ተራ፣ በግ ተራ ... አትክልት ተራ ... ሶማሌ ተራ ... ምናለሽ ተራ፣ ሚሊቴሪ ተራ፣ አጠና ተራ፣ ሣጥን ተራ ... ዶሮ ተራ፣ ሸማ ተራ፣ አሸዋ ተራ ... ጉማ ተራ፣ ሳር ተራ፣ ፍራሽ ተራ፣ ሞድ ተራ፣ ጫት ተራ ... እ .. ቤ..ት! የተራው አበዛዝ! ... ምን ቢበዛ ግን ሁሉም የየራሱ ድንበር፣ ክልልና ወሰን አለው። እርግጥ ነው! ... አንዳንዶቹ "ተሮች" እንደስማቸው የስማቸው የሚገኝበት ... የሚሸጥበትና የሚገበይበት ላይሆን ይችላል።

ሶማሌ ተራ፣ ሚሊተሪ ተራና ቦምብ ተራ ... ያሸረጡ ሶማሌዎች ውር ውር የሚሉበት፣ "ፋቲክ" የለበሱ ወታደሮች 'ጃ! ኧኽ!' እያሉ የሰልፍ ትርዒት የሚያሳዩበት! ... የሚፈነዱ ቦምቦች በየአይነቱ የሚኮለኮሉበትና ... የሚቸበቸቡበት "ተራ" አይደለም። አዲሳባ! ... ሁሉም ነገር አለ። ሁሉም ታዲያ የየራሱ ጓሮና በረንዳ አለው።

እህል በረንዳ፣ ቅቤ በረንዳ፣፣ ጉጀም በረንዳ ... አብዶ በረንዳ ... ጨው በረንዳ!

አዲሳባ! ... ሁሉም ነገር አለ። እናም ሁሉም የየራሱ መንደርና ሠፈር አለው።

ጣልያን ሰፈር፣ ተረት ሰፈር፣ አርመን ሰፈር፣ ቶሎሳ ሰፈር ... ኮንጐ ሰፈር ... ወላሞ ሰፈር ... ወርቁ ሰፈር ... አደሬ ሰፈር ... አዲሱ ሰፈር ... ወሎ ሰፈር!

አዲሳባ! ... ድንበር ያልገደበው፣ ወሰን ያልከለለው ... አጥር ያልጋረደው፣ ችካል ያልወሰነው አንድ ነገር ብቻ ነው። ወሬ! ... ያዲሳባ ንጉሥ– አቤቶ ወሬ!!

ያዲሳባ ወሬ– በተራና በረንዳ ... በሠፈርና መንደር ያልተከለለና ያልታጠረ ነው። ሁሉም ቦታ አለ። ያዲሳባ ወሬ– ሁሉም ሰፈር ሰፈሩ ነው። ... ሁሉም በረንዳ በረንዳው ... ሁሉም ተራ ተራው ... ሁሉም መንደር መንደሩ ነው።

ያዲሳባ ወሬ! ... ከሁሉም ጋር አለ። ሁሉንም ሆኖ! ... በሁሉም ሥፍራ ... ከሁሉም ጋራ!

ያዲሳባ ወሬ! ... ሁሉንም ነው። እንደስሜቱ፣ እንደምኞቱ ... እንደብጤቱ ... እንደአምሮቱ ... እንደየፍላጐቱ ... እንደእምነቱ፣ እንደየግምቱ ... ሁሉንም ነው። እንደሁሉም።

ይሽጣል! ... ይለውጣል! ... ይገዛል! ያስማማል! ... ያሻሽጣል ... ነጋዴም ደላላም ነው ያዲሳባ ወሬ።

ይታዘዛል፣ ያመጣል፣ ይቀዳል ... ይጠጣል ... ያስጠጣል! ይደግማል፣ ይጨልጣል! ... ይሰክራል! ያሰክራል ... ይንገዳገዳል! ... ያንገዳግዳል ... አስተናጋጅም ጠጪም ነው ያዲሳባ ወሬ።

ያዲሳባ ወሬ! ... ደስ ይላል። ቀንጆ ነው ያዲሳባ ወሬ። ፋንጋም እንኳ ቢሆን አንዳች መስህብ አያጣውም። ... ዝም ብሎ የደስ ደስ ነገር አለው። ደ ... ስስስስ ... ይላል።

ጉራዳ ጉርድርድም ቢሆን እንኳ ... ያዲሳባ ወሬ አያስቀይምበትም። የደም ገምቦ ነው። ደግሞ አዲስ አበቤው ራሱ ደማም ያደርገዋል። ጉራዳ ጉረድራዳውን ወሬ ውበት አፍስሶ ... ግርማ ሞገስ አላብሶ ... ቁ...ዌ! ቅዱስ ሚካኤልን! ... ሊያውም ከነሰይፉ! ... (ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ)

ያዲሳባ ወሬ! ... ኃጢያተኛ ነው። ያስኮንናል። ያስቀስፋልም። ... እንዲህም ሆኖ ግን ያዲሳባ ወሬ ደስ ይላል። ... እስቲ አሁን የሚያስቀስፍና የሚያስኮንን ነገር ምኑ ደስ ይላል? ... ምኑም!

ታዲያ! ... እያስኮነነም እያስቀሰፈም ... ያዲሳባ ወሬ ደስ የሚል እምኑ ላይ ነው? – እንጃ! ... ብቻ ዝም ብሎ የሆነ ነገሩ ደስ ይላል። ያዲሳባ ወሬ።

"ይገርማል!

"ምኑ?"

"ተፈራ ዋልዋ! በጠና ታሞ ውጪ ሄዷል አሉ።"

"ውጪ? ... የት ውጪ?"

"መካ!"

"ቀጣፊ! ... መካ ለፀሎት እንጂ ... ለህክምና ይኬድበታል?"

"ዝጋ ... ካመኑበት ፀሎትም ያድናል!"

የሣቅ ተራራው ይንቀጠቀጣል! ... ፈገግታዎች ይናዳሉ! ...

"ልክ ነው! ... በፀሎትም ይዳናል! ... እየሱስ ራሱ በኔ ያመነ ይድናል ብሎ የለ?"

"ታዲያ! ... እየሱስ መካ ምን ይሰራል? ... ባይሆን ኢየሩሳሌም እንጂ! ..."

"አሃ!? ... ነቢዩ መሐመድ አሉ አይደል?"

"ይኑሯ!! ... በኔ ያመነ ይድናል ያለው እየሱስ እንጂ ነብዩ መሐመድ አይደሉም።"

አ ኡዝቢላህ! ... ስታፍሩላህ! ... አቦ "አፉ" በሉኝ

ያዲሳባ ወሬ፦ በቃ ይኸው ነው። እንዲህም ሆኖ ግን ደስ ይላል። ክፋም ቢሆን ያስከፋል እንጂ ለክፋት አይሰጥም። እንዲያም ሆኖ ግን ደስስስ ይላል። ... ያዲሳባ ወሬ። – ታድሎ!

ያዲሳባ ወሬ– ሲያሰኘው ንጉሥ ነው። ይሾማል፣ ይሽራል! ... ይሰቅላል! ... ያወርዳል።

"የበረከትን ነገር ሰማችሁልኝ?"

"በረከት ... በረከ ... ት"

"በረከት ሰምያን ነዋ! ... ፈነገሉት አሉ። ...

ከኖታው አንስተውታል፤ ኧረ እንዳውም አስረውታልም እየተባለ ይ..ወ..ራ..ል"

"ምክንያቱስ?"

"ኧረግ! የኢህድን ቀኝ እጅ ነው የተባለለቱ ሰውዬ!? ..እ..ን..ዴ!? ... መጀመሪያውኑ ታዲያ በየት በኩል አድርጎ አማራ ሆነ?"

"በገርል ፍሬንዱ!"

ሣቅ! ... ቁጣ! ... ንዴት! ... ፈገግታ! ... ቁጭት ... ትዝብት ... እንደገና ሣቅ ... እንደገና ቁጣ ... እንደገና ቁጭት! ... (እናንተ!? ... እንደገና የሚባል ስም መኖሩን ታውቃላችሁ? ... ብቸና ውስጥ እንደገና የሚባል ሰው አውቃለሁ። ታዲያ የአባቱ ስም ማን መሰላችሁ? ... መጣ!)

ያዲሳባ ወሬ! ... ብርቱ ነው። ጠንካራ! ... አቀበት ቁልቁለት የማይበግረው! ... ጋራ ሸንተረር የማያግደው ... ቢሄድ አይታክት! ... ቢነጉድ አይደክም! ... ተጓዥ ነው ያዲሳባ ወሬ! ሃጅ! ... መንገደኛ! ... ይሄዳል፣ ይነጉዳል፣ ይዘልቃል! ...

"ኦሮሚያ ክልል የሆነውን ሰምቼ ..."

"ደሞ እዛ ምን ተፈጠረ?"

"ለወዶ ዘማቾች ገለፃ ሲደረግላቸው! ... አንዱ ዘማች ተነሣና! ... ሻዕቢያዎች በመልክም ይሁን በአቋም ከእኛ ጋር አንድ ናቸው። ... ታዲያ ጠላቴን በምን ለይቼ ነው የምተኩሰው? ... ብሎ ጠየቀ አሉ።"

"እና ምን ተመለሰለት?"

"ምንም ችግር የለም! ... ትግርኛ ወደሰማህበት ሁሉ መተኮስ ብቻ ነው! ... በግራም በቀኝም ከፊትም ከኋላም ብቻ አንተ ቋንቋውን ወደሰማህበት ተኩስ!"

የሣቅ ጋራው ይናዳል! ... ፈገግታዎች ይበናሉ። ያዲሳባ ወሬ! ... አይነ ሰፊ ... ጆሮ ብዙ ነው። ጓዳ ጎድጓዳውን ዘልቆ ያያል! ... ግንብ በርቅሶ ግድግዳ ምሶ ያዳምጣል ... በዳበሳ ያውቃል። በጠረን ይለያል። ... ኮርኒስ ቀዶ ብርድልብስ ገልጦ ... በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ ክር ሲገባ ... ሲ.. ጠ..ል..ቅ! ያያል። ያዲሳባ ወሬ።

"ይ...ቺ! ... የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ጉዳይዋ! ... እሷ ሴትዮ ግን ምን መሆኗ ነው? ... ለኤርትራ መወገኗ ይሆን?"

"ተዋት ባክህ! ...ተደርሶባታል!"

"ምኑ?"

"ው...ይ! ...አልሰማህም?"

"ምኑን?"

"የኃይሌ መርቆርዮስ! ...እንትትኑ ናት አሉ!"

"ባ...ባጀሌው! ... ጉድ...ጉድ! በምን ታወቀ? ... ማነው ይሄን ጉድ ያፍረጠረጠው!?"

"ቢቢሲ"

"ቲች! ... እኔ ደሞ እውነት መስሎኝ!"

"ነውና!"

"ኧረ ወደዛ! ... ደሞ አንተን ብሎ ቢቢሲ አዳማጭ! ... ኢቬሬዲ!!"

ያዲሳባ ወሬ! ... የራሱ መዝገበ ቃላት አለው። ይፈታል ይገልፃል! ... ያስረዳል! ... ያብራራል። "ኢቬሬዲ" – ዘጠነኛን ክፍል ማለፍ የተሳነው። ቀለም የማይዘልቀው ደደብ! ... ይለዋል የአዲስ አበቤው መዝገበ ቃላት! መቸስ የአዲስ አበቤው 'ዲክሽነሪ' ከነዌብስተር አይተናነስም። ከቃሉ ፍቺ በተጨማሪ ስዕላዊ መረጃም ያክልበታል። ... እናም ኤቬሬዲ ባትሪ ድንጋይ ላይ ያለችዋንና በ9 ቁጥር ውስጥ መሹለክ የተሳናትን ድመት ያስቀምጣል።

ያዲሳባ ወሬ! ... ሙሻዘር ነው። አግቦኛ! ... ፌዘኛ! ይተርባል! ... ይሸሙራል! ... ይሸረድዳል!

"የሚገርም እኮ ነው!"

"ምኑ?"

"የደቡብ ዘማቾች አሉ የተባሉት!"

"ምን አሉ ባክህ?"

ሣቅ ያፈተልካል! ... ፈገግታ ይሾልካል! ... ይኸው ነው ያዲሳባ ወሬ! ... ወሬው አልቆ ገና ወሬ ሳይሆን ድንገት መሀል ላይ ሣቅ ያመልጣል! ... ጥርስ ያገጣል! ... በቃ! እንዲሁ ነው ያዲሳባ ወሬ።

"እሺ ባክህ! ... ምን አሉ የደቡብ ዘማቾች?"

"የተነሱት ከዛው ከደቡብ ነው አሉ። ... ወደ ጦርነቱ ቦታ! ... ከደቡብ ማፍ! ... ወደ ሰሜን ማፍ! በመኪና ተጭነው ቢጓዙ! ቢጓዙ ... ቢሄዱ ቢሄዱ አልደረስ አላቸው። ባድመ ራቃቸው ... ይሄኔ ምን እንዳሉ ታውቃላችሁ?"

"ም...ን! አሉ?"

"እ..ን..ዴ! ይሄ ሁሉ የኛ መሬት ነው? ... ካሁን በኋላስ ለነገር ፍለጋ ካልሆነ በቀር መጓዝ የለብንም! ... እስቲ አሁን የኢትዮጵያ ድንበር እዚህ ድረስ እንኳ ቢሆን በቂ አይደለም!? ...አሉልሃ!"

"ዛላንበሳ ደርሰው ነው እንዲህ ያሉት?"

"ወልዲያ!"

ሣ...ቅ!! ... ወፍራም! ቀጭን! አጭር! ረ..ጅም ሣቅ! (እኔ የምለው? የሣቅ ጠይም! የሣቅ ጥቁርና ቀይ ዳማ ለምን የለውም!? ...ሲያናድድ!)

ያዲሳባ ወሬ! ... መንግሥት ነው ባለሥልጣን! ... ካሰኘው አምባሳደር ይሆናል። በል ሲለው ሚኒስትር! ... ፕሬዚዳንት ሆኖም ያውቃል። ... ኧረ ከዚያም በላይ! ... እግዚአብሔርንም ጭምር።

ያዲሳባ ወሬ! ... ኮሚሽነር ነው። የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን። – ኮሚሽነር።

"እባካችሁ! ... ከእንግዲህ ከኢትዮጵያ የተባረሩ ኤርትራውያን ማለቱ ይብቃ!"

"ለምን?"

"የሄዱት ሁሉ የት እንደገቡ ታውቃላችሁ?"

"አሥመራ ነዋ! ...አሥመራ!"

"እሱን ማን አጣው?...እኔ ያልኩት እዛ እንደደረሱ የገቡበትንና ያረፉበትን ነው!።"

"የት ነው እሱ?"

"አሥመራ ዩኒቨርስቲ!"

"እና!?"

"እናማ የተባረሩ ኤርትራውያን ሊባሉ አይገባም!"

"ታዲያ ምን ትላቸው?"

"ስኮላርሺፕ ያገኙ!"

ያዲሳባ ወሬ! ... ደስ ይላል ... የደስ ደስ አለው። ፉንጋም እንኳ ቢሆን አንዳች መስህብ አለው። ... የደስ ደስ አያጣውም። – ያዲሳባ ወሬ።
ያዲሳባ ወሬ፦ ሁሉንም ነው። እንደሁሉም! ... እንደተርጓሚው! ... እንደመንዛሪው! ... እንደልቡ! ... እንደፍላጐቱ! ... እንደግምቱ! ... ሁሉንም ያስደስታል ያዲሳባ ወሬ። – ለሁሉም።
ያዲሳባ ወሬ፦ ሁሉንም ነው። እንደሁሉም። ያስተክዛል! ... ያስቆዝማል! ... ያወራጫል! ... ያነጫንጫል! ... ያንጫጫል! ... ያፋጫል! ያጋጫል! ... ያገጫጫል! ... እንባ ያስረጫል።

አዲሳባ! ... እህል ቢጠፋ! ... የሚላስ የሚቀመስ ቢታጣ! ... ማን ግድ አለው!?

ለፓስታ? ... ማን አለው ደንታ?!ለገንፎ? ... ማን ሊውል ተወዝፎ?

ለእንጀራ? ... ማን አለው አራራ!?

አቦ! ... ወሬ ውሎ ይግባ! ... ወ...ሬ! ወሬ!... ወሬ! ወሬ! ወሬ! ... ያዲሳባ ወሬ!

"ሰማህልኝ?"

"ምኑን!?"

"አረጋሽ! ... አለች የተባለውን!"

"አ..ረ..ጋ..ሽ!? ... አረጋሽ የክልል አንድ ፀሐፊዋ? ... እኮ ምን አለች?"

"ቂ...ጣ!"

"ማንን?"

"ሰውየውን ነዋ!...መለስ ዜናዊን!"

"ለምን?"

"ተናዳ ነዋ! ...እስር ጊዜ አቋሙን እየለዋወጠ አልጨበጥ ቢላት ጊዜ ... ተናዳ ምን እንደ ቂጣ ትገለባበጣለህ!? ... ቂ...ጣ!! ... አለችዋ!"

"እንዴ!? ... የት ነው ይህን ያለችው?"

"የህወሐት ስብሰባ ላይ!"

"መቼስ አንተ ስብሰባ ላይ ልትገኝ የምትችልበት ተዓምር አይኖርም! ... ከየት ሰማኸው?"

"ከሰማ ሰው!"

"እኮ ከማን!?"

"ምስጢር ነው።

አዲስ አበቤው! ... ላዲሳብኛ ወጉ የጥገና ማዕከል አለው። ያቃናል! ... ያድሳል! ... ይቀባል! ...ያሳምራል! ... ወጉን የከረከሰውን! ... የተጨራመተውን።

"ውሸት! ... አረጋሽ መለስን ቂ...ጣ! ልትለው አትችልም!"

"በምን ተገለፀልህ?"

"ቀድሞ ነገር የህወሐት ስብሰባ በትግርኛ እንጂ በአማርኛ ተካሂዶ አያውቅም።"

"እና!?"

"እናማ! ...ቂጣ በአማርኛ ነው። ... አረጋሽ ደሞ በህወሐት ስብሰባ ላይ በአማርኛ ልትናገር አትችልም። ወይም በአማርኛ መናገሯ የማይመስል ነገር ነው።"

"ቆይ! ቆይ! ቆይ! ... ቂጣ በትግርኛ ምንድንነው የሚባለው!?"

"ቅጫ!"

ሳቅ ይፈነዳል! ... ጥርሶች ይበልጫሉ! ... አ...ቤ...ት! ... ስንት አይነት ጥርሶች አሉ ባካችሁ? ፀአዳ! ... የወየበ! ... የበለዘ ... የተነባበረ! ... ሸራፋው፣ ወላቃው፣ ጉል ጥርሱ! ... ደሞ በጉሉ መሀል ብቅ ጥልቅ የምትል ምላስ! ... አ...ቤ...ት! ጫኙ!? ...ቀ...ይ ነው።

"ታዲያ እኔ ምን አጠፋሁ? ... ወሬው ለኔ ሲደርሰኝ በአማርኛ ተተርጉሞ ይሆናላ! ዋናው ነገር ቂጣ ማለት ቅጫ! ... ቅጫ ደግሞ ቂጣ መሆኑ ላይ ነው።"
እንደገና ሳቅ ይፈርሳል። ... እያስገመገመ! እየተንዷዷ! ... እየተንጓጓ! ... የሣቅ ጋራው ይናዳል። ፈገግታዎች ይበናሉ።
ያዲሳባ ወሬ! ... ውበቱ ግልፅነቱ ነው። ደምግባቱ ... ዲሞክራትነቱ! ... ያልተከለለ ያልተገደበና ያልታጠረ መሆኑ! ... እንደሁሉም ... ለሁሉም ... ከሁሉም ጋራ ... በሁሉም ስፍራ መገኘቱ ነው።

ያዲሳባ ወሬ!... የዘር፣ የኃይማኖት፣ የፆታ... የርዕዮት ልዩነትን አያውቅም። ሁሉንም ነው ... እንደሁሉም ... ሁሉም ጋር ይገባል። ከሁሉም ጋር ይቀላቀላል። ከሁሉም ጋር ይውላል። ሁሉም ጋር ያመሻል። ... ከሁሉም ጋር ያድራል። ... ሁሉን ሆኖ ያነጋል።

ክርስቲያን ነው፦ ያዲሳባ ወሬ ባለክር! ... ባለመስቀል ... ባለማተብ! ... ያዲሳባ ወሬ ሲያሻው ይሰልማል ... ሁሉንም ነው ያዲሳባ ወሬ። ቤተክርስቲያን ይገባል። መስጊድ ይታያል። ... ፀሎት ያደርሳል። ሶላት ያደርጋል።

ፕሮቴስታንት፣ ጆሆቫ ዊትነስ፣ ... ቡድሂስት! ካቶሊክ! ... ታኦይስት! ... ሰባተኛው ቀን! ... ስምንተኛው ... ዘጠነኛው ... አስራ አንደኛው ... ዘጠና ዘጠነኛውም ነው። – ያዲሳባ ወሬ።

ያዲሳባ ወሬ! ሲያምረው ይዳምናል! ... ሲሻው ይወብቃል! ... ያካፋልም ይዘንባልም! ... ጎርፍ ሆኖ ያጥለቀልቃል! ... ሐሩር ሆኖ ላብ ያንዠቀዥቃል።

ያዲሳባ ወሬ! ... ህመም ነው! ... በሽታ! ... ከፉ ደዌ! ውጋት ነው! ነቀርሳ! ... ተስቦ ነው ኮሌራ! ... ጉበት! ... ቁርጥማት! ... ታይፈስ ነው፣ ታይፎይድ ... ማጅራት ገትር! አሜባ! ... በሽታ ነው ያዲሳባ ወሬ።

ደግሞም ኃኪም ነው ያዲሳባ ወሬ! ... ያሽላል! ያድናል! ... ይፈውሳል! ... ይጠግናል! ... ይቀዳሉ! ... ይቆርጣሉ! ... ይጥላሉ! ... ይሰፋሉ! ... ያሽጋሉ። ... ሰርጂን ነው ያዲሳባ ወሬ።

ያዲሳባ ወሬ! ... አርቲስት ነው። አቀንቃኝ! ... ድምፀ ሸጋ አዝማሪ! ... ባለመሲንቆ "ብአልዌራ ዋጣ" ... በዘለሰኛ "ሪትሙ" ... ማሲንቆውን እየገዘገዘ ... በሰላ ስንኙ ይገዘግዛል ...

"ጎጃሜ ቡዳ ነው ብላችሁ ስትሉ
ትግሬን ትግሬ በላው እንግዲህ ምን ትሉ?"

"ላ...ብ!" ... አዲስ አበቤው ከጣራ በላይ ይጮሃል! ... ይግላል! ... ያጋግላል! ... ያሞቃል፣

ያዳምቃል።

አዲስ አበቤው! ... ላዲሳብኛ ዘፈኑ ሃረግ ይመዛል! ... ሆሄ ይደረድራል! ... ስንኝ ይቋጥራል። ... "ያዝ!" ይላል... ግጥም ይሰጣል።

"ለእብደት መድኃኒት ከጠፋ ኤርትራ
ኢሳይያስን እምጡት ይጠመቅ ሸንኮራ!"

"ሳ...ብ! ... ሳ...ብ!"

አዲስ አበቤው! ... ዙርያ ገባውን ይቃኛል! ...
እናም ይቀኛል።

"በሰባት አመቱ አንድ ጊዜ ቢዋጋ
አላስቀምጥ አለን ያንኑ እያወጋ!"

"ሳ...ብ! ሳ...ብ!"

"እምበር አስመራዎች ጤፍን አቃለሉ
ሆዳቸውን ነፍቶት በለሱ ቁልቋሉ!"

"ሳ...ብ! ሳ...ብ!"

"ይገርማል እኮ እናንተ?"

"ምኑ?"

"ኢሳይያስ አፈወርቂ! ... ጤፍ የፈረስ ምግብ ነው ብሎ ለኤርትራ ህዝብ ከተናገረ በኋላ የአሥመራ ህዝብ በየቤተክርስቲያኑ ምን እያለ እንደሚፀልይ ሰምታችኋል?"

"ምን ብለው ይሆን የሚፀልዩት?"

"ፈጣሪ ሆይ! ... እባክህ ፈረስ አድርገኝ!"

ያዲሳባ ወሬ! ... ሀዘንተኛ ነው። ሠርገኛም ጭምር! ... ሠርግ ይሄዳል። ልቅሶ ይደርሳል። ያስተዛዝናል። ... ያሸርጣል! ፎጣ ይጥላል! ካፖርት ይደርባል፣ ባርኔጣ ይሰቅላል! ... ድንኳን ይገባል! ... ከንፈር ይመጣል! ከንፍሮው ይዘግናል!... ራስ ይነቀንቃል፣ ንፍሮውን ያደቃል! ... እናም ያኝካል ... ያኝካል! ... በእርጋታ፣ በዝግታ፣ በሹክሹክታ ... ያኝካል።

"ያቺ ነገር ናት አሉ?"

"ይ...ባላል!"

ሁለት ጊዜ ከንፈር ይመጠጣል።

"ይሻለዋል!"

"ምኑ?"

"እዚህ መሞቱ! ... ዛሬ ጊዜ ወደ ኤርትራ ከመባረር እዚችው ክንችር ማለቱ ይሻላል! ... በስንት ጣዕሙ!"

"ምነው አባቴ?"

"ባታውቀው ነው ልጄ!"

"ማንን?"

"ከኢሳይያስ ኤድስ መሻሉን!"

ንፍሮው ይቆነጠርለታል ... ጥርስ ያኝካል! ምላስ ያላምጣል! ... ወሬውንም ጭምር! ... ያኝካል፣ ያላምጣል! ... በእርጋታ፣ በዝግታ ... በሹክሹክታ—

"ልጄ! ... የኢሳይያስን ድርጊትና ባህርይ ብታውቅ ... ኤጭ! ኤድስ ምንድናት? ትል ነበር!"

"ያውቁታል ማለት ነው እርስዎ?"

"እብድን ማን ያጣዋል ብለህ? ... እንዳውም የዘር ነው!"

"ምኑ?"

"ዕብደቱ! ... ወንድሙም ያው ነበር! ... መቸስ ያ! ጠጅ ቤት ስንቱን ጉድ አሳይቶናል!"

"የ ...ቱ?"

"የናቱ ጠጅ ቤት! ... ጠጅ ነጋዴ ነበረች እናቱ!"

ያዲሳባ ወሬ! ... ይመዝናል ... ይገምታል! ... ይለካል፣ ይመትራል።

"እውነታቸውን ነው አቦይ! ... አሥመራ ሄዶ በውርደት ከመሞት ... እዚችው በእግዜሩ በሽታ መገላገል ፅድቅ ነው"

ከኢትዮጵያ የተባረሩ ኤርትራውያን! ... ከሁለት ያጣ ስለመሆናቸው ይተረካል! ... የቆጡን እናውርድ ብለው የብብቱን ስለመጣላቸው ይተረታል።

"ከዚህ ከተባረሩት አንዱ ... ኢንጂነር ሰርፀ ተገደለ! ... ኢሳይያስ ራሱ ነው 'አስቁት' ብሎ ያስረሸነው!"

"ጉ ...ድ!"

"ንግሥት ጊላ አሥመራ ከደረሰች በኋላ ራሷን በገመድ አንጠለጠለች!"

"አ ...ቤ ...ት! ... ለመሆኑ ንግሥት ጊላ የቷ ናት?"

"ምነው እንኳ! ... ይህቺ! ... ከዋቢሸበሌ ሆቴል ፊት ለፊት ያለችዋ!? ባለቡናቤቷ!"

"ጉ ... ድ!"

ያዲሳባ ወሬ! ... ያዝናል! ይተክዛል! ... የእንባ ከረጢት ይበጣል! ... ያስነባል!

ያዲሳባ ወሬ! ...ያስፈግጋል! ...የኮሚክ ዕጢዎችን ይኮረኩራል። ያስቃል! ያጫውታል። ... ያራፍዳል! ... ያዋውላል ... ያማሻልም ... ኧረ ያናጋልም ...ያዝናናል።

"ጐንደር የሆነውን ብነግራችሁ በሳቅ ነው የምትፈርሱት"

"ምን ሆነ?"

"እንግዲህ እዛ ጎንደር ከአማርኛ ይልቅ ትግርኛ ተናጋሪው ይበረክታል አሉ። ...ኤርትራውያን ይውጡ ሲባል ጊዜ ማንን ከማን እንደሚለዩ የተሳናቸው ባለሥልጣናት ...እንዳለ ትግርኛ ተናጋሪውን በሞላ ሰብስበው ወደ አዲስ አበባ ሰደዱት!"

"እንዴ!? ...ለምን?"

"እኛ የናንተን የዘር ሐረግ ስንቆጥርና ስናጣራ አንከርምም! ...ሌላ ብዙ ሥራ አለብን! ... ብለው ነዋ!"

"ታዲያ ለምን ወደ አዲስ አበባ ሰደዷቸው?"

"እዛው ሂዱና መለስ ይለያችሁ! ... ብለው"

የሣቅ ተራራው ይንቀጠቀጣል! ... ፈገግታዎች ይናዳሉ ...

አዲስ አበቤው! ...ክረምቱ አልበገረውም! ...ውርጭና ቆፈኑ፣ ብርድና ዝናቡ ... ካፊያና ውሽንፍሩ ... ከቶም አልተሰሙት!

አዲስ አበቤው! ... ይህን ክረምት የተወጣው— ካፖርት ስለደረበ፣ ጃንጥላ ስለዘረጋ፣ ጓንት ስላጠለቀ ... ምድጃ ስለሞቀ! ... አረቄ ስለጨለጠ ... ሸንኮራ ስለመጠጠ ... ስኳር ድንች ስለገመጠ! ... በቆሎ እሸት ስለጋጠ

አይደለም። አዲስ አበቤው! ... ብርድና ውርጩ ያልበገሩት፣ ቁርና ቆፈን ያልፈተኑት! ... ወሬ ስላለ ብቻ ነው። እሱው ስለሚያሞቀው! ... ወሬ፦ ያዲሳባ ወሬ! ... ያሞቃል! ... ያሟሙቃል!

"የአሥመራ ሊስትሮዎች ... ግልብጥ ብለው ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ!"

"ምክንያት?"

"ምን ሠርተን እንብላ!?"

"የሚጠረግ ጫማ ጠፍቶ?"

"ህዝቡ ሁላ ኮንጎ ጫማ ማድረግ ስለጀመረ ... ማን ሸበጥ ያስጠርጋል?"

ያዲሳባ ወሬ! ... እንዳሻው ነው። እንደሁሉ። እንዳመሉ። እንደስሜቱ፣ እንደብጤቱ ... እንደ ኃይማኖቱ ... እንደግምቱ ... እንደየእምነቱ ... ሁሉንም ነው። – እንደሁሉም።

ባርኔጣ የደፋ፣ ካፖርት የደረበ፣ ከዘራ የጨበጠ፣ ፒፓ የጎረሰ – ቁንጠኛ አዛውንት ሆኖ አደባባይ ይወጣል። – ያዲሳባ ወሬ።

ፀጉሯን እያዘናፈለች! ... ዳሌዋን እያስረገደች! ... ማስቲካዋን በቁንጥ (ቀጭ ... ቋ!) እያደረገች ... በአንደኛው "ፓብ" ውስጥ ልትከሰትም ትችላለች። – ያዲሳባ ወሬ!

"የመሐሪስ ነገር እንዴት ነው? ... ከአገር መባረሩ የጎዳሽ ይመስላል!"

"ለጊዜው!"

"እንዴት ለጊዜው?"

"ተመልሶ መምጣቱ አይቀርማ!"

"በምን ተአምር?"

"በተዓምር ሳይሆን በዘመቻ! ... በዘመቻ መልክ ተመልሶ ይመጣል። በሽሬም ይሁን በቡሬ! ብቻ መምጣቱ አይቀሬ ነው!"

"ኡ ...ኡ ...ቴ! ... ከሻዕቢያ ጋር? ... በድል አድራጊነት?"

"ኖ! ኖ! ... በምርኮኛነት!"

"ም ... ን!?"

"አዎን! ... እጄን ሰጥቼም ቢሆን ተመልሼ እመጣታለሁ! ... ካንቺ ውጪ ህይወት አይኖረኝም ብሎኛል!።"

አዲሳባ! ... ወሬ ባይኖር ምን ይውጣት ነበር? ... ምንኛ ባስቀየመች! ... ምንኛስ በደበረች ኖሯል? ... ያዲሳባ ... ወሬ ነው ውበቷ ... ወሬ ነው ድምቀቷ ... ወሬ ነው ታቦቷ! ...

"ኸረ አንድ ወሬ ሰምቼ! ... እኒህ የሸዋ ዳቦ ባለቤት ... የዘፍኮ ህንፃ ባለንብረት ... አቶ ዘሙይ የሚባሉት ኤርትራዊ ከበርቴ! ... ከአሜሪካ መጥተው መንግሥት አስሯቸዋል እየተባለ ይወራል!"

"ሥራም አላጡ! ... ለምን ይመጣሉ?"

"እሃ!? ... ንብረታቸውስ? ... ያ! ሁሉ ንብረት ይቅለጥ ታዲያ?"

"ለምን ይቀልጣል!? ... ከኤርትራና ከአሰብ የተፈናቀሉ የኛ ወገኖች! ... እነሱ በደንብ ይጠበቁላቸዋል!"

ሣቅ ይናዳል! ... ፈገግታ ይበናል!

"ምን ነካችሁ? ... ሰውየው አሜሪካ ቀሩ አልቀሩ ... ታሰሩ አልታሰሩ! ... ሚስትና ልጆቻቸው እንደሁ ያሉት እዚህ!"

"እና ቢኖሩስ?"

"ሚስትየዋ! ... ኢትዮጵያዊ ናቸዋ!"

"ልክ ነው! ... ሊያውም ጎጃሚ!"

"ማ!? ... የዘሙይ ሚስት? ... ጥርት ያሉ ወሎዬ!"

ያዲሳባ ወሬ! ... አንዳች መግነጢሳዊ ኃይል አለው። ቀልብና ስሜትን ይገዛል። ጆሮ ያስጥላል ... አይን ያስፈጥጣል ... አፍ ያስከፍታል ... የበሽተኛውንም እንኳ ቢሆን! ... ህመም አልጋ ላይ የጣለውን! ... የሚያጣጥረውን ... ልሣኑ የለገገውን ሳይቀር ... በጣዕርም ቢሆን ያናጋራል ... ያስመሰክራል፦

"እ ...ህ! ... ኡህ ...እህ! ..."

"ውይ አፍር በበላሁ! ... ስንጯጯህ ቀሰቀስንህ?"

"እ ...ህ! ... ኡህ ...እ!"

"አጥሚቱን ልስጥህ? ... ትንሽ እንኳ አፍህ ላይ ብታደርግ! ... ከትናንት ጀምሮ እህል የሚባል አልቀመሰም!"

"እህ! ...እህ...እህ!"

"ከበሽታው ይልቅ ያደከመህ እኮ ረኃቡ ነው! ... ካልበላህ ደሞ መድኃኒቱ አይሰራም!"

"እህ! ... እህ! ... መ..ን..ዜ!"

"ም...ን!? ... የምን መንዜ?"

"እህ! ...እህ! ... የዘሙይ ሚስት! ...መ..ን..ዜ ናቸው እህ! ...እህ! ..."

ያዲሳባ ወሬ!...አስማተኛ ነው! ምትሀተኛ!...የታመመ ያስነሳል!...የተኛን ይቀሰቅሳል! ...

ያዲሳባ ወሬ ... ሁሌም እንደደራ! ሁሌም እንደኮራ ነው። ጅንኑ! ... ቀብራራው ያዲሳባ ወሬ ጭርታን አይሻም ... እርጭታን አይወድም! ... ፀጥታን አይመርጥም! ... ሁሌም ሞቅ ደመቅ እንዳለ ነው።

ያዲሳባ ወሬ! ... ይነግዳል! ያናግዳል! ... ያስነግዳል። ያተርፋልም! ... ያከብራልም። ... ቁምጣ ጨው ያስገዛል። ኩንታል ጤፍ ያሸምታል። ... ፈረሱላ በርበሬ ያስጭናል። ... ዘንቢል ያስቋጥራል። ቡሀቃ ያስሞላል።

"ከፋም ለማ! ... ከአሁኑ ገዝቶ ማስቀመጥ ይሻላል።

"ምኑን?"

"ሁሉንም! ... ወደ ሆድ የሚገባውን! ... ለቤት የሚበጀውን! ... ሁሉንም ቢሆን!"

"ምነው!? ... ምን መጣ!?"

"ጦርነቱስ!? ... ኋላ የሁሉም ነገር ዋጋው ሰማይ ቢነካስ? ... ማን ያንጋጥጣል? ከነአካቴው እልም ቢልስ? ... ማን ይቆራመዳል?"

አዲስ አበቤው? ... ያብራራል! ይዘረዝራል! ... ያስረዳል፣ ያስታውቃል! ... ያስጠነቅቃል!
ያዲሳባ ወሬ!... መሐረብ ያስፈታል! ዶልቼ ያስፈለቅቃል። ... በርሜ ያስወጣል፦ ሬብጣ ያስመዝዛል! ... "ቡክ" ያስጨብጣል፦ ወደ ባንክ ያስሮጣል።
ያዲሳባ ወሬ! ... ይሸጣል! ... ይገዛል! ያጋዛል! ... ያስማማል ... ያፋርሳል፦

"መኪና በርካሽ ዋጋ አገኘሁ!"
"ምን አይነት?"
"ማንትስ የምትባል!"
"በስንት?"
"በምንትስ!"
"ትቀልዳለህ!? ... ይሄማ ወድቆ አገኘሁ እንጂ ገዛሁ አይባልም!"
"ለምን መሰለህ? ... መኪናዋን የሸጠልኝ ሰውዬ ኤርትራዊ ነው!"
"በል! በል! በል! በል! ... እንደዛማ ከሆነ ኪሳራ ነው! ... መኪና ጣለልኝ ሳይሆን ገንዘቤን ጣልኩት ብትል ይሻላል!"
"ሻጭ ኤርትራዊ ስለሆነ?"
"እንክት!"

አዲስ አበቤው! ... ምክንያት ይደረድራል! ... አክርማ ይሰነጥቃል! ... ሰበዝ ያርሳል! ... በቃ! ... ከዛ መስፋት ነው! ... የወሬ ቀልቢጥ! ... የወሬ ሙዳይ! ... መውጋት! መንቀል! ማስገባት፣ ማስወጣት! መስፋት! ... ወሬ።
ስፌቱ ብዙ ነው። እንደሰበዙ! ... እንደአለላው ከለር! ... እንደአክርማው! ... እንደወስፌው ይወሰናል። አይነቱ የሚለየው ቁርጡ የሚታወቀው! ... ስፌቱ ሲያበቃ ነው። ... ወይ አገልግል ይወጣዋል። ወይም ሌማት ሆኖት ያርፈዋል ወይም እርቦ፣ ወስከምበያ፣ ዕንቅብ፣ ... ከነዚህ አንዱን ሊሆን ... ይችላል። – የወሬው ስፌት!

"ትዝ ይልሃል ስድሳ ሰባት? ኤርትራዊ ሁላ ከመኃል አገር ነቅሎ ወደተስፋይቱ ምድር የተመመበት ዘመን!"
"እንዴታ! ..."
"ያኔ! ስንቱ መሰለህ የከሰረው? ... በርካሽ ያገኘ እየመሰለው ... ከኤርትራውያኑ ንብረት የገዛ ሁሉ ደም አልቅሷል። ... የገዛው መኪና ሞተሩ ቶዞ እየሆነበት! ... መኪና ሳይሆን ቆርቆሮ ታቅፎ የቀረው ስንቱ መሠላችሁ!?"
"ልክ ነው! ... ሞተሩ ውስጥ ጨው እየጨመሩበት ነው አሉ የሸጡት! ...እ..ቤ..ት! ተንኮል!!"

ያዲሳባ ወሬ! ... ጠርጣሪ ነው! ...ቆ...ቅ!
"ልጆች አባካችሁ ይሄን የማብሰያ ጋዝ ስትገዙ እየተጠንቀቃችሁ!"
"አባዬ! ... ምነው!? ደሞ ምን ሰማህ?"
"...እነዚህ ሰዎች ምናቸው ይታመናል ብላችሁ ነው? ... ቤንዚን ቢቀይጡበትስ?"
ያዲሳባ ወሬ! ... ልጆችን ያስፈራል! ... ያስደነግጣል! ያሸብራል! ያስደነብራል! ...ያፈዛል! ያቃዣል! ...
"ምንም ነገር ቢሆን! ... ዳቦም ቢሆን!
"ሙዝም ብርቱካንም ቢሆን!"
"ከረሜላም ቢሆን እንዳታነሱ!"
ያዲሳባ ወላጅ! ... ልጆቹን ያስጠነቅቃል።
"አባዬ! ... ፍራንክስ?"

አዲስአበቤው ህፃን – ወላጁን ይጠይቃል! ... ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ... ... ... ...

አዲስ አበቤው! ... ወሬ ያውቅበታል። ወሬውን በአሽሙር ይሞርደዋል። በፌዝ ያስላዋል። በምፀት ያሾለዋል።

"እናንተ!? ... ምነው ጦርነቱ ዘገዩ!? መለስ ምን እየጠበቀ ነው?"
"ሻዕቢያ ደሴ እስክትደርስ!"
"ምን!?"
"ልክ ነዋ! ... መለስ ከዚህ ቀደም የተናገረውን ረሳሽው?"
"ምን ብሎ ነበር?"
"ተቃዋሚዎችን! ... ግማሽ መንገድ ድረስ ሄደን እንቀበላቸዋለን! ..."
"እና!?"
"እናማ! ... ሻዕቢያ ያለችው ገና ባድመ! ... ግማሽ መንገድ የሚባለው ደሴ ስትደርስ ነው"

ሣቅ ይዳምናል ... ፈገግታ ያካፋል።

አዲሳባ! ... ማህፀኗ ለምለም ነው። የተቀደሰ። ... የተባረከ። በየሴኮንዱ ትፀንሳለች። በየደቂቃው ትወልዳለች። – ወሬ!
አዲስአበቤው! ... ወሬውን ገና በሙቅትላነቱ ይታቀፈዋል። ... ያጠበዋል! ... ይመግበዋል! ... ይንከባከበዋል! ... ያወፍረዋል፣ ያደልበዋል።
ያዲሳባ ወሬ! ... ከናቱ ካዲሳባ ማህፀን ተወልዶ ... በአዲስአበቤው ልዩ ፍቅርና ክብካቤ ያድጋል! ... ይመነደጋል።
ያዲሳባ ወሬ! ... ቅመም ነው! ... ውበት ነው! ... አዲሳባ! ... ያላዲሳባ ወሬ ጨለማ ናት! አዲስ አበቤው! ... ያላዲሳባ ወሬ ጨገጎታ ነው!

ያዲሳባ ፍቅር፦ ያላዲሳባ ወሬ አያከንፍም። ያዲሳባ ውስኪ፣ ጠጅና አረቄ – ያላዲሳባ ወሬ ከጉሮሮ አይወርዱም።
ያዲሳባ ክትፎ፣ ሎሚና ብርንዶ! ... ያላዲሳባ ወሬ አይቆረጡም! ... አይዋጡም።
ያላዲሳባ ወሬ! ... ሽንኩርቱ አይላጥም! ... ማስቲካውም አይላመጥም!
ያላዲሳባ ወሬ! ... ገበያ አይደራም! ፖኞሮ አያኮራም! ... ቪላ አያመፃድቅም! ... ልግስና አያፀድቅም! ... ማጣት አያስደንቅም! ... ማግኘት አያስፈነድቅም።

አዲሳባ! ... ወሬ ነው ውበቷ። ... ወሬ ነው ድምቀቷ! ... ወሬ ነው ታቦቷ!!

# የመከላከያ ኃይላችንን ለማሽመድመድ የተፈጸመውን ደባ ለማጋለጥ ህወሐት (ወያኔ) ምነውሳ ተለጉመ?

ምንተስኖት (ካዲሳባ)

"በወዳጅነት እንሰንብት" የሚል አባባል ከፖለቲካው ስንክሳርና ውስብስብ ትርምስ ፈንጠር ላሉ ወገኖች ካልሆነ በቀር "ፖለቲካ ... ፖለቲካ ..." ለሚጫወቱ የዕለት ተዕለት ዜማቸውም "ፖለቲካ" ለሆነ ከቶውንም አይሰራም። በፖለቲካ ዓለም ዘላቂ ወዳጅነትም ሆነ ዘላቂ ጠላትነት እንደሌለ ስናይ የፖለቲካው ጠበብት በግልፅ የሚያወሱት ሀቅ ትክክለኛነቱን የበለጠ ያረጋግጣል። ፖለቲከኞች በወዳጅነት ፀንቶ መኖር በወዳጅነት መዝለቅና በወዳጅነት ማርጀት አልፈጠረባቸውም። ደግሞም አልታደሉም። ማለዳ የኢኮኖሚ፣ የትምህርት፣ የመገናኛ፣ የንግድ፣... ወዘተ ትብብር ተፈራርመው ስነዱ የተፃፈበት ቀለም ሳይደርቅ በጠላትነት ቢፈላለጉ የአምባገነን ፖለቲከኞች የተለመደ ባህሪ ነውና እምብዛም ላይደንቅ ይችላል።

ፖለቲከኞች ከወዳጃቸው ጋር ማርጀት እንደማይቻላቸው አያሌ አስረጅ ጠቅሶ ማመላከት ቢቻልም፣ የዛሬዋ ኤርትራ መሪዎች አጋሚዶ ይሰኙ በነበረበትና አገር የመገንጠል አላማቸውን ለማሳካት "የትጥቅ ትግል" ያካሂዱ በነበረበት ወቅት ከሱዳን ጋር የነበራቸው ግኙኘነት፣ ከደርግ ውድቀት በኋላም አስመራና አዲስ አበባ ላይ መንግስት የመሰረቱት ወያኔና ሻዕቢያ ለአብነት ይጠቀሳሉ።

ፖለቲከኞች በአንድ ሲያጣፍሩ የሰሩትን ደባ ጀርባ ለጀርባ ሲዘዋወሩ አንዱ የሌላኛውን ገበና ማፍረጥረጣቸውም የተለመደ ጉዳይ ነው። ይህንንም ከኢትዮ-ኤርትራና ሻዕቢያና ወያኔ ንፅፅር መመልከት ይቻላል። ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመድፈር ግዛታችንን በኃይል ከወረረና በንፁሐን ዜጐች ላይ ጥቃት ካደረሰ በኋላ ቀድሞ በወዳጅነታቸው ጊዜ የተፈፀሙ ድርጊቶችን በማጋለጥ ረገድ በሁለቱም በኩል አልፎ አልፎ መጠነኛ እንቅስቃሴ ቢስተዋልም ሻዕቢያ የወያኔን ድርጊት ባገኘው አጋጣሚ ከማሳየት የሚያደርገውን ጥረት ያህል በወያኔ በኩል የሻዕቢያን እኩይ ተግባራት ሙሉ በሙሉ አጋልጦ ለማሳየት ያለው በጐ ፈቃደኝነት የተመናመነ ነው ማለት ይቻላል። ለምን?

በእርግጥ ወያኔ ኢህአዴግ በኤርትራ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሻዕቢያ ይደርስባቸዋል የሚለውን በደል በግዙፍ መገናኛ ብዙሃኑ ያወጋናል። ዓላማው ከጅምሩ የሻዕቢያን እኩይ ተግባር በማመላከት ዲፕሎማሲያዊ ድል ለመቀዳጀት የነበረ ቢሆንም ዛሬ ከዚያ መልኩ አፈንግጦ ለእርዳታ ማሰባሰቢያ ሲባል እንደሚደረግ ተብሎ ያለቀለት ጉዳይ ነው። ህወሐት ተመሳሳይ ድርጊቶችን ብቻ በማውሳት የሻዕቢያን ገበና የሚያጋልጥ ይምሰል እንጂ ሌሎች በሻዕቢያ የተከወኑ አያሌ እኩይ ተግባራትን አፍና ለመያዙ ድርጊቱ ምስክር ነው። ለምን?

ሻዕቢያ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጐቹን በአንድ ፖለቲካዊ ሰንሰለት አቅፎ በስውር ስለመንቀሳቀሱ ወያኔ እንደ አዲስ ግኝት ከውዝግቡ መካረር በኋላ ቢነግረንም ከምስረታው ጀምሮ የበኩሉን ድጋፍና እገዛ ሲያደርግ ለመቆየቱ ከህዝብ የተሰወረ አይደለም። ኢህአዴግ ሻዕቢያ "በኢትዮጵያ ሰላዮችን መልምሎ" ይንቀሳቀስ እንደነበረ ሲናገር ፖለቲከኞች ገበናቸውን የሚገላለጡት ከመንደር ሴቶች ባልተለየ መልኩ ሲጣሉ ብቻ ነው በሚል እሳቤ ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ በግንቦት 1983 አስመራና አዲስ አበባ ላይ የወያኔና የሻዕቢያ መንግስታት በተመሰረቱ ማግስት በተለይ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ለማሽመድመድ የፈፀመው ደባ ሊጋለጥ እንደሚችል በመገመት ጆሮውን አቅንቶ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ህወሐት ኢህአዴግ እንዳችም እንዳላየ እንዳልሰማ ሁሉ ፊትም ፀጥ እንዳለ ዛሬም ዝምታን ዘይዷል። በዚህም ሳቢያ ግንቦት 20 ቀን 1983 "ሸጐሌ" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ወታደራዊ ተቋም ላይ በተደረገ ጥቃት ከ5 ሺህ የማይተናነስ ህዝብ ሲያልቅ "በዝርፊያ ላይ የነበሩ" የሚል ቅጥያ የተበጀለት ጉዳይ ከመወሳቱ በቀር ሌቦችም ይሁኑ ዘራፊዎች (በቦታው የኢህአዴግ ወታደሮች የነበሩ መሆኑንና ድርጊቱንም በዝምታ መመልከታቸውን ያስታውሷል) ለዚያ ሁሉ ህዝብ እልቂትና ለተቋሙ ውድመት ተጠያቂው ማን እንደሆነ የተሰጠ መግለጫ የለም። በድርጊቱ ተጠይቆ ለፍርድ የቀረበም አልታየም። ይህ በሆነ ሳምንት ጊዜ በቀድሞ ወታደሮች የተመካኘውና ከ300 በላይ ሰዎች ያለቁበትና ብዙዎች የተጐዱበት (የበቅሎ ቤት) ፍንዳታ በተቀነባበረ መልኩ ለመከወኑ በኮምሮሉ የአውሮፕላን አደጋ ህይወቱ ያለፈው የፎቶ ጋዜጠኛ መሐመድ አሚን ከአደጋ ተከላካይ ሰራተኞች ቀድሞ ካሜራውን አነጣጥሮ መድረሱ የሚጠቁመው ፍንጭ ቢኖርም እነሆ እስከዛሬ ለዚህ ታላቅ ውድመት ተጠያቂ የሆነ ክፍል አልታየም። አልተሰማም። በአገር መከላከያ ላይ የተጣለ በትር እንደዋዛ ታለፈ። የቃሊቲው መሣሪያ ማከማቻም በተመሳሳይ መልኩ ወደመ። ማን ሰራው? ... ዝም። ዝቋላና አምቦም በዚሁ ዙሪያ ይካተታሉ።

የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል ለማሽመድመድ በህዝብ አንጡራ ሀብት የተገዛን መሣሪያ እንደዋዛ ከጥቅም ውጪ ለማድረግና በኢትዮጵያ ላይ ጊዜ ጠብቆ ጥቃት ለመሰንዘር የታለመ የቆየ እቅድ እንደነበር እኒህ ተግባራት ያመላክታሉ። የአገሪቱ ወታደራዊ ተቋማትንና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበትን መሣሪያ አጋይቶ ቀሪው ወደ ሰሜን ሲጓዝ ህወሐት አላየም አይባልም። ፈንጂ በማምከን ስም ከየቦታው የተሰበሰበው ፈንጂ ድምፁ ሳይሰማ ማን እንደዋጠው አለመታወቁም ያጠያይቃል። ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ለማካሄድ ያመቸው ዘንድ ገና ከጅምሩ በወታደራዊ ተቋማት ላይ ያደረሰው ጥቃት መንግስት እስከ ዛሬ ይፋ ካደረጋቸው ብርቱ የአገር ጉዳዮች በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚሰፍር ነው። በወታደራዊ ተቋማቱና በህዝቡ ላይ ለደረሰው ጥቃት ተጠያቂው ሻዕቢያ ብቻ ላይሆን ይችላል። ወያኔ ኢህዴግም ረጅም እጁን እንዳሻው ያስገባ ነበርና። ያም ሆነ ይህ የመከላከያ ኃይላችንን ለማሽመድመድ የተፈፀመውን ደባ ማጋለጥ ዛሬም ከወያኔ ይጠበቃል። ወቅቱ የአገር ጉዳይ ተድፈንፍኖ የሚታለፍበት ጊዜ አይደለምና።

# ማህበራዊ ጉዳይ

## ራስን ፍለጋ

### መስቀል - መስቀል - መንገዶች ሁሉ ወደ ጉራጌ አገር ያመራሉ

በጅማ መንገድ ከአዲስ አበባ 155 ኪሎ ሜትር ተጉዞ ወልቂጤ ከተማ ይደረሳል። የወልቂጤ ከተማ በመስቀል ሰሞን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ደምቃ ያገኛቷል። የመስቀልን በዓል ለማክበር ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ የሚጓዙትን ተወላጆችና እንግዶች በማስተናገድ ትዋከባለች። የከተማዋ ሙዚቃ ቤቶች አዳዲስና ነባር የጉራጊኛ ዘፈኖችን ከፍ ባለ ድምፅ ማጉያ በማስሞዘቅ ራስን የመፈለግ የልብ ትርታን ይቀሰቅሳሉ።

"የወራይ ሰመሌ" እያሉ ይጓዛሉ የጉራጌ ልጆችም። አዲስ አበባ ውስጥ ተጠፋፍቶ የኖረውም ወልቂጤ ላይ ይገናኛል። ከተማዋ ወዳፈራቻቸው ምግብና መጠጥ ቤቶች ጉራ ብሎ ይገባበዛል። ገንዘብ ለማውጣትና ለመጋበዝ ዓይኑን የሚያሽ የለም። ሁሉም አመቱን ሙሉ የተዘጋጀበት ጉዳይ ነው። ሁሉም ነገር ለመስቀል በዓል ነው። ወደ ረኸሙ የወላጅና የዘመድ ምርቃት እስኪደርሱ ድረስ ትንሹ የጓደኛ ምርቃት ወልቂጤ ላይ ይጀምራል። ለሰላም፣ ለፍቅርና ለሥራ ፅዋ ይነሳል።

ከዚያ በኋላ ወደ ትውልድ መንደር ጉዞው ይቀጥላል። ጉራጌው ቤተሰቡን፣ የመከረሚያ ልብሱንና ያጠራቀማት ገንዘቡን እንደያዘ በትላልቅና በትናንሽ መኪናዎች እየበረረ ያልፋል። የመስቀል በዓል በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች በተለያየና በተመሳሰለ መልክ ቢከበርም፣ የሰባት ቤት ጉራጌን አከባበር የተለየ የሚያደርገውና የሚያደምቀው አብዛኛው ተወላጅ ወደ ሀገር ቤት ገብቶ ለምርቃት መብቃቱ ነው። ለመስቀል ሀገር ቤት ገብቶ ያልተመረቀ ጉራጌ ወላጆቹን ያሳዝናል፤ እንደ የግለሰቡም እምነት በመጪው አመት ስራው ላይ የስነ ልቦና ተፅዕኖ ያሳድርበታል። እና የከፋ ችግር ያልገጠመው፣ ወይም የገጠርና ከተማ የግንኙነት ገመዱን ያልበጠሰ ሁሉ ይሄዳል።

በሊስትሮነት፣ በመኪና አጣቢነት፣ በቤት ውስጥ አገልጋይነት፣ በሱቅ በደረቴነትና በመሳሰሉት ትናንሽ የሥራ ዘርፎች ከተሰማሩት ጥሮ አደር ጉራጌዎች ጀምሮ ትላልቅ ሆቴሎች፣ የሸቀጥ ሱቆችና የአስመጪና ላኪነት ፈቃድ እስካላቸው ሀብታሞች ድረስ ሁሉም እንደየአቅሙ ኪሱን ሞልቶ የመስቀልን በዓል ሊያከብር ሀገር ቤት ይገባል።

ከወልቂጤ ወጥቶ የጅማ መንገድን ከፊት በመተው ወደ ግራ ሲታጠፉ አፈራማው ጥርጊያ መንገድ ወደ ዋቢ ወንዝ ያመራል። ዋቢን ተሻግሮ አፋፍ ላይ ሲወጡ የጉራጌ ምድር በእንሰትና ጫት ተክል ተውቦ ይቀበላል። ወደተለያየ አቅጣጫና መንደር የሚወስዱት የሰባት ቤት ጉራጌ ጥርጊያ መንገዶችም ደረታቸውን ገልብጠው ያስተናግዳሉ። ከዚያ በኋላ አቅጣጫውን ወደተወለዱበት ወይንም ለበዓሉ ወደተጋበዙበት መስመር ማቅናት ነው።

የሰባት ቤት ጉራጌ ጥርጊያ መንገዶች ገጠሩን ከከተማው ለማገናኘት በተወላጆቹ መዋጮና ጥረት ከቅርብ አመታት ወዲህ የተዘረጉ ናቸው። የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ይመላለሱባቸዋል፤ የቁንጅት መኪናዎች ገጠሩ መንደር ድረስ ሰተት ብለው ገብተው ጫታቸውን ቁነው ይወጣሉ። ጥንት ከነሸክሙ በእግሩ ሲኳትን የኖረው የጉራጌ ተወላጅ አሁን ይህን ለውጥ ሲመለከት ልቡ በኩራት ይሞላል። ወደ ኋላ መለስ ብሎም የልጅነት የገጠር ህይወቱን በትዝታ ያስታውሳል። ከርቀት ጥቅጥቅ ያለ ደን የሚመስሉት ተክሎች ቀርበው ሲያዩአቸው እንሰትና ጫት ሆነው ይገኛሉ። እያንዳንዱ ጉጆ ጓሮውን ወይንም ዙሪያውን በእንሰትና በጫት ተክል ሞልቶታል። ጉጆዎቹም ሆነ እልፍኞቹ በአብዛኛው አንድ አይነት አሰራር ስላላቸው እንደ አዲስ አበባ ቤቶች ምስቅልቅልነት አይታይባቸውም። ሁሉም አንድ አይነት ናቸው። ወደ ውስጥ ተገብቶ ጓዳ ጉድጓዳው ካልታየ በቀር ቤቶቹ ከውጭ የኑሮ መበላለጥን አያሳዩም። ይህ አንድ አይነት የቤት አሠራር ከየጓሮው ተክል ጋር ተዳምሮ ለገጠሩ ልዩ ውበት ሰጥቶታል።

ጉራጌው ወደ ትውልድ መንደሩ እየቀረበ ሲሄድ የከተማ ጭምብሉን አውልቆ ትክክለኛ እሱነቱን ከውስጡ መፈለግ ይጀምራል። ከተማ ውስጥ ተወልዶ ያደገና ገጠሩን ያላየ ትንሽ ልጁን አስከትሎ ከሆነ ከጥያቄ አያመልጥም።

"ለምንድነው ወደዚህ ጫካ የመጣነው?"

"መስቀልን ለማክበር ነዋ"

"ታዲያ መስቀልን አዲስ አበባ ሆነን ማክበር አንችልም እንዴ?"

"ድምቀቱ፣ ባህሉ፣ ወጉ እንደገጠሩ አይሆንም። በጉራጌ ባህል መስቀል ትልቅ በዓል ነው፡፡ የገጠር ወላጆቻችንና ዘመዶቻችንን የምንጠይቅበት ጊዜ ነው። አንተም ዛሬ አያቶችህን ለማየት በመምጣትህ በጣም ደስ ይላቸዋል። ይህንን ማወቅም መልመድም አለብህ"

ከአዲስ አበባም ሆነ ከሌላ ከተማ ከመነሳታቸው በፊት እንዲህ አይነት ነገሮች ለልጁ ተደጋግመው ተነግረውት ይሆናል። ሆኖም ልጅ ነውና ደጋግሞ መጠየቁን አያቆምም። ደግሞም ከሞቀ አካባቢ፣ ትርምስ ከበዛበት መንደርና በትላልቅ ህንፃዎች ከታጠረች ከተማ ወጥቶ ፀጥ ወዳለ ገጠር ሲገባ ግርታው ሊጨምር ይችላል።

"ታዲያ እኛ ከምንሄድ አያቶቼ እንደሌላው

ቀን አዲስ አበባ፣ እኛ ጋ ቢመጡ ምናለበት?”

“የለም፤ ሌላ ጊዜ እነሱ ሊመጡ ይችላሉ። ለመስቀል በዓል ግን እኛ ነን ወደ እነሱ መሄድ ያለብን”

ጉራጌው ለልጁ ማስረዳትና ማሳየት የሚፈልገው አንድ ዕውነት አለ። ይህን ዕውነት ልጁ ሲያድግና ሲበስል ይደርስበታል። አሁን ለጊዜው ገጠሩና ገጠሬውን ተለማምዶ በአዕምሮው ከቀረፃቸው ይበቃዋል። እያንዳንዱ ጉራጌ ለመስቀል ወደ ሀገር ቤት የሚገባው ራሱን ፍለጋ ነው። ብዙዎቻችን ከገጠር ወጥተን ከተማ መሀል ስንገባና ኑሮ ስንጀምር ሳናስበው እንጠፋለን። የከተማው ሙቀትና ግርግር፣ የዕቃዎች እጥረትና ክምችት፣ የኑሮ ውጣ ውረድና እሽቅድምድም፣ የአየር ላይ ሩጫ፣ የማኪያቶ ቃር፣ የድራፍትና የውስኪው ግሳት፣ የቢሮክራሲው መጠላለፍ ወዘተ ... ራሳችንን እንድንረሳ ያደርጉናል፤ ውስጣቸው ሰምጠን እንጠፋለን። ከገጠር ህይወታችንና ከገጠሬው እኛነታችን ጋር የሚያገናኘንን ክር በጥሰን ከሆነ እንደጠፋን እንቀራለን። ጉራጌው ግን እንዲሁ እንደዋዛ ጠፍቶ አይቀርም። ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ገጠር ገብቶ፣ እትብቱ የተቀበረበትን መሬት ፈልጉና በዘመዶቹ ተመርቆ ራሱን ያገኘዋል።

ጉራጌው ወደ ትውልድ መንደሩ ገብቶ ወደ ወላጆቹ ጎጆ ሲያመራ ገጠሬዎቹ አዛውንትና ህፃናት ከየጓራቸው ወይንም ከየደጃፋቸው ብቅ ብቅ እያሉ በመሳም ሞቅ ያለ የ“እንኳን ደህና መጣህ” አቀባበል ያደርጉለታል። ወጣቶች የያዘውን ዕቃ ተሸክመውለት ወደ ጎጆው ያስገቡታል። ከወላጆቹና ከዘመዶቹ ተገናኝቶ በተዘጋጀለት ምንጣፍ ወይንም በርጩማ አረፍ ከማለቱም የአካባቢው ሰው ሁሉ መጉረፍ ይጀምራል። መሳሳሙ ይቀጥላል። ልጁ ወላጁን እናቱንና የትውልድ አፈሩን አክብሮ በመምጣቱ ይሳማል። እናት እንዲህ አይነት የተባረከ ልጅ በመውለዷ ትሳማለች። የእርድ ቀን ከሆነ ሥጋ፣ የፆም ቀን ከሆነ ደግሞ ቤት ያፈራውን ምግብ ለእንግዳ ይቀርባል። ጠላው ይከተላል።

የአካባቢው ማነቃቂያና ማጫወቻ የሆነው የአረቄ “ማውረድ” ሥነስርዓትም ከዚሁ ይጀምራል። ሁሉም ቤት አረቄ ይወጣል ማለት ይቻላል። ለወትሮው ከእንሰትና ከጫቱ ጉን ለገበያ በመዋል የኑሮ መደጐሚያ ሆኖ ያገለግላል። በእንዲህ ዓይነቱ በዓል ደግሞ ለእንግዳ መቀበያ ይሆናል። ይሁን እንጂ በአካባቢው ባህል መሰረት እንግዳውን ለመቀበል የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ በመጋበዝ ባለቤት መጐዳት የለበትም። ሁሉም እንደየአቅሙ ከጠርሙስ አረቄ እስከ ጠርሙሶች አረቄ በገንዘቡ ይጋብዛል። ጋባዥ ጠርሙሱን ከፍቶ በጉራጌው ወላጆች ይመረቃል። ዝቅ ብሎም የመረቁትን ይስማል። ረዥሙና ለጉራጌው የዓመት ስንቁ የሆነው የምርቃት ስነስርዓትም ከወዲሁ ይጀምራል።

የአካባቢው ሽማግሌዎች ምርቃቱን ያዥጐደጉዱታል።

“ወላጆችን እንዳከበርክ ለአንተም የሚያከብርህ ልጅ ይስጥህ”

“አሜን”

“ዕድሜህን ያርዝምልን”

“አሜን”

“የወላጅ፣ የዘመድ፣ የወዳጅ መኩሪያ ያርግልን”

“አሜን”

“በንግድህ ክበር”

“አሜን”

ምርቃቱ ይቀጥላል። የአረቄ ግብዣውም በየተራ ይቀጥላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጨዋታው ሞቅ ሲልም ማህበራዊ ውይይቱ ይጦፋል። በአካባቢው ሰላም ጉዳይ ላይ፣ በመንገድ ሥራ ላይ፣ በጓሮ ተክሎች ጉዳይ ላይ፣ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ፣ ወዘተ ... ሁሉም በተቆርቋሪነትና በተወላጅነት ስሜት እየተነሳ ይናገራል። አንዳንዴ መደማመጥም ይጠፋል። ለእንግዳ ተመልካች ምናልባትም የከረረ ፀብ ውስጥ የገቡ ይመስላል። በመጨረሻ ግን ጭቅጭቁ ረግቦ፣ በአዋቂ ወይም በሽማግሌ የመፍትሄ ሀሳብ ቀርቦ፣ እንደገና አረቄ ወርዶ ተመራርቀው ይለያያሉ። የአካባቢው ነዋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በስራ ተጠምደው ስለሚኖሩ ችግራቸውን የሚወያዩት፣ አጥፊዎችን የሚወቅሱትና አልሚዎችን የሚመርቁት በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ይመስላል። እርግማን ይፈራል፣ ምርቃት ይከበራል። የከተማው ጉራጌ በከተማ ምስቅልቅል ውስጥ የጠፋበትን የእሱነት ወግና ባህል ገጠሩ ውስጥ ያገኘዋል ... ጉዞውም ለዚሁ ነው።

ጉራጌው የእንኳን ደህና መጣህ የመጀመሪያ መስተንግዶውን አጠናቆ፣ የአካባቢውን ሰዎች ሸኝቶ ከወላጆቹ ጋር ብቻውን ሲቀር ጐጆውንና ግቢውን መቃኘት ይጀምራል። ወላጆቹ ከዓመት ዓመት እያረጁ ሄደውበት ይሆናል። ሆኖም ከገጠር ጋር የሚያገናኘው ክር ሙሉ በሙሉ ይበጠሳል የሚል ስጋት የለውም። በእልፍኙና በጓዳው ጭስ መጨሱ አያቋርጥም። ድርቅ መክት የሆነው እንሰት ከቶውንም ከጓሮው አይጠፋም። እትብቱ የተቀበረበት ግቢና ጎጆ ምንጊዜም ፆሙን አያድርም። እሱ ለልጁ፣ ልጁም ለልጅ ልጁ ራስን የመፈለጉን ባህል እያወረሱ የሰባት ቤት ጉራጌ ምድር ህይወት እንዲቀጥል ያደርጋሉ። ሁሉም ይህን የሚያደርግበት የእናት መሬቱና የእንሰት አደራ አለበት።

ከከተማ ቪላ ጋር የሚነፃፀረውን እልፍኝ ለማሰራት የሚጠይቀው ገንዘብ ጉልበትና ትዕግስት ቀላል አይደለም። የሣር ቤቱን መስሪያው ጥሬ ዕቃ ሙሉ የሚገኘው ከአካባቢው ነው – እንጨት፣

ልጥና ሣር። የአሠራር ጥበቡ ግን ውብና የሚያስደንቅ ነው። አንድ ምስማር ሳያርፍበት ቤት ሆኖ በጠንካራ ምሶሶ ይቆማል፣ ለብዙ አመት ሳይነቃነቅ ይኖራል። አንዳንዶቹ ቤቶች የከብት ማደሪያን ከመኖሪያ ጎጆአቸው ነጥለው ይሰራሉ። አንዳንዶቹ ግን እንደጥንቱ ያንኑ ትልቅ እልፍኝ ከፋፍለው ለመኝታም፣ ለማብሰያም፣ ለከብት ማደሪያም ይጠቀሙበታል። ዘመናዊ የተባሉት የሣር ቤቶች የጭስ ቤቱን በግድግዳ የለዩ ቢሆኑም እልፍኝ ውስጥ ጭስ መጨሱና ጉልቻ መቀመጡ አይቀርም። ጭሱ የጎጆዋ የእስትንፋስ ምልክት ተደርጐ የተወሰደ ይመስላል። ምግቡም፣ መጠጡም፣ ጨዋታውም፣ ምርቃቱም፣ የሚካሄደው በእሳቱ ዙሪያ ጭሱን እየሞቁ ነው።

ሰላሳ ሰው በሚመክት ጀበና የቅቤ ቡናውም እየተፈላ ሲጠጣ ይውላል። እዚህም ላይ ባለቤት ብቻውን እንዳይጐዳ መረዳዳት አለ። ለእንግዳው አክብሮትና ፍቅር ሲባል የቅርብ ጐረቤቶች የየራሳቸውን ቡና በጀበና አፍልተው ያመጣሉ፤ ሦስትና አራት ትላልቅ ጀበናዎች ይደረደራሉ። ጀበናዎቹን ከብቦ ወሬ እየሰለቁ ሳይታክቱ መጠጣት ነው። ክትፎው ቅቤ፣ ሥጋ ማጣቀሻው ቅቤ ... ቡናው ቅቤ ... ።

ጉራጌው ለመናፈስ ወይንም ወገቡን ለመፈተሽ ወደ ጓሮው ወጣ ሲል፣ በረዥሙ የተነጠፈው የእንሰትና የጫት ተክል ውስጥ ይገባል። አሁንም በሀሳብ ባህር ወደኋላው ብዙ ዘመን ተጉዞ የእንሰትን ውለታ ያስታውሳል። ከልጅነት እስከ እውቀት አንዴም ለድርቅ ሳይዳርግ ወላጆቹን መግቦ ያኖረና እሱን ያሳደገ እንሰት ነው። አሮጌው እንሰት እድሜውን ጨርሶ ሲወድቅ ወጣቱ እንሰት በቦታው ይተከላል። ትንሹ የእንሰት ችግኝ ደግሞ የወጣቱን ቦታ ይይዛል። በስብሶ የረገፈው የአሮጌው እንሰት ቅጠል ለአዲሶቹ ማዳበሪያ ሆኖ ያገለግላል። የጉራጌና የእንሰት ቁርኝት በዚሁ ዓይነት ይቀጥላል። ጉራጌው ከእንሰቱ ወጣ ብሎ አሻግሮ ሲመለከት የልጅነት ትዝታው ይቀሰቀስበታል። ለጨዋታ ይውልባቸው የነበሩት ሜዳዎች፣ ለትምህርት ወይንም ለስራ የተመላለሰባቸው ቀጫጭንና ወጣ ገባ የገጠር መንገዶች፣ ከጭፍጨፋ የተረፉትና ከእሱ ዕድሜ በላይ የኖሩት ትላልቅ ዛፎች፣ መንደሮችን እያቋረጡ የሚፈሱ ወንዞች፣ ከየአቅጣጫው በመፍለቅ ህዝቡን ከውኃ ጥም ያዳኑ ምንጮች ... ሁሉም ይታዩታል። ምናልባትም ትዝታ ፈንቅሎት ዕንባ ይተናነቀዋል። የጉራጊቷ ልጅ የከተሜነት ባዶ ጭንምብሉ ወልቆ፣ ወደ ውስጡ ተመልክቶ፣ ራሱን አግኝቶታል ማለት ነው። የመስቀል የዕለቱ ዕለት ከቀትር በኋላ ከብት ይታረዳል። የቻለ በግሉ ያርዳል፣ ያልቻለም ቅርጫ ይገባል። ሆኖም ሁሉም ግቢ ከብት የማረዱ፣ የመግፈፉና ብልት የማውጣቱ ሥራ የሚካሄደው በደቦ ነው። መጀመሪያ በዕድሜ ታላቅ ከሆነው ቤት ይጀመርና በተዋረድ ይቀጥላል። ከብቱ ተጠልፎ ለእርድ ከመጣሉ በፊት የተለመደው ምርቃት ይካሄዳል። ከብቱን የገዛው ይመረቃል፤ በሄደበት ሁሉ አድባሯ እንድትጠብቀው ደጋግሞ ይመረቃል። በየቤቱ ከገባ በኋላ ሥጋውም የሚበላው እየተጠራሩና በጋራ ነው። ሥጋው ቤት ገብቶ ከተቆራረጠ በኋላ ለምግብ ማቅረቢያነት የሚያገለግለው "ይወደረ" እልፍኝ ውስጥ በረዥሙ ተነጥፎ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ከብቦ ይቀመጣል። ቢላዋውና ሥጋው በየአጠገቡ ይደረደራል። የገጠሯ የጉራጌ ሴት ስትደክምበት የከረመችውን ቆጮ ታቀርባለች። ለሥጋው ማጥቀሻ ሚጥሚጣ ቅቤ ተለውሶ በየመሀሉ ይቀመጣል። አሁንም ምግብ ከመጀመሩ በፊት ጉራጌው ለዓመት ስንቅ የሚሆነውን ምርቃት ይቀበላል።

"በህብት ላይ ህብት፣ በጮማ ላይ ጮማ ይስጥህ"

"አሜን"

"ሀሳብህ ሁሉ ይሙላልህ"

"አሜን"

"እስመጪና ላኪ ሁን"

"አሜን"

"በፒያሳ መንገድ ትልቅ ሱቅ ክፈት"

"አሜን"

"እግዚአብሔር ከምቀኛ ይጠብቅህ"

"አሜን"

"ትረፍ"

"ከእኔ የጐደለ እግዚአብሔር ይጨምርልህ"

"አሜን" የሚሉና ሌሎች ምርቃቶች ቢያንስ በሶስት ትላልቅ ሰዎች ይመረቃል።

ከዚህ በኋላ በባህላዊ የመመገቢያ ዕቃዎች የቀረበውን ሥጋ እየቆረጡ በረዣዥሙ የቀንድ ማንኪያ "አንቀፎ" መከስከስ ነው። ሻኛ በአካባቢው ትልቅ ክብር ስላለው ከሌላው ስጋ ጋር አብሮ አይቀርብም። በተለየ ጊዜ ጐረቤትና የቅርብ ዘመድ ተሰባስቦ፣ በክብር ለብቻው ቀርቦ ተባርኮና ተመርቆ ነው ሻኛ የሚበላው። ጥሬ ሥጋው ሆድ ውስጥ ተንሸራሽሮ ቦታውን ሳይለቅ ክትፎው ደግሞ ይከተላል። የእንሰት ቅጠል ለመያዣነት ተጠቅልሎ በእጅ በእጅ ይሰጣል። በቅቤ የተጥለቀለቀውን ክትፎ በመያዣዋ ቅጠል "ጥለስ" ተቀብሎ ለመብላት በቂ ችሎታና ጥንቃቄ ያስፈልጋል። እንደእውነቱ ከሆነ በቅቤ የተዋጠው ክትፎ በማንኪያ ይጠጣል እንጂ አይበላም ማለት ይቻላል። የተሰጠውን የጨረሰ እስኪጠግብ ይጨመርለታል። በስተመጨረሻም ለመበተኛ የአረቄ ግብዣው ይቀጥላል። ምርቃቱም ይዥጐደጐዳል።

ማታ ሁሉም ችቦውን እያቀጣጠለ ለጋራ ደመራ ይወጣል። በቤተክርስቲያን አቅራቢያ ለብዙ ቀናት ወይም ወራት ቀደም ብሎ የቆመው

የደመራ እንጨት በደንብ ደርቆ ይጠብቃል። ከከተማ በእንግድነት መጥቶ በየጎጆው ያረፈው ከተሜና የአካባቢው ህዝብ እዚህ የጋራ ደመራ ላይ ይገናኛሉ። ሁሉም ከየቤቱ አቀጣጥሎ ያመጣውን ችቦ የጋራ ደመራው ላይ ይጨምራል። ትልቁ ደመራ በቁስ ተባርኮ ይቀጣጠላል። የችቦው አስተሳሰር ህብረትን ይመስላል። ብዙ ችቦዎች ደግሞ አንድ ትልቅ ደመራን በማጀብ ትልቅ ብርሀን ይሰጣሉ። በርተው የታዳሚዎቻቸውን ፊት በተስፋ ካበሩ በኋላ አመድ ይሆናሉ። ጣቶች በዙሪያቸው የጉራጊኛ ዘፈን በመዝፈን ፍሙን ይሞቃሉ። የአዛውንቶች የጋራ ምርቃት ለጋራ ጉዳይ ለመጨረሻ ጊዜ ይካሄዳል።

“ሀገራችንን ሰላም ያርግልን”
“አሜን”
“መሬታችንን ፆም አያሳድርብን”
“አሜን”
“ልጆቻችንን ይባርክልን”
“አሜን”
“እርሻችን የተቃና ይሁን”
“አሜን”
“ጦርነትን ያርቅልን”
“አሜን”
“በመንገድ ሥራ፣ በልማት፣ በትምህርት አካባቢያችን ይደግ”
“አሜን”
“እግዚአብሄር ከኛ ጋር ይሁን”
“አሜን”

የመስቀል በዓል በምርቃት ተጀምሮ በምርቃት ያልቃል። ከተሜው ጉራጌ በቂ የእረፍት ጊዜ ካለው በባህሉ መሠረት እስከሰባት ቀናት ከዘመዶቹ ጋር ተቀምጦ ክትፎውን ሲበላ ይከርማል። የቸኮለም በትውልድ ሠፈሩና በዘመዶቹ መሀል ራሱን አግኝቶ፣ የአመት ምርቃቱን ተቀብሎ፣ ልቡ በተስፋ ተሞልቶ፣ ኪሱን ሞልቶ የሄደውን ገንዘብ ለዘመዶቹ አከፋፍሎ ጨርሶ ... ወደ መኖሪያ ከተማውና ወደ ስራው ይመለሳል። ሌላው መስቀል ደርሶ ለሌላ ምርቃት እስኪበቃ ድረስ አመቱን ሙሉ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ይሰራል።

ገጠሩ ከከተማው ምንጊዜም መገናኘት አለበት። የከተማው የጀርባ አጥንት ገጠሩ ነው። ይህንን የግንኙነት ክር ለማጥበቅ ከተወላጁ በላይ ማንም ሊመጣ አይችልም። እኔነት በከተማ ምስቅልቅል ውስጥ ተውጦ እንዳይቀር በመፈለጉም ሂደት ይረዳል። ከተሞችና ገጠሮች ግንኙነታቸውን አጥብቀው ከተጓዙ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ብቻ መሆኗ ይቀራል። ጤናማው የገጠር አየርም የተበከለውን የከተማ አየር ያድሳል።

ይህን ጽሑፍ የላኩልን አቶ አበበ ካዲስ አበባ ናቸው።

# ከሠርግ በፊት ለሚደረግ ዕቅድ

ከከበደ ኃይሌ

ስለ ጋብቻ፣ በትዳር ላይ ስለሚያጋጥሙን ችግሮችና ስለትዳር ጓደኛ አፈላለግና አገኛኘት ዘዴዎች በተደጋጋሚ በተለያዩ መድረኮች ሃሣብ፣ ትችትና ምክር ተሰጥቶባቸዋል። ይህ ርዕስ በተለይ የሚያተኩረው ግን ትዳር ለመመስረት ዕቅድ ያለን ሰዎች የድግስ ዝግጅት ከማድረጋችን በፊት መውሰድ ስለሚገባን ቅድመ ዝግጅቶች የሚመለከት ነው።

ይህንን ጽሁፍ ላዘጋጅ ያነሳሳኝ በርዕሱ ባለሙያ፣ የህግ ሰው፣ የሠርግ አዘጋጅ ድርጅት አባል፣ ወይም ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዙ የንግድ መስኮች ውስጥ የተሰማራሁ ግለሰብ አይደለሁም፣ ነገር ግን ስለርዕሱ የሰማኋቸውን፣ ያነበብኳቸውን፣ ያየኋቸውንና የገጠሙኝን ሠርግ ነክ ነገሮችን በጽሁፍ ለአንባቢያን ባቀርበው የሚጠቀሙበት ወገኖች ይኖሩ ይሆናል በማለት ሲሆን እግረ መንገዴንም ከርዕሱ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ነጥቦች እየነካካሁ ለማለፍ እሞክራለሁ። ከትውልድ አገርና ከወላጅ ቁጥጥር ስር ወጥቶ ራስን ማስተዳደር ከተጀመረ ልጅነት እንደሌለ የምንኖርበት አገር የአኗኗር ጠባይ በተግባር እንድንማር አድርጎናል። የተማርነው በትምህርት ቤት፣ ያልተማርነው ከአካባቢው ልዩ ልዩ ጽሁፎችን ከማንበብ፣ ከመስማት፣ ከመመልከት ትምህርት ቀስመን አዕምሮአችን ጎልምሷል። አካባቢያችን ባህላችንንና አስተሳሰባችንን ለውጦታል። በአካልና በጠባይ ተለውጠናል። ንዋይና ንብረት አፍርተናል። ለብቻ ከመኖር ይልቅ ከሰው ጋር ደባል ሆኖ መኖር ከኢኮኖሚውና በሃሳብ ከመረዳዳትና ከማህበራዊ ኑሮ አኳያ ጥቅሙን ተረድተናል።

አሁን የሚቀረን የትዳር ጓደኛ የሚሆነንን ሰው ፈልገንና አፈላልገን ካገኘን በኋላ ተቀራርበንና በሃሳብ፣ በጠባይና በዓላማ አንድነታችንን አረጋግጠን ዕቅድ አውጥቶ ትዳር መመስረትና ከዚያም ልጅ ወልዶ ማሳደግ ነው። ስለትዳር ጓደኛ አፈላለግና አገኛኘት ከአሁን በፊት በጽሁፍ ከወጡትም ሆነ በቀጥታ ከተገኙት መረጃዎች አንፃር ስንመለከተው በወላጆች በኩል የሚመሰረተው ትዳር ኋላ ቀር ነው የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም እኔ ግን አልደግፈውም። ለምን? ስለምትሉ የራሴን ምክንያቶች ላቅርብ።

የአገራችን ባህልም ሆነ የማንኛውም አገር ህብረተሰብ የሚደግፈው በቤተሰብ በኩል የሚመሰረተውን ትዳር ነው። ምክንያቱም ወላጆች የልጆቻቸው፣ ልጆች የወላጆቻቸው ነፀብራቅ ናቸውና ነው። የትዳር ጓደኛሞቹ ተገናኝተው የተጋቡት ከዚህ ውጭ ከሆነ በመካከላቸው አለመተማመን፣ በትንሹም በትልቁም ንዝንዝና ንትርክ ስለሚኖር ትዳራቸው የሚሰምረው የአብዛኛው አይደለም። ይህም ሲባል ከወላጅ ፈቃድ ውጭ በሆነ መንገድ የተጋቡ ትዳራቸው ጨርሶ አይሰምርም ወይም በወላጆች በኩል የተመሰረተ ትዳር ችግሮች የሉበትም ለማለት ሳይሆን በወላጆች አማካይነት የተመሰረተው ትዳር አብዛኛው ዘላቂነት ያለው መሆኑን በተግባር የተመሰከረለት ነው ለማለት ነው።በአሜሪካንና በሌሎች አገሮች ተሰድደን የምንኖር ኢትዮጵያውያኖች በአጠገባችን የሚኖሩ ወላጆች

ጥቂቶች ስለሆኑ የትዳር ጓደኛ ለማግኘት በቤተክርስቲያን፣ በጓደኛና በዘመድ በኩል ተገናኝቶ መተዋወቁ ተቀራርቦ ልብ ለልብ በሃሳብ መገናኘቱ በቀጥታ በግል ተገናኝቶ ከመጋባት ይሻላል ባይ ነኝ። ካለበለዚያ ለብዙ ጊዜ አብሮ እየገቡ እየወጡ በመቀራረብ እርግጠኛ የትዳር ሰው መሆናችንንና ዓላማን መርምሮ ለመረዳት ከፍተኛ ጥረትንና ትዕግሥት ቢጠይቅም ትዳር መመስረት ጊዜንና መስዋዕትነትን ይጠይቃልና በዚህ ልንጠቀም እንችላለን። ከሁለት በአንዱ መንገድ ለትዳር የሚሆኑንን ሰዎች ካገኘን በኋላ ወላጆቻችን በቅርብ ከሌሉና አገር ቤት በህይወት ካሉ ለትዳር የተስማማነውን ሰው በደብዳቤ የተደገፈ ፎቶግራፍ ለቤተሰብ ልኮ በማስተዋወቅ ጋብቻችንን እንዲያፀድቁልን መጠየቁ ለወላጆች ክብር ለተጋቢዎቹ ደግሞ ምርቃት ይሆናል። ለግንዛቤ ያህል፣ አሜሪካውያኖች ለጓደኝነትም ሆነ ለጋብቻ ከተፈቃቀዱ ከወላጆች ጋር በቅድሚያ ማስተዋወቅ አንዱ ተለምዷዊና ችኩል ባህላቸው ነው። ይህንን የሚያደርጉበት ምክንያት በአገሩ ውስጥ ወንጀል ፈጻሚው ሰው ቁጥር በመብዛቱ ለጥንቃቄ ሲሆን፣ በተለይ ለትዳር ከተፈላለጉ ወላጆች የቅርብ ክትትል በማድረግ ከሁሉ አቅጣጫ ያላቸውን ውጫዊ ባህርይ ለማጥናት እንዲረዳ ነው። በሁለቱ መካከል ለጋብቻ የገቡት ቃል ፀንቶ እየገፋ ከመጣና ዕቅዳቸውን ለማከናወን ሙሉ ጥረታቸውን ካሳዩ ወላጆች የሚችሉትን ድጋፍ ሁሉ ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም።

በአሁኑ ጊዜ በእኛ ዘንድ የጋብቻ አይነት መልኩን እየለዋወጠ በመምጣቱ ትዳር ፈላጊዎች በተለያየ መንገድ ተዋውቀው ብዙ ተቀራርበው ማንነታቸውን በጥልቅ ሳይተዋወቁ የሚጋቡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን እየሰማንና እያየን ነው። አንደኛው መንገድ ወደ አገር ቤት በመሄድ አይናችን ያረፈባትን ሴት/ኮረዳ በመምረጥ ወደ አሜሪካን ለመመለስ የተሰጠን የቪዛ የጊዜ ገደብ ሳይደርስ የጋብቻ ሥርዓቱን በመፈጸም ሚስት በማግባት አሜሪካን ከተፍ እንላለን። ይህ አይነቱን የጋብቻ ዘዴ ኩዊክ ፒክ (Quick Pick) የተባለ ስም ተሰጥቶታል። ሁለተኛው መንገድ ሚስት ለማግባት ፍላጉት ያለን መሆኑን አገር ቤት ለሚኖሩት ዘመዶቻችን ስናሳውቅ እነሱም እኛን ትስማማለች ብለው ያመኑባትን ሴት መርጠው መስማማቷን በቀጥታም ሆነ በዘመዶቿ በኩል ጠይቀው ካረጋገጡ በኋላ ጠቅላላ ቁመናዋን የሚያሳይ ፎቶግራፍ ይልካሉ። ከወደድናት በስልክ በማነጋገር በደብዳቤ በመጻጻፍ በድምጽ ከተዋወቅን በኋላ እኛም ፍላጉታችንን እንገልጽና ካመቸን ወደ አገር ቤት ሻገር ብለን አግብተን እንመለሳለን። ካላመቸንም ቪዛ አውጥተንላት ወይም በጉብኝት እንድትመጣ አድርገን ስትመጣ እዚህ አብረን ሠርጉን ደግሰን ትዳሩን በይፋ እንያያዘዋለን። ይህ አይነቱን የጋብቻ መንገድ ፌዴክስ (FEDEX) የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ሌላው የጋብቻ ዓይነት ለጥቅም ስንል የምንጋባ ወገኖች አለን። ይህ ዓይነቱ የጋብቻ ዘዴ የሚፈፀመው የገንዘብና የማቴሪያል ፍላጐታችንን በረጅም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሟላት ዕቅድ ሲኖረን ይህን ያሟላሉ ብለን የገመትናቸውን ሰዎች ተሟሙተን በማግባት ነው። ወደአርዕስቱ ልመለስና አካባቢን መስሎ መኖር ብልህነት ነው። በመሆኑም የጋብቻ ሥርዓትና ዝግጅትም ከአገራችን የጋብቻ ሥርዓትና ዝግጅት ፍጹም የተለየ መሆኑን ለሁላችንም ግልጽ ነው። እናም ስለሠርግ ዕቅድና ዝግጅት ከአገራችን አኳያ የተመለከትነው እንደሆነ ለሰርጉ የማቀዱንና የመዘጋጀቱን ጉዳይ አሉን ብለን በምንመካባቸው ሰዎች ላይ የተጣለ ሆኖ ተጋቢዎች የሚፈለጉት ለምክክር ይሆናል እንጂ በሠርጉ ላይ ያለን ተሳትፎ መጠነኛ ነው። አሁን ከምንኖርበት የስደት አገር አንፃር ስናየው ግን ዕቅድ አውጪዎቹም፣ አዘጋጆቹም፣ ደጋፊዎቹም በአብዛኛው እኛው ትዳር መሥራቾቹ ነን። ሌላው ድጋፍ ሰጪ ነው። በዚህ ምክንያት ጊዜና ጉልበት ለመቆጠብ ስንል ወደ ባለሙያዎችና ሆቴሎች ዘንድ እናመራለን። ሃሳቡ አማራጭ የሌለው ቢሆንም በቅድሚያ እኛ ዕቅድ አውጥተንና ተዘጋጅተን ቀርበን ካልተጠቀምንባቸው ዝግጅቱ ካለን በጀት ቁጥጥር ውጭ ይሆንብናል። አንዳንዴ ትዳር ይዞ መኖርን እንመኝና ስለዝግጅቱ ገና ስናስበው እየከበደን ሃሳቡን ጨርሶ እንሰርዘዋለን። ዝግጅቱን ከጀመርን በኋላም ይህ ይሁን፣ ይህ ይቅር በመባባል በዕቅድ ደረጃ ላይ እያለን ሳለ በሃሳብ ባለመግባባትና ባለመጣጣም አንዱ በአንዱ ላይ እያመካኘ ዝግጅቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሸጋገር ዕቅዱ ሳይሳካ ይቀርና ሳንጋባ ተለያይተን የቀረን ሰዎች ብዙ ነን። ታዲያ በእንደዚህ ያለ ጭንቀት ውስጥ ገብቶ ከመዋኘት ወጪ ወደማይጠይቅና ጊዜ ወደማይፈጅ የትዳር መመስረቻ ድርጅት ወይም መ/ቤት በመሄድ ጥያቄ አቅርቦ በህግ ፊት ተፈራርሞ በቀላሉ ትዳር መመስረት ይቻል የለምን? ይህን መንገድ መቼም ሁላችንም እናውቀዋለን። ግን ችግሩ ደግሞ ግርግሯን እንፈልጋታለን።

መዝገበ ቃላት ትዳርን በሁለት ሰዎች መካከል የሚመሰረት የማህበራዊ ኑሮ ውል ወይም ኮንትራት ነው ይለዋል። እኔም ይመስለኛል። ትዳር ሲመሰረት ከባድ ኃላፊነት ለመቀበል ቆራጥ ውሳኔ የምናደርግበት፣ ከፍተኛ ወጪ ባወጣ ድግስና ዝግጅት በብዙ ሰዎች ታጅበን ለንጉሥና ለንግሥት የሚሰጥ ክብር ያህል ለአንድ ቀን ተሰጥቶን በታላቅ ደስታና ፈንጠዝያ የምናሳልፍበት፣ በቅርብ ዘመድና ወዳጅ ፊት ቆመን ከዛሬ ጀምሮ እሷ ሚስቴ ናት፣ እሱ ባሌ ነው በክፉና በደግ ጊዜም አንለያይም ተባብለን ቃል የምንገባበት፣ የወላጅና የአገር ሽማግሌዎች ምርቃት ተቀብለን ከወላጅ ስር ከመተዳደርና ከጓደኛ ጋር ተዳብሎ ከመኖር ራሳችንን ችለን ለመተዳደር ቃል በመግባት ጨርቃችንን ጠቅልለን እንባ ተራጭተን የምንለያይበት፣ የገባነውን ቃል ኪዳን በተግባር ለመተርጐም ሀ ብለን የምንጀምርበትና ውለታ የምንፈርምበት ቀን ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ታልፎ የተገባው ቃል ኪዳን ተጥሶ ጋብቻን በቀላሉ ማፍረስ በቤተሰብ ላይ ችግር መፍጠር፣ ልጆች የአባት ወይም የእናት የቅርብ ፍቅር ሳያገኙ እንዲያድጉ፣ ወደ አልባሌ ስፍራ እንዲያመሩ፣ መጥፎ ጠባይ እንዲማሩ፣ ዲሲፕሊን ያልተሞላው ባህርይ በአዕምሮአቸው ውስጥ እንዲቀርፁ የሚያደርጋቸው አንዱ አይነተኛ መንስኤ ይህ የትዳር ጠንቅ ስለሆነ ይህንን ለመከላከልና ለማስወገድ ለሠርግ ዕቅድ ስንዘጋጅ በአንጻሩም ትዳር ምን ማለት እንደሆነ፣ ኃላፊነት መቀበል የቱን ያህል ከባድ መሆኑንና ማንኛውንም የኑሮ ውጣ ውረድ የኃላፊነት ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን በአዕምሮአችን ውስጥ ዕቅድ ይዘን የመንፈስ

ዝግጅት ማድረግ ያሻል። ያልታሰበ ወጪ ውስጥ ገብቶ ከመጨነቅ ትዳር በቀላሉ ለመመስረት እንደሚቻል ከላይ ጠቅሰነዋል። በእርግጥ ሠርጋችን በትልቅ ሆቴል ውስጥ ተደግሶ ብዙ ሰው ተጠርቶና ታጅበን ሠርጉ ሲከናወን ማየቱ የሁላችንም ምኞትና ፍላጐት ነው። ነገር ግን ሰው የሚኖረው እንደራሱ እንጂ እንደጐረቤቱ ስላልሆነ የገንዘብ አቅማችን በሚፈቅደው በጀት መጠን ዕቅድ አውጥተን መሰረጉ ታላቅ ጥበብ ነው። ይህን ለማከናወን የሚረዳው በበጀት ሊሸፈኑ የሚችሉ የዕቅድ ዝርዝር አውጥቶ ወጪን በመቆጣጠር በሥራ ላይ በማዋል ዓላማን ግብ መምታት ነው። ለዚሁ ጉዳይ ይጠቅማሉ ብዬ ያሰብኳቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸው ስለሆነ ትዳር ለመመስረት ስናስብ እንጠቀምባቸው።

1. በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሠርግ የደገሱ ሰዎችን አፈላልጐ ከእነሱ አንዳንድ መረጃዎችን በማግኘት ልምድ መቅሰሙ ስህተት ውስጥ ከመግባት ያድናል።
2. ከሁለቱ ትዳር መሥራቾች የሚፈለጉ የጽሁፍ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አዘጋጅቶ ለመገኘት እንዲረዳ በሰከነ መንፈስ ጊዜ ወስዶ ስለዝግጅቱም ሆነ ስለወደፊት ዓላማ በግልጽ መነጋገር ያስፈልጋል።
3. ሠርጉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለሚፈለጉ ዘመድና ጓደኛ ስብሰባ በመጥራት መድረኩን ለጥያቄና መልስ ክፍት በማድረግ ውይይት ከተደረገ በኋላ ማን ምን መስራት እንዳለበት የስራ ክፍፍል ማድረጉ ለባለጉዳዮቹ ሞራል ሲሰጥ በአንፃሩም ከዝግጅቱ ተሳታፊዎች ሊገኝ የሚችለውን የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የሰው ኃይል መጠንና ዓይነቱን ለማወቅ ያስችላል።
4. የህግ ባለሙያዎችንና የቤተክርስቲያን ኃላፊዎችን በቅድሚያ ማነጋገሩ ከትዳር መሥራቾቹ በኩል የሚፈለገውን ማንኛውም ማስረጃና የሚወስደውንም ጊዜ ለማወቅ ከመርዳቱም በላይ የጊዜ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ይጠቅማል።
5. ለሠርጉ ዝግጅት የሚረዱ ማንኛውንም አስፈላጊ ነገሮች በዝርዝር ይዞ የዋጋ ዉረታ (ፕሮፎርማ) ማሰባሰቡ ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚወጣውን የገንዘብ ልክ ለማወቅ ይረዳል።

እንግዲህ አርዕስቱን በሚመለከት ከላይ የተሰጡት አስተያየቶችና የዕቅድ አወጣጥ ስልቶች ለሠርግ ዝግጅት እንደመንደርደሪያ ሃሳብ ይጠቅማሉ ወይም ፍንጭ ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ። በመጨረሻም ለለሠርግ ዕቅድ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ትልቅ ፕሮጀክት ስለሆነ ግብን ለመምታት ከትዳር መስራቾች ያላሰለሰ ጥረትና ትዕግስት ይጠበቃል። ስለዚህ አጭር ለብሶ ወገብ ታጥቆ፣ እጅጌ ጠቅሎ ችግር ሳይበግረን የሰው ወሬ ሳይፈታን የትዳራችንን ዕድሜ ለማርዘም በአንድ ልብ ቆርጠን በመነሳት ኑሮን እንድንቋቋም ብርታቱን ይስጠን እላለሁ።

ከበደ ኃይሌ የአትላንታ ነዋሪ ናቸው።

## ለምን ስምንት ዓመት ወደ ኋላ?

በዘመን አሪት አብዛኛዎቹ የዓለም ህዝቦች ዘመናቸውን የሚቆጥሩት በፀሐይና በጨረቃ ነበር። ለምሳሌ ዕብራውያን በጨረቃ፣ ግብፃውያን ደግሞ በፀሐይ ይቆጥሩ ነበር። ክርስቶስ ሲወለድ ዕብራውያን ከጨረቃ ወደ ፀሐይ አቆጣጠር ተዛወሩ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በሰጠው የምህረት ተስፋ መሠረት ከልጅ ልጅህ ተወልጄ፣ በደጃፍህም እንደማንኛውም ህፃን ድሄ፣ እንደማንኛም ልጅ ሆኜ አድጌ ገቢረ ተአምራት ፈጽሜ፣ በመስቀል ተሰቅዬ፣ ሶስት ሌሊት፣ ሶስት መዐልት በከርሠ መቃብር አድሬ፣ በሶስተኛውም ቀን ተነስቼ አድንሃለሁ ብሎ እንደተናገረለት ፈጽሟል። ወደሲኦልም ወርዶ በሞቱ ዲያብሎስን ድል ነስቶ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ከሲዖል አውጥቶ ወደ ገነት አግብቷቸዋል።

ክርስቶስ 33 ዓመት በመሬት ሲኖር ድውያንን ፈውሷል፣ እውራንን አብርቷል፣ ለምፃሞችን አድኗል፣ አያሌ ተአምራትን ካከናወነ በኋላ ወደ አባቱ ተመልሶ አርጓል። ያረገውም በ33 ዓመት ነው።

ጥጦስ የተባለ ንጉስ ኢየሩሳሌምን አጥፍቶ ህዝቦቿን ለስደትና ለመከራ ዳርጐ መግዛት የጀመረው ክርስቶስ ባረገ በ37ኛው ዓመት በተወለደ በሰባኛው ዓመት ነው። በዚህ አቆጣጠር ኢትዮጵያና የጁልየስ ቄሳር ዘመን አቆጣጠር ተጠቃሚዎች ናቸው። ክርስቶስ በ33 ዓመቱ ወደ ሰማይ አረገ። ከ37 ዓመት በኋላ በጥጦስ ዘመነ መንግስት በሰባ ዓመት ኢየሩሳሌም ጠፋች ብለን ዓመተ ምህረቱን ከኢየሩሳሌም ጥፋት እንጀምርና እስከዛሬ ዘልቀናል።

ክርስቶስ ከተወለደ 1991 ዓ.ም. ብለን እንቆጥራለን።

በሌላ በኩል አብዛኛው ዓለም የሚጠቀምበት ዓመተ ምህረት አቆጣጠር ከኢትዮጵያና ከጁልየስ ቄሳር አቆጣጠር በሰባት ዓመት ይበልጣል። ለምሳሌ እኛ መስከረም አንድ ቀን 1991 ዓ.ም. ብለን እንቆጥራለን። ጐርጐርዮሳውያን ደግሞ 1998 ብለው በሰባት ዓመት ይቀድሙናል።

ምክንያቱ እንዲህ ነው። ፓፓ ጐርጐርዮስ 13ኛ የኛን የዘመን አቆጣጠር አሻሻልሁ ብለው የጐርጐርዮሳውያኑን በሰባት ዓመት አሳደጉት። እንዴት አድርገው? ብሎ መጠየቅ ያባት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው በ33 ዓመቱ ሳይሆን በ44 ዓመቱ ነው። ጥጦስ ኢየሩሳሌምን ያጠፋው በሰባ ሰባት ዓመት ነው። እኛ በ33 አረገ የምንለው እንዳለ ሆኖ የጐርጐርሳውያን 44 ሲደመር 77 ይሆናል ልዩነቱ ይህ ብቻ ነው።

ሌላው ማስታወስ የሚገባ የዓመቱ ቀናት 365 በ3 ዓመት፣ 366 ለአንድ ዓመት ይሆናል። ፈረንጆች ጳጉሜን "ሊፕ ይር" ሲሏት በማንሸራሸር ከ12ቱ ወራት ውስጥ በአምስቱና በስድስቱ ላይ ይለጥፏታል። እኛ ግን 13ኛ ወር ብለን በመንግስት የደመወዝ ሊስት እንደ ወር ባትቆጠርም በውሃ፣ በመብራት፣ በቴሌፎን በቤት ወጭ ሁሉ ተረስታ ያስቸገረች ወር ናት። በቱሪዝም ኢንዱስትሪ በኩል ለ13 ወራት ፀሐይ የማይጠልቅባት አገር እየተባለች ትጠራለች።

በደርግ ዘመነ መንግስት የአንድ ወር ደመወዝ ለድጐማ እየተባለ ይሰጥ ስለነበረ "ሰርቲን መንዝስ ኦፍ ሰንሻይን" የሚለውን "ኢለቨን መንዝስ ኦፍ ሳላሪ" እየተባለ ይገለጽ ነበር። ■

# ዜና ቤተ ክርስቲያን

## ቅዱስ ሲኖዶስና ርክበ ካህናት በኮሎምበስ ኦሃዮ ተካሄደ

ከጥንት ቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣው ቅዱስ ሲኖዶስና የርክበ ካህናት ጉባኤ በውጪ ዓለም በምዕራብ አገሮች በኮሎምበስ ኦሃዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ከጥቅምት 25 — 27 1991 ዓ.ም.፣ ተካሄደ። ይህንንም ጉባኤ የመሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሲሆኑ ብፁዓን ጳጳሳትና ከአስቴቱ የተጠሩ የአድባራት አስተዳዳሪዎች አበው መነኮሳት፤ ካህናትና ዲያቆናት በጉባኤው ተሳታፊ እንደነበሩ የደረሰን ዜና ያበስራል።

በዚህ ወደ ሃያ የሚጠጉ በውጪ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ባካተተው የቅዱስ ሲኖዶሱና የርክበ ካሁናቱ ጉባኤ ላይ ብዙ ውሳኔዎች ተላልፈዋል። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የተከሰተው ችግር የቆየና ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑ ቢታወቅም ሥልጣነኞች ሕዝቡን አለያይተው እንዲጨፋጨፍ በማድረግ፤ በዚህም ምክንያት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቃጠሉ፤የቤተ ክርስትያን አባቶች እንዲገደሉ፤ እንዲታሠሩና እንዲሰደዱ መደረጋቸውን ከፉኛ በመቃወም፤ የአገር መሪዎች ነን ባዮቹ አንዷን ኢትዮጵያ ከሁለት ከፍለው ዛሬ የሚፋለሙባት ቦታ ሳይሆን ዳር ድንበራችን ጥንታዊ ታሪካችን ቀይ ባህር መሆኑን ሁሉም እንዲረዳው አደራ በማለት ጉባኤው ጠንካራ ውሳኔ አስተላልፏል። ኢትዮጵያ አገራችን ከጥንት ጀምሮ ፈተና ሲገጥማት ዋና መሣሪያ አድርጋ የምትጠቀምበት ሰው ሰራሽ የጦር መሣሪያን ሳይሆን ጸምና ፀሎት ስለሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነት ከአገራችን ይወገድ ዘንድ በየአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ ምህላና ፀሎት እንዲደረግ ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ ጥሪውን አስተላልፏል።

ከዚህ በተጨማሪ ቅዱስ ሲኖዶሱ ሌሎች ውሳኔዎችን ያስተላለፈ ሲሆን ከነኚህ ውስጥ፤ አብያተ ክርስቲያናትንና የወንጌል ትምህርትን ለማስፋፋት በዓመት አንድ ጊዜ በሚደረገው ቅዱስ ሲኖዶስና ርክበ ካህናት ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያ ቃለ አዋዲ በሚደነግገው መሠረት ከደብሩ አስተዳዳሪ ጋር ከምዕመናን የሰበካ ጉባኤ አንድ ተወካይ፤ ከወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት አንድ ተወካይ እንዲሳተፉ መወሰኑ ታውቋል።

ከጉባኤውም በኋላ በዚሁ በኦሃዮ የጥቅምት መድኃኒያለም  በዓለ ንግሥ ሥርዓተ ቅዳሴው በቅዱስ ፓትርያርኩ እየተመራ በደመቀ ሥነ ሥርዓት መከበሩ ታውቋል። የኦሃዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔያለም ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ተነስቶ ባደረገው አስተዋጽዖ በቅዱስነታቸው ካቴድራል ተብሎ ተሰይሟል። በበዓሉም እጅግ በጣም ብዙ ሕዝብ የተገኘ ሲሆን የአትላንታ ቅድስት ማርያም ካቴድራል፤ የኒው ዮርክ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤የቦስተን ቅዱስ ሚካኤል፤ የካናዳ ቶሮንቶ መንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል፤ የችካጎ መድኃኒያለም ወጣት መዘምራን በቦታው በመገኘት ለበዓሉ ትልቅ ድምቀት የሰጡ መሆኑ ታውቋል። የወጣት መዘምራን አንድነት በጣም ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ከቦታው የደረሰን ዜና በተጨማሪ አብስሯል።

## የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል መንበረ ፓትርያርክ ሆነች።

ኦሃዮ የተካሄደው ቅዱስ ሲኖዶስ የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል መንበረ ፓትርያርክ እንድትሆን መወሰኑን ለማወቅ ተችሏል። አትላንታ የቅዱስ ፓትርያርኩ መንበር መሆኑ ያትላንታ ነዋሪዎችን ያስደሰተ መሆኑንና ቅዱስትቸውም በቅርቡ ተጠቃለው ወደ አትላንታ እንደሚገቡ ታውቋል። እጅግ ብዙ ምዕመናን ያላት አትላንታ ሁለት የታወቁ አብያተ ክርስቲያናት ያላት ሲሆን እነሱም የቅድስት ማርያም ካቴድራልና የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሲሆኑ ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት የቅዱስ ፓትርያርኩን ወደ አትላንታ መምጣት በታላቅ ደስታ መቀበላቸውን ለማወቅ ችለናል።

**የግጥም ጉባኤ**



# ደብል ሔሊክስ
## (የጥምር አብራክ ገመድ)

ከልሣኑ ሥምረት

ጉንጉናቱን እያጣመረ፣ አየር እየተረተረ...... ነፋሱን እያዋቀረ
እርስበርሱ እያሳረረ፣ አብራክን እያሰገበረ.....መንታ መንታ ሆኖ ሠገረ
በዝግመተ—ለውጥ እሩሩ ደቅሎ አስደቀለ....ተነባበረ ተዘራዘረ
አንድዮ ይቀደስና፣ ስሙ ለዘላለም ይጥና....."የቡሄ ጅራፍ" አስመሰከረ
ክሮሞዝም የሚሉት ገመድ የዘር ንዑስ ምጥን ምታት....ተዋረድን አስመነዘረ
የሕዝብን ሁሉ አንድነት ምልዐተ—ሥምረት.... አስረገጠ አስተናበረ።

ኸረ ማነው እርሱ ያልደፈረስ የደሙ ባህር ያልታመሰ.....ያልተናወጠ ያልተከለሰ
ጉልጥምጥሚቱ ያልታረሰ ደመ ነፍሱ ያልተገሰሰ.... ዓይነሥቡ ያልተዳሰሰ።
ሠርገኛ ጤፍን መስሎ ከቶ፣ ሲያሰኘው ፈልቶ.... ተያይዞ ያልቸፈረገ
ተርመስምሶ ዘሩን ቆልቶ፣ አንዱ ባንዱ ተላግቶ.... በጋራዊነቱ ያልሶገገ
የችግኝ መድበለ—ክንፉ፣ የምላጭ ምዕራፉ.... ሥሉቱ ሳይሠላ ያልዛገ
መሠረታዊው ሠደፉ፣ ሥሩ ቅርንጫፉ.... ተፈላቆ ያልተሰነገ
ሆኖ የቅልስ ቤት ጣሪያ፣ የክፍክፉ ሰንጣራ.... በገመድ ያልተሳረገ።

ዘር ሳትሆኑ ሳትረቡ፣ ሳታሼቱ ሳታፈሩ.. ትውልድን ሁሉ ለምታሳጡት
እስቲ ይውጣ ጉዱ፣ ይኸ'ጎድጎድ ነጎድጓዱ...የጠራ ዘር ለምትሉት .
እንዳልተያያዘ ግንዱ2 የጥምር አብራክን ገመዱ... ሙጃ መሰል ለምትነቅሉት
የቁማርን አዛውራችሁ፣ ለፈጣሪ መድባችሁ....ሕብረ—ሥባኤ ለምትዘምሩት።

የክልላችህ አሙካ፣ ሀረ ሕዋሱ አባ ሰንጋ.... ብትሸፍኑት ተከፈተ
እንኳን ለዛሬ ቀርቶ፣ ለትውልድ አሰግቶ .... ሥራይ በሥራይ አመረተ
እንጠያየቅ ማን አለ፣ ራሱን በራስ ያልፈነገለ.... ከሌላው ጋር ያልተንኳተተ።

በሕይወቱ ሠረገላ ሠግሮ ያልተንኳለለ ..... ሲያኘው ያልተዋሰበ
ደብል ሔሊክስ ጥምር ሾላ፣ በዘር ቆለጡ ያልሳለ....በቀስቱ ያልተከበበ
እንደሐረግ ተቃቅሮ፣ ሳይመራረጥ ተቃቅሮ..... እርስ በርሱ ያልተሳሳበ
በሰው ሰራሽ በተፈጥሮም፣ እረፍት በሌላት ዓለም... በትርምሱ ያልተዋከበ
የእንስቷን ክቡር ሙዳይ፣ ወለላዋን ያልቀመሰ..... ልቅ ገብቶ ያላጣጣመ
በፍላፃዋ ያልተቀሰፈ፣ በፍቅሯ ሰንኮፍ ያልተነደፈ.. በትንፋሿ ያልተረገመ።

እስቲ ምቱት፣ የትግል መሰንቆውን ... ክራሩንም ቃኙት
ግን ብቻ ጅማት ቆጥራችሁ፣ ስንኙን አትክፈሉት.... ረጋ ሰራሽ አታድርጉት
የጥምር አብራክ ሰንሰለቱን፣ የዘመናት ትሥሥሩን.. እንደሲባጎ አትቀንጭቡት።

ኸረ ምንድነው ግርግሩ፣ የክልላችሁ ቅጥአምባሩ . . . "የአውልያችሁ የአድባሩ"
የዘለላችሁ ትርትሩ፣ የድጓችሁ ድርድሩ . ....የቀለማችሁ ሁሉ ድምሩ
እስቲ እንጠያየቅ ስለሥሩ፣ ስለአብራክ መልክዐምድሩ...ስለጋራው ሸንተረሩ
ኸረ ምንድነው ግርግሩ፣ የክልላችሁ ቅጥአምባሩ... የነገራችሁ ነገሩ።

## እንቧ በይ ላሚቱ

የሚያጠቃሽ በሬው፣ ወይፈኑስ ምናለሽ
ሙማሽ ከሚያጓጓው፣ ካያ ጅቦ ስትሸሽ
መቆየት ደግ ነው፣ ዛሬስ አያ አህዮም
ለራሱ ከጀለሽ
እንቧ በይ ላሚቱ፣ ኧረ ዝም አትበይ
ወተትሽ ተጠብቶ፣ ጥጆችሽም አልቀው
አንቺ እንዳትበይ።

## እውነትና ንጋት

### ከመጽሐፈ ሲራክ

ትናንትም አለፈ
ዛሬም ያው ከነፈ
እውነትን ከንጋት ባንድ እያሳለፈ
መች ይቀራል ንጋት
መች ይሞታል እውነት
ጨኸት በመቀማት
በጊዜያዊ ድርጉ በብልጣብልጥነት።
በመቆያ መከፈልት ነገን በማያደርስ
ወንዝ በማያሻግር የግርግር ድግስ
ማን ይዘናጋና እውነት ከግብ ሳይደርስ!
ረዥም ተጓዦች አመለ ኩሩዎች
ለመቆያ መከሰስ ግዴለሽ ቋምቶች
እነርሱ ተርበው የህዝብ እንባ አባሾች
ጨለማውን ንደው ንጋት አብሳሪዎች፥
መቼ ይቆማሉ አንድ ቀን ሩጠው
በመከሰስ እንጀራ ሆዳቸውን ሞልተው
ከቶ እንዴት ሊደክሙ በቃኝን ተንፍሰው
በመቆያ ቁራሽ ወኔአቸውን ሰልበው
ይጓዟታል እንጂ ጨለማን ጠቅጥቀው
የአዲስ ዓለም ፍካት ንጋትን ተማምነው።
ይሮጡታል "እይ" ፅልመትን ጀርባ አርገው
ውሎ ላደረ እውነት ተስፋቸውን ጥለው።
ጨረቃን አያምኑም
ለወረት መቆሚን አይጠራጠሩም
ላታለማ አብርታ
ላትቀድስ አድርታ
ላትቆይ እንዲያ ፈክታ
እንደምትሸሽ ከድታ
ያውቃሉ ጠባይዋን የማይቆይ አመሏን
ምሁዋር ፈለጓን አነሳስ ጉዞዋን።
ትተዋት ቢነጉዱ ብሩህ ነው እጣቸው
በነገዋ ሙራ መድመቅ መሞሸር ነው።
ባንድ ለማትረጋ የሰማይ ላይ ውላጅ
ጨረቃ ድምቡልቦቃ አይሉም እንደልጅ
በመቆያ ብርሃን አይረግጡም የሰው ደጅ
እውነትና ንጋት ላንድነት ላይፈርጅ
"እና . . .
ንጋት የነገ ነው ፥ ይመጣል አይቀርም
እውነት ዘላቂ ነው ፥ በሀሰት አይሞትም
ምህላው መቆያው የትም አያደርስም
ይልቅስ መታረም፣ ትውልድ እንዳይረግም።

====== / / ======

## ቁጭት

ሞቴ ባይሆን የዘለዓለም
ቢኖር የብቻ ትንሳኤ
አሁን አሁን የሚነሳ
የትናንቱ ፍርጥም ክንዴ
ለሀገር ጠላት መች ሲሳሳ
ታጠቅ ያልኩት ያ ፈረሴ
ተነስ ካልኩት መቼ ይደክም
መቼ ይቆም፤
አደራ ያልኩት ተከታይ
አደራ ቢስ ሆኖ ሲገኝ
ለቅባትም ለወቀሳም
ጥሩ ነበር እኔ ብገኝ።

====== / / ======

## ከቅኔዎቻችን

●በዋግ አድርጋ በደላንታ
በቅሎዬ ጠፋች ተሳስታ
ፈረስ አገኘሁ ከወንድሜ
ኮርቻ አጣሁ ደግሜ።

●ባልንጀሮቼ እና እምስቱ
ቅኔና ድጓ ሲፈትቱ
ምስጢሩን እንኳ አላየሁ
እንዲያው ተከኜ ቀረሁ።

●እያም አዳራሽ ገብተን
አጉል ከንብንብ ሽፍንፍን
ከላይኛው ምች ላያድን
እንዳይታዩ ከወደዱ
ይልቁን በጋረዱ።

●ቢማጠኑህም ከመንገድ
አቤት ጌታዬ ብለህ ሂድ
እምትሟገት እንደሆን
እኛም ዳኛ አይደለን።
●ሥጋ ከተገኘ በእውነት
ኧረ አብስሉ ይብላው ስጡት።

●ለባላንጣዎች ዘንቦላቸው
አምሮላቸው መከራቸው
ለኛም ደግሞ አልተሰወረ
ደመናም ሆኖ አልቀረ።

# ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

☝ የጊዜው መፈክር ምንድነው?
☺ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን።

✡ ✡ ✡

☝ ክረምቱ አለፈ፣ ጦርነቱ ለምን አልተጀመረም? .. .
☺ ጦርነቱ እኮ ትምህርት ቤት አይደለም።

✡ ✡ ✡

☝ የዮሃ ምስክሩ አጐቴ ወደ ኤርትራ በመባረሩ በጣም አዘንኩኝ።
☺ እንዲያውም ጥሩ ነው ለአቶ ኢሳያስ ወንጌልን ይሰብክላቸዋል።

✡ ✡ ✡

☝ አስመራ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ጋዜጠኞች ለምንድነው ወገናዊነት የሚታይባቸው?
☺ የሮይተሯን ዘጋቢ እስር አይተው ጽዋው እንዳይደርስባቸው ሰግተው ይሆናል!

✡ ✡ ✡

☝ የመንግስት አፈቀላጤዋ ወ/ት ሰሎሜ ታደሰ ሰሞኑን ስለታሰሩት ጋዜጠኞች ለቢቢሲ የሰጡትን ሰማህልኝ?
☺ የሰሙትን ቢነግሩኝ አይቀልም?
☝ ስለጋዜጠኞች መፈታት ሲጠየቁ እሳቸው ግን "በጀርመን አገር እንኳ ስለናዚ የሚጽፉ ጋዜጠኞች ይታሰራሉ" ብለው አረፉታ።
☺ "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ" ብል ይስማማ ይሆን!

✡ ✡ ✡

☝ አንድ ወቅት "ነፍጠኛ" እያሉ ይደነፉ የነበሩት ሀሰን አሊ ምነው ያን ቁጣቸውን ለሻዕቢያ ቢያውሉት?
☺ ዛሬ ጊዜው ለእሳቸውም ማጠፊያው ያጠረበት ነውና ምነው ቢተዋቸው?

✡ ✡ ✡

☝ ሜጀር ጄኔራል ፃድቃን ስለ ሰራዊቱ መግለጫ የማይሰጡበት ለምንድው?
☺ "መግለጫ" እስኪሰጥባቸው እየጠበቁ ነው እንዳልል የሰማሁት የለምና አብረን መታገሱ አይከፋም።

✡ ✡ ✡

☝ አሜሪካ አስሩ ቦታ ጥልቅ ስትል ምነው የሻዕቢያን ጆሮ መቆንጠጥ ተሳናት?
☺ "የአፍሪካ ራስ ምታት እንዲሆን ስለፈለገች ነው" እየተባለላት ነው።

✡ ✡ ✡

☝ የተፈቱት ጄኔራሎች መቼ ነው ስራ የሚጀምሩት?
☺ ስለኢትዮጵያ አንድነት መቆርቆር ሲያቆሙ!

✡ ✡ ✡

☝ የመከላከያ ሠራዊታችን ተልዕኮ እስከ ምን ድረስ ነው?
☺ እስከመከላከል።

✡ ✡ ✡

☝ የስንቅ ዝግጅቱ ምነው ቆመ?
☺ "ሠራዊቱ መብላት አቁሟል" የሚል አሉባልታ እየተወራ ስለሆነ ይሆናል።

✡ ✡ ✡

☝ ከግንባር የሚመጡ ወሬዎች ሠራዊታችን ሻዕቢያን ለመደምሰስ ተዘጋጅቶ እየጠበቀ መሆኑን ነው የሚያበስሩት ግን ተግባሩ መቼ ነው?
☺ ያአራት ኪሎ ሹመኞች ትዕዛዙ ላይ ተኝተውበት ነው እየተባለ የሚወራው ለዚህ ይሆን?

✡ ✡ ✡

☝ "ጀግና በለው በለው ..." የሚለው ዘፈን ለምን አሁን አይዘፈንም?
☺ የአሁኖቹ መሪዎቻችን "እሣ በለው በለው ... " የሚለውን ነው የወደዱት።

✡ ✡ ✡

☝ ጥላሁን ገሠሠ በዚያን ሰሞን ግንባር ሄዶ "ምግብማ ሞልቷል" ብሎ የዘፈነው ለምንድነው?
☺ ሠራዊቱ የፍየል አጥንት ሲግጥ ስላየ ነዋ!

✡ ✡ ✡

☝ በኤርትራ ጤፍ ወደምንነት እንደተቀየረ ታውቃለህ?
☺ ወደ ሽቶነት!

✡ ✡ ✡

☝ አባ ጳውሎስ ወደ ኖርዌይ የሄዱበትን ምክንያት ሰማህልኝ?
☺ አዎን! ከኤርትራው አቻዎቻቸው ጋር ሊመካከሩ!!

✡ ✡ ✡

☝ ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ የወታደር ልብስ ለብሰው የሚታዩት መቼ ነው?
☺ የማን አገር ፕሬዚዳንት ፋሽን ሾው ሲሰራ አይተሃል?

✡ ✡ ✡

☝ ኢህአዴግ በረሃ እያለ የሴት ታጋዮች ነበሩት አሁን ምነው ሴቶችን መመልመል ፈራ?
☺ ባለስልጣኖቹሚስቶቻቸው እንዳይሄዱባቸው ሰግተው ይሆናላ!

✡ ✡ ✡

☝ የሼህ አላሙዲን ገንዘብ እንዲህ የሚበዛው በምንድነው?
☺ እየተዋለደ።

✡ ✡ ✡

☝ የኢትዮጵያ ቡና ክለብ ዘንድሮ ምነው ውጤት ራቀው?
☺ "የተለያዩ የቢራ ዓይነቶች መመረት ስለጀመሩ ተደናግጠው ነው" እያሉ የመርካቶ ልጆች ሲያሟቸው ሰምቻለሁ።

✡ ✡ ✡

☝ ምነው ለሠራዊቱ የሚበረከተው የፍየል ስጦታ ቆመ?
☺ "ዘመቻ ፍየል" ወደ "ዘመቻ ፈንዲሻ" መቀየሩን አልሰማህም?

✡ ✡ ✡

☝ የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽነሩን ተፈናቃዮች ማገታቸውን ሰማህ?
☺ ምን ዋጋ አለው? ኮሚሽነሩ ጤፍ አይደሉ ቡና አያጣጥሟቸው፣ መጠለያ አይደሉ አይኖሩባቸው።

✡ ✡ ✡

☝ በኬንያ ድንበር በተደረገው የጅምላ ጭፍጨፋ ምነው ፕ/ት ነጋሶ የሃዘን መግለጫ አልላኩም?
☺ በአንተ ቤት ፕሬዚዳንቱ "የኦነግ ታጋይ ስለነበሩ ነው" ይለኛል ብለህ ከሆነ ሞኝህን ፈልግ።

✡ ✡ ✡

☝ ባህታዊ ገ/መስቀልን ለመወንጀል ገንዘብ እየተሰበሰበ ነው የሚባለውን ወሬ እንዴት አየኸው?
☺ ለዚህ ነዋ አባ ጳውሎስ የሰላም እንቅልፋቸውን መለጠጥ ጀምረዋል የተባለው።

✡ ✡ ✡

☝ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቴክኒሽያኖች ሰሞኑን የአድማ ጉምጉምታ ይታይባቸዋል የሚባለው እውነት ነው?
☺ ከኤርትራውያን አገዛዝ ቢላቀቁም የደሞዛቸው ጉዳይ ገና ስላልተሳካላቸው ነው ይባላል።

✡ ✡ ✡

☝ ኤርትራዊ ጉረቤቴ ስትባረር ቤቷ ውስጥ ከሽያጭ የተረፉትን ዕቃዎቿን ሰባብራ በመሄዳ በጣም አዘንኩኝ።
☺ ፈንጂ ቀብራ አለመሄዷም እሷ ሆና ነው።

✡ ✡ ✡

☝ እነዚህ ኤርትራውያን ለምንድነው ልጅ በወለዱ ቁጥር ቸበር ቻቻ የሚያበዙት?
☺ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ላይ የደረሱ እየመሰላቸው።

✡ ✡ ✡

☝ አቶ ኢሳያስ አንድም የረባ ኢንዱስትሪ ወይም የተፈጥሮ ሃብት ሳይኖራቸው የኤርትራ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዕቃ ወደ ውጭ መላክን የሚያበረታታ ነው ሲሉ ምን ሊልኩ አስበው ነው?
☺ እየር/ንፋስ ሊልኩ ይሆናላ!

✡ ✡ ✡

☝ ኢሳይያስን እንዴት ታያቸዋለህ?
☺ የንጉሥ ልጅ ንጉሥ፣ የአርበኛ ልጅ አርበኛ፣ የባንዳ ልጅ ባንዳ የሚለውን እያስታወሱኩ።

✡ ✡ ✡

☝ የኛዎቹ ባለስልጣናት በሐኒሽ ደሴት ውዝግብ ጊዜ ለኤርትራ ወግነው አንዴ ተምዘግዛጊ፣ አንዴ ተወንጫፊ፣ እያሉ የሚሳይል አይነት ሲልኩም አልነበር?
☺ ነበራ! ዛሬማ ሚሳይሉ ወደኛው ዞሯል!

✡ ✡ ✡

# ከአበው

## ትምህርት በምሳሌ

### ታሪክና ምሣሌ
### በትንሽ ነገር መታመን
### የሚያስገኘው የክብር ልዕልና

መሢህ ሰገድ በሚል ስመ መንግስት ተቀብተው በ1713 ዓ.ም የነገሡት ዓፄ በካፋ ከልጅነታቸው ጀምሮ ያደጉት በጐንደር ቤተመንግስት አልነበረም። ከ12 በጎች ቆዳ ተውጣጥቶ የተሰፋ ቅጥልጥል የተማሪ ደበሎ ለብሰው ዐፅመ ጊዮርጊስ በሚል ስም እየተጠሩ ተራ ሰው መስለው ቅኔና የቅዱሳት መጻህፍትን ትርጉም ሲማሩ ከአንዱ ደብር ወደሌላው በማዘዋወር በጐጃም ክፍለሀገር ብዙ ዓመት ኖሩ። ትምህርታቸውንም በማጠናቀቅ ላይ ሳሉ የአባታቸው የአፄ ኢያሱ አጽዮም ሰገድ ልጆች ዳዊትና ተክለሃይማኖት በየተራ ሲነግሡ የመንግስታችን ተቀናቃኝ ይሆናሉ በሚል ፍራቻ ይዶልቱባቸው ስለነበር ከማኅበረ ሥላሴ ገዳም ተነስተው በሱዳን በኩል አቋርጠው ወደ ግብጽ ለመሰደድ ውሳኔ አደረጉ። በጉዞ ላይ ሳሉ ወባ ይዟቸው ታመሙ። በዚህም ጊዜ የቋራ ባላባት የሆኑ ቀኛዝማች እሸቴ የሚባሉ ደግ ሰው ወደቤታቸው ወስደው አስታመዋቸው ሲድኑ ከመልካቸው ማማር የተነሳ ተደስተው ከሴቶች ልጆቻቸው መካከል ታላቅ የሆነችውን ምንትዋብን ዳሩላቸው። ዐፅመ ጊዮርጊስ (የኋላው ዓፄ በካፋ) ግን ዘመዶቼን ጠይቁ ልምጣ በሚል ሰበብ ለጊዜው ተሰናብተው ሄደው በጎጃም ክፍለሀገር ከደብር ደብር እየተዘዋወሩ ትምህርታቸውን ማስፋፋት ቀጠሉ። ከጊዜ በኋላ ብዙ ፈተና አሳልፈው በአባታቸው በዓፄ ኢየሱስ አጽዮም ሰገድ ዙፋን ላይ ነግሰው ዘውድ ሲደፉ ያ የቋራ ባላባት ቀኛዝማች እሸቴ ሴት ልጃቸውን በመዳር ያደረጉላቸውን መልካም ስራ አስታውሰው ከሠራዊታቸው ጋር በታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት ታጅበው ለጉብኝት ወደ ቋራ ሄዱ። እዚያም እንደደረሱ ታላቅ የክብር አቀባበል ተደርጉላቸው ግብር የሚያበሉበት የተንጣለለ ዳስ ተሰርቶ ቆያቸው።እርሳቸው ግን ከጸሐፌ ትዕዛዝ ጋር በምስጢር ተመካክረው ልብሰ መንግስታቸውን ለውጠው፣ ዘውዳቸውን አኑረው የተራ ተማሪ በርኖስ ለብሰው በርሳቸው ዙፋን ሌላ እርሳቸውን የሚመስል ሰው አስቀምጠው ከሁለት ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ጋር ወደ ቀኛዝማች እሸቴ ቤት አመሩ። ቀኛዝማች እሸቴም ሲያያቸው ደስ ብሎት በተማሪ ቤት ስማቸው "ዐፅመ ጊዮርጊስ እንኳን ደህና መጣህ! ሚስትህ ምንትዋብም ስላንተ በማሰብ ላይ ነበረችና ይህችውልህ! እናንተ በቤት ሆናችሁ ዕረፍት በማድረግ ተጫወቱ። እኔ ግን ደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ዓፄ በካፋ አገሬን ሊጐበኙ በመምጣታቸው ደስ ብሎኛልና ወደርሳቸው ሄጄ ላገልግል" አሉ። ዐፅመ ጊዮርጊስም(በካፋ) "እኛስ ከርስዎ ጋር አብረን ብንሄድ አይፈቀድልንምን?" ሲሉ ጠየቁ። ቀኛዝማች እሸቴም "ይደክማችኋል ብዬ ነው እንጂ እንዲያውም ከእኔ ጋር ሄዳችሁ ቅኔ ብታበረክቱላቸው ደስ ይላቸዋል" ካሉ በኋላ ልጃቸው ምንትዋብ በንጉሡ ፊት የሚቀርብ ምግብ የተሰራበትን መሶብ ወርቅ ተሸክማ እየመራች ንጉሠ ነገሥቱ ወደአረፉበት ቦታ ሄዱ። እዚያም እንደደረሱ ጸሐፌ ትዕዛዝ (አዛዥ) ሲያዩአቸው ዐፅመ ጊዮርጊስንና ምንትዋብን ለይተው ወደ እልፍኝ አስገቡዋቸው። በዚያም ዐፅመ ጊዮርጊስ (ዓፄ በካፋ) የክብር ልብሰ መንግስታቸውን ለብሰው ዘውዳቸውን ደፍተው ከጐንደር ቤተመንግስት ተዘጋጅቶ የመጣውን የሠርግ ልብስ ለምንትዋብ አልብሰው በራስዋ ላይ የወርቅ አክሊል አድርገው ህዝቡና ሠራዊቱ ወደአለበት ትልቅ ዳስ ሲገቡ ጭብጨባውና እልልታው አስተጋባ። ወዲያውኑም መጽሐፈ ተክሊል ተነብቦ የጋብቻቸው ሥነሥርዓት በደስታና ክብር ተፈጸመ። በዚሁም ዕለት ቀኛዝማች እሸቴ ከደስታቸው ብዛት የተነሳ ደንግጠው ሁለት ቀን ታመሙ ይባላል። ከህመማቸው ሲድኑ ወደ ዓፄ በካፋ ዘንድ ቀርበው የደጃዝማች ማዕረግ ተሰጥቶአቸው የደንቢያና የአለማጣቁሳን ግዛት ተሰጡ ተብሎ ተጽፎላቸዋል።

እንግዲህ ይህን አጭር ታሪክ ያየነው ለትንሽ ምሳሌነት በመጥቀስ ነው። ነገር ግን ባለሙያ ጸሐፊዎችም ሆኑ የኪነት ሰዎች በድራማ መልክ ቀርጸው መድረክ ላይ ቢያቀርቡት ከዊልያም ሼክስፒር ሥራዎች አንዱን ክፍል የሚተካ ለመሆን በበቃ ነበር እላለሁ። አይመስላችሁምን? ፕሮፌሰር ፓንክረስት የተባሉ አንድ ታሪክ ዘጋቢ ኢትዮጵያን በሚመለከት ከሃያ መጻህፍት በላይ ጽፈው ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ አበርክተዋል። እርሳቸውም በሰጡት ምስክርነት ወደየትኛውም አገር ቢሄድ በቂ ታሪክ ለማግኘት ችግር ነው። ወደኢትዮጵያ የሚመጡ ጸሐፊዎች ግን ታሪክ ተትረፍርፎ ሰብሳቢ እንዳጣ መካሪ የትም ቦታ ተዝረክርኮ ያገኛሉ ብለዋል። የሚያሳዝነውም ነገር ይህን የመሳሰለ አስደናቂ ታሪክ ያላት አገር የራስዋ ታሪክ፣ ባህል፣ ሥነ ጽሁፍና እምነት በከፊል እየተረሳ የሌሎች አህጉር ታሪክና ባህል አድማቂ ሆኖ መገኘት አዲሱን ትውልድ የሚያስወቅስ ሆኖ መገኘቱ ነው። የአዲሱ ትውልድ ባለሙያዎችም (የኪነት ሰዎች) የራሳቸውን አገር ታሪክ በጥሩ ብዕር ቀርጸው ከማቅረብ ይልቅ የድራማው መድረክ ከውጭ አህጉር በተወረሱ የትርጉም ዝግጅቶች ተጣቦ ይታያል። አንዳንድ የውጭው ዓለም ድራማዎች ተተርጉመው አይቅረቡ ለማለት ሳይሆን ቅድሚያ ለሀገር ታሪክና ባህል ሆኖ ሌላው የሁለተኛነት ደረጃ ይሰጠው ማለታችን ነው።ወደተነሳበት ታሪክና ምሣሌ መደምደሚያ ስንመለስ በቀውጢ ጊዜና በፈተና ወቅት ችግር ላይ ለወደቁ ሰዎች መልካም ነገር ማድረግ ምን ያህል ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው ያስገነዝበናል። አንዳንዱ ወሮታ በዚህ ዓለም የሚከፈል መቶ እጥፍ ዋጋ የሚገኝበት ሲሆን አንዳንድ መልካም ሥራ ደግሞ በአዲሲቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የዘለዓለም ህይወት የሚወረስበት መሆኑን ታላቁ መጽሐፍ ያበስራል። ይህ አባባል የማይዋጥላቸው ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ ባለቅኔ የተናገረውን ቃል ቢያጤኑ መልካም ይመስለናል። እርሱም እንዲህ የሚል ነው፦

"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም
ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም።"

መጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው

## ቢስቁም ባይስቁም!!

ምንም እንኳ ስጠፋ ጠፋሀ የሚለኝ በማጣቴ ማኩረፍ ቢገባኝም ወሬ ወዳድ ነኝና ዛሬም ብቅ ብያለሁ። ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? የአገራችን ሁኔታስ እንዴት እያደረጋችሁ ነው? መቼም እንኳን ይህን የጦርነት ወሬ ሰምታችሁ እንዲሁም ፈገግ የማትሉም ብትሆኑ እኔ ደግሞ . . .

የዛሬን ጸሁፌን የምጀምረው ከዚህ በፊት ስለ ቆምጨአምባው የሚነገሩትን ቀልዶች (እውነተኛ) የጀመርኩትን በመቀጠል ነው።

ቆምጨ በአንድ ወቅት የወረዳው የእግር ኳስ ቡድን ግጥሚያ ይኖረውና በክብር እንግድነት ተጋብዞ ይሄዳል። በኳስ ሜዳው ተገኝቶ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ጨዋታው አልቆ እሱ የሚያስተዳድረው ወረዳ ቡድን በጨዋታው አሸንፎ ዋንጫውን ለመስጠት ዝግጅቱ ይጠናቀቃል። ከዚያ በፊት ግን ጓድ ቆምጨ ስለ ጨዋታው የመዝጊያ ንግግር ያደርጋሉ ይባልና በጭብጨባ ከመቀመጫው ይነሳል። "በመጀመሪያ ቡድናችን ለዚህ ዋንጫ በመብቃቱ የተሰማኝ ደስታ ከፍተኛ ነው። ቢሆንም ግን የአገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታ በጣም ደካማ በመሆኑ ምክንያት 11 ተጫዋቾች ሁሉ በአንዲት ኳስ ላይ ሲራኮቱ በማየቴ በጣም ነው ያዘንኩት፤ እና የወረዳችንን ህዝብ በብርቱ የማሳስበው ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት ለሚቀጥለው ጊዜ እያንዳንዱ ተጫዋች አንዳንድ ኳስ አግኝቶ እንደፈለገው እንዲጫወት አስቸኳይ መዋጮ እንዲደረግ አንድ ኮሚቴ እንዲሰይም አጥብቄ አሳስባለሁ" እንዳለ ይነገራል።

ሌላ ከቆምጨአምባው ወጣ ያሉ ቀልዶች ልጨምርና ልሰናበት፦

ወይዘሮ አስቴር መዘፋፈን የምትወድ ሴት ናት። ስትወጣም ስትገባም፤ ወጥ ቤትም ሆነ ... ስትሆን ማንጐራጐር ትወዳለች። እንደለመደችው ዘፈኗን ስትጀምር ባሏ ጥሏት ወደ ውጭ ይወጣል። በኋላም በጣም ትናደድና፦

"እረ አንተ ለመሆኑ እኔ ሁልጊዜ ዘፈን ስጀምር ወደ ውጪ የምትወጣው ለምንድነው?" ብላ ትጠይቀዋለች።

ባልም ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ "እኔማ ወደ ውጪ የምወጣው ጐረቤቶቻችን የምደበድብሽ እንዳይመስላቸው ነው" ብሏት እርፍ።

☆ ☆ ☆

አንዲት ህፃን ልጅ አንድ ልብስ ሰፊ ዘንድ ትሄድና "አባባ ለአሻንጉሊቴ የሚሆነኝ የተቀራረጡ ጨርቅ ስጡኝ?" ትለዋለች። ልብስ ሰፊውም እሺ ብሎ የተለያዩ የተቆራረጡ ጨርቆችን ለቃቅሞ ይሰጣታል። ልጅቷም ጨርቁን ከተቀበለች በኋላ "ለዚህ ስንት ነው የሚያስከፍለው?" ብላ ስትጠይቅ፤ ልብስ ሰፊው "ሚሚዬ ለዚህ የሚያስከፍለው እዚች ጉንጨ ላይ ሳም ማድረግ ብቻ ነው" ይላታል። እሷም "እሺ አባባ ለእናቴ ይህንኑ እነግራታለሁ፤ ዋጋውን ጠይቂና እኔ እከፍለዋለሁ ስላለችኝ ነው" ብላው ሄደች።

☆ ☆ ☆


# የእትመትና የትርጉም ሥራ

በኮምፒውተር የአማርኛና
የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

ከለር ማስታወቂያዎች፣
መጽሐፍት፤ መጽሔቶችና
የተለያዩ የአማርኛና
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን በጥሩ ዋጋ
በፍጥነትና ጥራት ባለው ሁኔታ
ለማሰራት ከፈለጉ ደውለው
ገነትን ያነጋግሩ።

በተጨማሪ የትርጉም ሥራዎችን እንሠራለን

ስልክ — (404)508-4657
ፋክስ — (404)508-2447

# <u>ሰንጠረዥ</u>

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺ ዓመት
SAEFU © Copyright 1998

ይህን የሰንጠረዥ ጨዋታ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይና በሰያፍ በመክበብ የቀሩት ኖጌያት የሚያነቡትን በመፈለግ በጊዜዎት ይዝናኑ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሻ | ለ | ቃ | ወ | ል | ደ | ጋ | ብ | ር | ል | ካ | በ | ባ | ኃ |
| ቢ | ሙ | ረ | ገ | ም | ብ | መ | ሸ | ሻ | ሳ | የ | ር | መ | ይ |
| ሠ | ም | ዓ | ል | ያ | ተ | ድ | ላ | ባ | ው | ያ | ር | ባ | ሉ |
| ው | ዳ | ለ | ቃ | ር | ራ | አ | ጋ | ብ | ው | ዬ | ባ | ራ | አ |
| ር | አ | ሜ | ረ | ማ | ደ | ዲ | ነ | ጻ | ዬ | ሻ | ሻ | ሰ | ለ |
| ቴ | ዎ | ዓ | ደ | ነ | ስ | ዘ | ው | ር | ለ | ሸ | ጊ | አ | ቃ |
| ፋ | ቤ | ሉ | ጎ | ዳ | ታ | ሎ | ብ | ም | መ | ር | ዚ | ን | እ |
| ን | ድ | ው | ማ | ኪ | ስ | ገ | ለ | ሞ | ዮ | ሮ | ጉ | ግ | ን |
| ክ | ጣ | ዩ | ስ | ሰ | ሪ | ም | ሰ | ጊ | አ | ሜ | ት | ዳ | ግ |
| ድ | ጋ | ጸ | ስ | ራ | ሰ | ወ | ል | ደ | ማ | ር | ያ | ም | ዳ |
| ን | ግ | ጄ | ው | ሸ | ስ | ኤ | ል | ለ | ኒ | ኢ | ት | ግ | እ |
| ሮ | ጎ | ታ | ማ | ዋ | ሙ | አ | ሊ | ም | ማ | ታ | ን | ፈ | ብ |
| ጅ | ፈ | ደ | ሴ | ሳ | ዮ | ጵ | ዳ | ግ | ን | እ | ማ | ሰ | ተ |
| በ | ያ | ከ | ን | ቲ | ባ | ኃ | ይ | ሉ | ይ | ና | ስ | ሐ | ው |

ሐ
ሐሰናይ

መ
መርዚን
መሸሻ (ራስ)
መሸሻ (ደጃች)
ሙአሊም ማታ
ማኅደረ ቃል

ረ
ራስ እንግዳ
~~ራስ ኪዳነማርያም~~
ራስ ወልደማርያም
ራስ ጸጋ
ራስ ውቤ
ራስ አዳሉ

ሰ
ሳሙኤል ጊዮርጊስ
ሳባጋዲስ (ፊታውራሪ)

ሸ
ሻለቃ ወልደጋብር

በ
በካል (ቢቶደድ)
በጅሮንድ ከንፉ
ቢሠውር (ቢቶደድ)
ባሻ ለምለም
ባርያው
ባርያው ጳውሎስ(ራስ)

ተ
ተድላ(ፊታውራሪ)
ተሰማ እንግዳ(ደጃች)

ኀ
ኃይሉ (ጥርሶ)

ነ
ንጉሤ (አቶ)

አ
አለቃ እንግዳ
አማኒ
አብተው (ልጅ)
አዳም
እንግዳ (ባሻ)

ከ
ከንቲባ ኃይሉ
ከንፉ (በጅሮንድ)

ወ
ዋሴ (ቢቶደድ)

ዐ
ዓለሜ ጓሉ (ደጃች)

ዘ
ዘነበ (አለቃ)

የ
ይመር

ደ
ደማሸ (ቢቶደድ)
ደብተራ ደስታ

ገ
ገለሞ (አጋፋሪ)
ገረሙ
ጎጄ (ደጃች)

ጠ
ጣዩ

ፈ
ፈንታ (አዛዥ)
ፊታውራሪ ገብርዬ

## መልሱን ባድራሻችን ላኩልን።

# ቃላት በሰንጠረዥ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | ■ | 6 | 7 | 8 | 9 | ■ |
| 11 | 12 | 13 | 14 | ■ | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | ■ | ■ | 25 | 26 | 27 | ■ | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | ■ | 35 | 36 | 37 | ■ | 39 | 40 |
| 41 | ■ | 43 | 44 | 465 | ■ | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | ■ | 55 | 56 | ■ | 58 | 59 | ■ |
| ■ | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | ■ | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | ■ | ■ | 76 | 77 | 78 | ■ | 80 |
| 81 | ■ | ■ | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | ■ | 98 | 99 | 100 |

## ወደ ጎን

1. ከቤት ፊትለፊት
6. ወንዴ ጾታ
11. ረካን
16. ሳይሞት
21. በአፉ በኩል ወደ ውስጥ ከተተ
25. ሠርቶ _ _ _
29. ጫፍ
31. ስህተት መረጉን መጠቆም
35. ድጋፍ ሊሰጠኝ
39. ቸር
43. ትምህርት መጨረስ
47. ክምር
51 አጭር
55. የቀሳፊ በሽታ ትንኝ
58. _ _ዚህ
62. የሁለተኛ ዲግሪ ትምሕርት
69. አሰልቺ
71. ዝግ ያልሆነ
76. የመሬት መለኪያ (ጋሻ እንደማለት)
84. ጠንካራ ድጋፍ
91. በማስተዋል
98. ትጨነቅ

## ወደ ታች

1. ሳይረፍድ ተጓዝ
2. በእግሯ ነካች
3. ማር ሠራተኛ
6. ተዋሰ
7. ጣና ዳር ያለ ከተማ
8. ተመልከት
9. ትገጥማለች
20. የልብ ምት
25. አልከራከር
33. ትዕቢት
48. ቀዳዳ
52. ሥዕል ቅርፅ
56 ሳታስበው ተተኮሰባት
67. ፊደሎች ሲገናኙ
70. ፊቱ የማይፈታ
71. ድንበር
78 የቤት ለማዳ እንስሳ
84. ይህ ዕቃ _ _ ነው?
85. ተናገረ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

| | 12 ISSUES | | 6 ISSUES | |
|---|---|---|---|---|
| U.S | $30.00 | ☐ | $16.00 | ☐ |
| Canada | $40.00 | ☐ | $22.00 | ☐ |
| Europe | $56.00 | ☐ | $30.00 | ☐ |
| Asia | $70.00 | ☐ | $38.00 | ☐ |
| Institutions | $80.00 | ☐ | $40.00 | ☐ |

*Please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ____________________

*Address:* ____________________

*City:* ____________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* ____________________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ____________________

*Address:* ____________________

*City:* ____________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* ____________________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*

# ADVERTISEMENT RATES ON LANDAFTA

ላ
ን
ዳ
ፍ
ታ

***LANDAFTA is An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic, the Official Language of Ethiopia.***

| | Single Issue | Two Consecutive Issues (Paid One time) | Three Consecutive Issues (Paid One Time |
|---|---|---|---|
| BACK COVER OUTSIDE | ☐ $240.00 | ☐ $420.00 | ☐ $600.00 |
| INSIDE | ☐ $180.00 | ☐ $330.00 | ☐ $450.00 |
| FRONT COVER INSIDE | ☐ $200.00 | ☐ $360.00 | ☐ $500.00 |
| TEXT PAGES PAGE 1 | ☐ $150.00 | ☐ $280.00 | ☐ $400.00 |
| ANY FULL PAGE | ☐ $140.00 | ☐ $260.00 | ☐ $380.00 |
| HALF PAGE | ☐ $ 95.00 | ☐ $170.00 | ☐ $240.00 |
| 1/4 PAGE | ☐ $ 70.00 | ☐ $120.00 | ☐ $145.00 |

Please, fill out the following form to place an ad on LANDAFTA.

Name: ____________________

Address: ____________________

City: ____________________ St. ________ Zip: ____________________

Contact Person: ____________________

Phone:( ) ____________________ Fax:( ) ____________________ E-Mail: ____________________

Please, place my ad as indicated above on Landafta starting ____________

A copy of the advertisement is attached.

A check or money order in U.S. $ for the amount selected above should be attached with the order. (ክፍያ በቅድሚያ መከናወን አለበት)

Signature ____________________ Date ____________________

For Office use


LANDAFTA
P.O.Box 49301 - Atlanta, GA 30309
Phone: (404)508-4657 - Fax: (404)508-2447
E-Mail: landafta@aol.com


For Office use

# MRA'G TRAVEL, Inc.

ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

92 Piedmont Ave. NE - Atlanta, GA 30303



ለዓለም አቀፍና
ለአገር ውስጥ ጉዞዎ አለንልዎ!!

EXCELLENT SERVICE - SPECIAL FARE - GROUP FARE

ገነት ፈቀደ – ፕሬዚዳንት
GENET FEKEDE
PRESIDENT

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቀጥታ በረራ**
**ከአዲስ አበባ — ዋሽንግተን ዲ.ሲ.**
**ከJune 4, 1998 ቀን ጀምሮ**
**ዘወትር ሐሙስና ቅዳሜ**
**በረራውን ለማስተዋወቅ**
**ልዩ ታላቅ ቅናሽ**

SPECIAL INTRODUCTORY FARE

**Please, call** (404) 577-4404
(404) 577-4682
(404) 577-4889
**Fax:** (404) 222-9305

Cerified Agent for:
ARC - IATA - CLIA


**Also Call:**
**San Fransisco Area**
**Aderaw Yeshiwas**
**Selam Fekede**
**Phone: (510)829-0529**
**Fax: (510)829-0529**

የኢትዮጵያ አየር መንገ
**ETHIOPIAN**
**AIRLINES**
*Fly ETHIOPIAN*
የኢትዮጵያ አየር መንገድ
ልዩ ወኪል
CONSOLIDATOR FOR
*ETHIOPIAN AIRLINES*

# Allstate®

**You are in good hands.**

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978 - Fax: (404)299-6266



Theodros
Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

- ⇨ **AUTO**
- ⇨ **HOME OWNER'S**
- ⇨ **RENTERS**
- ⇨ **LIFE**
- ⇨ **BUSINESS**
- ⇨ **COMMERCIAL AUTO**

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indeminity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**